# የሕያው ተስፋ ድምጽ



በድረ ገጽ | በሬድዮ | በሥነ ጽሁፍ

ይህም የመንግስት ወንጌል በዓለም ሁሉ ይሰበካል። ማቴ 24፥14



# ቅድስና ለእግዚአብሄር

እግዚአብሄርም ምድርን አየ ። እነሆም ተበላሸች ሥጋን የለበሰ ሁሉ በምድር ላይ መንገዱን አበላሽቶ ነበርና ። --እግዚአብሄርም ኖህን አለው አንተ ቤተሰቦችህን ሁሉ ይዘ ህ ወደ መርከቡ ግባ በዚህ ትውልድ ፊት ጻድቅ ሆነህ አይቼሃለሁና! (ዘፍ 7:1)

## ሌማታችን

### እግዚአብሄርን መፍራት

በፓስተር ዳንኤል መኮንን

እግዚአብሄር ሊፈራ የሚገባው ብቻውን ያለ ድንቅ ጌታ ነው። የዳዊት መዝሙር ም.34 ቁ 6-11 ላይ እንደዚህ ይላል ፡- “ ይህ ችግረኛ ጮኸ እግዚአብሄርም ሰማው ከመከራውም ሁሉ አዳነው የእግዚአብሄር መልአክ በሚፈሩት ዙርያ ይሰፍራል ያድናቸውማል ።እግዚአብሄር ቸር እንደሆነ ቅመሱ እዩም፤ በእርሱ የሚታመን ሰው ምስጉን ነው። የሚፈሩት አንዳችም አያጡምና ቅዱሳን ሁሉ እግዚአብሄርን ፍሩትይሳል።



ሰዶምና ገሞራ ከተማዎች በግብረሰዶማውያን ሐጢአት ምክንያት በእሳት ጠፉ ( እግዚአብሄር ግን ሎጥና ልጆቹን አዳነ )፣ ሚስቱ ወደኂላዋ ስታስብ የጨው አምድ ሆና ቀረች ።

በሌላ ሥፍራ ደግሞ እግዚአብሄርን ስለመፍራቱ ተሰማለት ይላል ። በምሳሌ መጽሐፍ ላይ ከልጅነታችን ጀምሮ የምናውቀው የሚነገረን አንድ ጥቅስ አለ “እግዚአብሄርን መፍራት የጥበብ መጀመርያ ነው” የሚል መጽሐፍ ቅዱሳችንን ስናይ ከዘፍጥረት ጀምሮ እስከ ራዕይ ድረስ እግዚአብሄርን ስለመፍራት በስፋት ተቀምጦ እናገኛለን ።...ወደ ገጽ 4 ዞሯል

## ቤተሰባችን

### አለአግባብ ጋብቻና አስገድዶ መድፈር የተንሰራፋበት ህብረተሰብ

ከሐዋርያ ሉቃስ ወ/ጻድቅ

1ኛ. ጋብቻ ምንድ ነው?

ጋብቻ አንድ ለአቅመ አዳም የደረሰ ወንድና አንድ ለአቅመ ሄዋን የደረሰች ሴት አብሮ ለመኖር ቤተሰብ ለመመስረት የሚያደርጉት ስምምነት ወይም ቃልኪዳን ነው ። በጋብቻ ውስጥ ከምንም በላይ የተጋቢዎቹ ፈቃደኝነትና ስምምነት በጣም አስፈላጊ ሲሆን ተጋቢዎቹ በማንኛውም መንገድ ይመራረጡ ወሳኙ ነገር ሁለቱ ጋብቻ ውስጥ ለመግባት መፍቀዳቸው ነው ። ለይስሐቅ የምትሆን ሚስትን ፈልጎ የማግኘትን ሥራ የሠሩት አብርሃምና ሎሌው ነበሩ ። ይህንንም ሂደት ይስሐቅ የተቀበለው እንጂ የተቃወመው አለመሆኑን ዘፍጥ. 24 ከቁ 1–52 ላይ ለማስተዋል ይችላል ።

ወደ ገጽ 8 ዞሯል

## ወጣት ለክርስቶስ

### እንደጥበበኞች እንመላለስ

ከፓስተር ፍጹም ክበበው

ዛሬ የምንካፈለው የእግዚአብሄር ቃል ከኤፌሶን ም. 5 ቁ 15–20 ላይ ነው ። “እንግዲህ እንደ ጥበበኞች እንጂ ጥበብ እንደሌላቸው ሳይሆን እንዴእንድትመላለሱ በጥንቃቄ ተጠበቁ ፣ ቀኖቹ ክፉዎች ናቸውና ዘመኑን ዋጁ ። ስለዚህ የጌታ ፈቃድ ምን እንደሆነ አስተውሉ እንጂ ሞኞች አትሁኑ። መንፈስ ይሙላባችሁ እንጂ በወይን ጠጅ አትስከሩ ይህ ማባከን ነውና ፣ በመዝሙርና በዝማሬ በመንፈሳዊ ቅኔ እርስ በረእርሳችሁ ተነጋገሩ ለጌታ በልባችሁ ተቀኙና ዘምሩ። ሁልጊዜ ስለሁሉ በጌታችን በእየሱስ ክርስቶስ ስም አምላካችንና አባታችንን ስለሁሉ አመስግኑ”(ኤፌ5፥15-20)የኤፌሶንን መጽሐፍ ሐዋርያው ጳውሎስ በወህኒ ቤት ስለወንጌል ታስሮ በነበረበት ጊዜ ነው የጻፈው ። ይሄን መልዕክት ወደ ኤፌሶን ቤተክርስቲያን የላከው መልዕክት ነው።መልዕክቱን በሁለት መሠረታዊ ሐሳቦች ላይ ተንተርሶ ነው የጻፈው። የመጀመርያዎቹ ሶስቱ ምዕራፎች እግዚአብሄር በክርስቶሰ ለእኛ ምን እንዳደረገልን እግዚአብሄር ለእኛ የሠራቸውን የሚያስገርሙና የሚያስደንቁ ነገሮች ይናገራል ። ---

ወደ ገጽ 5 ዞሯል

በሕያው ተስፋ መንፈሳዊ ሬዲዮ አገልግሎት ሥነ ጽሁፍ ክፍል በየሦስት ወሩ እየታተመ የሚወጣ ጋዜጣ ቁ 4

አዘጋጅ ጥላሁን ታደሰ

በውስጥ ገጾች


ርዕሰ አንቀጽ

ሌማታችን ፡- እግዚአብሄርን መፍራት.ገጽ 4

ታውቃላችሁ ...ፖርኖግራፊ

ቤተሰባችን .አስገድዶ.መድፈ.

ራስ ይናገር ምስክርነት ወ/ሮ ተዋበች

ወጣት ለክርስቶስ -እንደጥበበኞች...

ከደብዳቤዎቻችሁ

የጥያቄዎ መልስ

# የሕያው ተስፋ ድምጽ

በሕያው ተስፋ ስነጽሁፍ ክፍል ተዘጋጅቶ
በየሶስት ወሩ የሚወጣ
አዘጋጅ ፡- ጥላሁን ታደሰ


## ቅድስና ለእግዚአብሄር

ቅድስና የሚመጣው እግዚአብሄርን በግል ከመውደድ የተነሳ ነው ፡፡ ዓለም አመፃዋ እየበዛ በሄደ ቁጥር የእግዚአብሄር የፍርድ ቀን እየቀረበ መሆኑን ያሳየናል ፡፡ ቅድስና ማለት <u>በአስተሳሰብ</u> ፤<u>በአነጋገርና</u> <u>በአካሄድ</u> ፍቅር ለሆነው ለእግዚአብሄር ሃሳብና ፈቃድ መገዛትና መለየት ማለት ነው ፡፡ ቅድስና ከአስተሳሰብ ይጀምራል ፡፡ ሰዎች በአስተሳሰባቸው ከተቀደሱ በአነጋገራቸውና በድርጊታቸው ይጠነቀቃሉ ፡፡ አስተሳሰባቸው በእግዚአብሄር ፊት ቅንና ቅዱስ ከሆነ አነጋገራቸውና ድርጊታቸው እንደ እግዚአብሄር ሃሳብ ይሆናል ፡፡ ማንኛውም የእግዚአብሄር ሰው ከአስተሳሰብ በመነሳት በሕይወት ምልልሱ ሁሉ ቅድስና ሊኖረው ያስፈልጋል ፡፡ የረከሰ አእምሮ እግዚአብሄርን ደስ አያሰኝም ፡፡ ዲያቢሎስም የሚሸነግለው ሐሳባችንን ነው ፡፡

የኃጢአት ሃሳብ ወደ አእምሮአችን ብቅ ሲል፡- ቃሉ ምን ይላል ; እኔስ እንደ እግዚአብሄር ሰው ምን ማድረግ አለብኝ ማለት ይገባናል ፡፡ የዲያብሎስን ሽንገላ አንስተውም ፡፡ ዲያቢሎስ የጠቀመን ለክብራችን የሚሟገት መስሎ በስውር ይቀርብ ይሆናል፡፡ ‹‹ተደፈርክ እኮ፣ በሐይልህ በሥልጣንህ ተጠቀም›› ሲል ይችላል፡፡ ወይም የሥጋ ምኞት ፣ የገንዘብ ምኞት ከሆነ ‹‹ይህ እድል አያምልጥህ ›› ሲል ይችላል ፡፡ ጌታ እየሱስን ‹‹አይሁንብህ›› ያለው የለው ሰይጣን ነበር፡፡ ግን የጌታ እየሱስ መልስ ድንቅ ነው ፡- “ወደ ኋላዬ ሂድ አንተ ሰይጣን የሠውን እንጂ የእግዚአብሄርን አታስብም” አለው ፡፡ ጌታ በምድር የተመላለሰው የራሱን ስምና ክብር ለማስጠበቅ ሳይሆን የአባቱን ፈቃድ ለመፈጸም ነው ፡፡ የእግዚአብሄርን ሃሳብ መፈጸም የምንችለው የእኛን ጥቅምና ክብር ወደ ኋላ አድርገን የእግዚአብሄርን ክብር ስንፈልግ ነው ፡፡ በአጠቃላይ በኑሮ፣ በአገልግሎት ና በህይወት ልዩ ልዩ ጌታን ሊያሳዝኑ የሚችሉ ሀሳቦች ሊመጡብን ይችላሉ ፡፡ ይህንን ሃሳብ እንደመጣ ማስተናገድ ሳይሆን መመርመር፣ መልካም ካልሆነም መቃወም ይገባናል ፡፡ በአስተሳሰብ በአነጋገርም ሆነ በአስተያየት መቀደስ ከመሪዎች ይጀምራል ፡፡ በተለይ በአሁን ዘመን በአብያተ ክርስቲያናት በኀላፊነት ስፍራ ላይ የተቀመጡና ልዩ ልዩ መንፈሳዊ ድርጅቶች አመራር ላይ ያሉ ክርስቲያኖች ለሌሎች ምሳሌና ሞዴል መሆን ስለሚገባቸው ለወገኖቻቸው ፍቅርና ቅንነትን የተሞላ አስተሳሰብ ሊኖራቸው ይገባል ፡፡ ለእግዚአብሄር መቀደስና በአንድነትና በፍቅር እርሱን ማሳየት የሚኖርብን ዘመን ቢኖር አሁን ነው ፡፡ እኛ ሁልጊዜ አሸናፊዎች ነን ፡፡ ለዚህም የእግዚአብሄርን ቃል ሁልጊዜ በመመገብ፣ በጸሎት፣ የእግዚአብሄርን እቃጦር በመልበስና (ኤፌሶን ም.6) ፍቅርን በማሳየት፤ እንዲሁም የግልና የህብረት አምልኮን በማጠንከር አሸናፊዎች እንሆናለን ፡፡ ቅድስና ለእግዚያብሄር ፡፡

# ታውቃላችሁን

# ወጣቱና ፖርኖግራፊ

ከእንዳለ በሽር

በቅርብ ቀን አንድ ወዳጄ አንድ ጉዳይ አጫወተኝ ፡፡ ያወጋኝን ወግ ሃሳቡን ለመስማት ጆሮዎቼ ጉጉታቸውን አበረቱ ፡፡ ልቤም በጉዳዩ ላይ ትኩረቱን አበረታ ፡፡ ጉዳዩ እንዲህ ነው ፡፡ በአንድ የክርስቲያን ወጣቶች ስብሰባ ላይ በተደረገ መንፈሳዊ ፕሮግራም ላይ አንዲት እህት ወደ ፖርኖግራፊ ሱሰኝነት እንዴት እንደተቀላቀለች ለተሰበሰበው አቅመ ዓዳምና ሔዋን ሁሉ በድፍረት ተናገረች ፡፡ አድማጭ ሁሉ በዚህ ባልጠበቀው የልጅቷ የቀደመ የሕይወት ተሞክሮ የሚገባበት ያጣ ይመስል አንገቱን ወደ መሬት ቀበረ ፡፡ ያም ሆነ ይህ ምስክርነቱ እውነት ነበር ፡፡ ይህች ልጅ እዚሁ በመዲናችን አዲስ አበባ ካሉት አንጋፋና የምሁራን መፍለቂያ በሆነው በአዲስ አበባ ዩንቨርሲቲ የሶስተኛ ዓመት ተማሪ ናት ፡፡ በምትማርበት የስድስት ኪሎ ካምፓስ ውስጥ ብዙውን ጊዜዋን የምታጠፋውእንዲሁም የምታተኩረው ተጠናውጧት ከነበረው የፖርኖግራፊ ምስል ላይ በመሆኑ መንፈሳዊነቷ ውሃ እንደሸረሸረው ቋጥኝ መልክ እያጣ ይሄዳል ፡፡ ይህ ችግሯ ኋላም ላይ ልክ አልፎ ከእንስሳት ጋር እንኳን ሳይቀር ድርያ እንደነበራት ትናገራለች ፡፡ የእግዚአብሄር አምላክ ምህረት አያልቅምና ዛሬ ልጅቱ ከዚህ ከተናወጣት የፖርኖግራፊ ሱስ ነጻ ወጥታ መልካሙን የእግዚአብሄርን ፈቃድ በሕወቷ እየተገበረች ትገኛለች ፡፡ ለዚህም ነው ሌሎችንም እንደርሷ አይነት የሕይወት ጎዳና ላይ ያሉቱ ይተርፉ ዘንድ በዚያ የወጣቶች ጉባኤ ውስጥ የጉዳዩን አስከፊነት በገሃድ አውጥታ ለመናገር የደፈረቸው ፡፡

<u>ለመሆኑ ፖርኖግራፊ ምንድነው?</u>

ለዚህ ግልጽ ትርጓሜ ዳንኤል ወርቁ ካሳ ባዘጋጀው የእንግሊዘኛ መዝገበ ቃላት ላይ እንዲህ የሚል ትርጓሜ ይገኛል ፡፡

- የወሲብን ድርጊት የሚያሳዩ መጽሐፍት / ፊልሞች
- ምግባረ ብልሹ / ወሲብን

ለማነሳሳት የሚደረግ ድርጊት ፡፡

ይህ ትርጓሜ ለዚህ ጽሁፍ ሃተታ በቂ ነው ፡፡ በዚህ ትርጓሜ ያልተካተተ ሃሳብ ቢኖር ፖርኖግራፊ በመጽሐፍትና በፊልሞች ላይም የመገኘቱን ጉዳይ አለማንሳቱ ነው ፡፡ የፖርኖግራፊ ጽንሰ ሃሳብ በግድግዳ ምስሎች ወይም በእንግሊዝኛ የሙያ አጠራር ‘ ግራቪቲ ኢሜጅ’ ተብሎ

በሚጠራው ላይም ይገኛል ፡፡ ለአብነትም የአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲን የተማሪዎችን ሽንት ቤት መጎብኘቱ በቂ ነው ፡፡ ከዚህም በተጨማሪ የፖርኖግራፊ

ምስሎች በበርካታ የኢንተርኔት ድህረገጾች ላይ ይገኛሉ ፡፡

የእነዚህ የፖርኖግራፊ ምስሎች በታዋቂ ፎቶግራፈሮች ፣ በሠዓሊዎች ፣ በግራፊክ ዲዛይነሮች ፣ በካርቱኒስቶች እንዲሁም በቪዲዮግራፊ ባለሙያዎች በምቹ ሁኔታ ተቀነባብረው ለደንበኞቻቸው ይቀርባሉ ፡፡

በፖርኖግራፊ ተጠቃሚነት ረገድ የታላቋ ልዕለ ሃያል ሃገር አሜሪካ ወጣቶች በግምባር ቀደምትነት ይጠቀሳሉ ፡፡ ዘጠና ከመቶ የሚሆኑት የአሜሪካ ወጣቶች የዚህ የፖርኖግራፊ ሱሰኞች በመሆናቸው ፤ ካለፉት ዓርባ ዓመታት ወዲህ ታይቶ የማይታወቅ የትምህርት ውጤት ድካም እንዳለባቸው በመስኩ ጥናት ያደረጉ ምሁራን ይናገራሉ ፡፡ ምክንያቱም ወጣቶቹ አብዛኛውን የትምህርት ውሎአቸውን የሚያሳልፉት የፖርኖግራፊ ምስሎችን በማየትና በማገላበጥ በመሆኑ ከፖርኖግራፊ ከሚገኘው የስሜት ንዳድ ተቋዳሽ ናቸው ፡፡ በእኛ በሃበሻ ምድርም እንደዚሁ!! ከላይ የመሰከርንላት ልጅት ለዚህ በቂ ምስክር ናት ፡፡

በዚህ በመዲናችን አዲስ አበባ ውስጥ በርካታ ወጣቶች የፖርኖግራፊ ተጠቃሚዎች ናቸው ፡፡ በተለያዩ ሚዲያዎች የሚቀርቡ ፖርኖግራፊዎችን በመመልከት ሊወጡ ካልቻሉበት ማጥ ውስጥ ይገኛሉ ፡፡ ታዲያ የወጣቱ ብቻ እንዳይገርማችሁ ፡፡ ባለትዳር ሰዎችም ( እነ ሹገር ዳዲ ) የዚህ ጉዳይ ሰለባዎች ናቸው ፡፡ አንዳዶቹን አግኝተን እንዳወያየናቸው ፖርኖግራፊን መመልከት የወሲብ ስሜቶቻቸው በቀላል እንዲነቃቁላቸውና ወደ ትዳር ወዳጆቻቸው ሄደው በቀላሉ ይረኩ ዘንድ መልካም አጋጣሚ እንደሚፈጥርላቸው አውግተውናል ፡፡ ሌሎች ደግሞ ፖርኖግራፊን የሚመለከቱበትን ሚስጥር ሲያወጉን ፡ “ቅድመ ጋብቻን ለመለማመድ” እንደሆነ ይናገራሉ ፡፡ ሌሎችም አሉ ይህን አሳማኝ ነጥብ የሚያወጉ እንዲህ በማለት ፡- ‹‹በቃ ሱስ ሆነብኝ ›› ይላሉ ፡፡ እዚህ ጋ ልብ ሊባል የሚገባው ጉዳይ ቢኖር ፖርኖግራፊን መመልከት ሱስ የመሆኑ ሚስጢር ነው ፡፡ ለዚህም ነው በርካታ ወጣቶች በልዩ የመለኮታዊ ድጋፍ ካልተረዱ በስተቀር ከፖርኖግራፊ ሱሰኝነት መላቀቅ ያቃታቸው ፡፡ ሌሎች ደግሞ አሉ ፖርኖግራፊን የሚመለከቱ ፡- ያላቸውን የስነ ወሲብ እውቀት ከፍ ለማድረግ ሲሉ ከትዳር አጋሮቻቸው ጋር ሆነው በአንድ የተወሰነ ቤት ውስጥ በጸጥታ ታድመው ፖርኖግራፊን ኢንጆይ ያደርጉታል፡፡

# ሬሱ ይናገር

**የ ወ / ሮ ተዋበች ምስክርነት**

እንደሚታወቀው ያለፉት የእምነት አባቶቻችን ለእውነት ሲሉ ራሳቸውን ለሰይፍ ስለት እስከመስጠት ታማኝ ሆነው ለእኛ ወይም አሁን ላለው ትውልድ የክርስቶስን ወንጌል አስተላልፈዋል ። በአሁኑ ዘመን ደግሞ እንደቀደመው ዘመን ሰይፍ መዞ ከእውነት የሚያስቀር ባይኖርም መልኩን በመለዋወጥ እውነትን ችላ እንድንልና እግዚአብሄርን በፍጹም ነፍሳችንና መንፈሳችን እንዳናመልክና እንዳንገዛለት የሚያደርጉን ብዙ ነገሮች አሉ። እኛም በእነዚህ ነገሮች ውስጥ ጸንተን እግዚአብሄርን አክብረን ለመጪው ትውልድ የወንጌል እውነት ማስተላለፍ እንድንችል በእምነታችን ጠንክረን መቆም አለብን ። ይህንን ያልነው ያለምክንያት አይደለም ። ጌታን በመከተላቸው ምክንያት ወዳጅ ዘመድ ጎረቤት ብሎም የአካባቢ ማህበረሰብ ባስነሱባቸው ተቃውሞ ውስጥ ጸንተው በመቆም ጌታን ያከበሩና ስለ ወንጌል ትልቅ ዋጋ የከፈሉ አንዲትን እናት ልናስተዋውቃችሁ ስለሆነ ነው።

ወ/ሮ ተዋበች ወ/ማርያም ይባላሉ። ተወልደው ያደጉት በሰሜን ሸዋ ዞን ቀወት ወረዳ ልዩ ስሙ ደብደቦ በተባለ ቀበሌ ገበሬ ማህበር ውስጥ ነው ። በትክክል የተወለዱበት ዘመን አያውቁትም። ይሁንና የ1933ቱ የጣሊያን ወረራ ጊዜ የመጀመርያ ልጃቸውን ወልደው እንደነበር አጫውተውናል ። ከዚህም ተነስተን በግምት ከ 86 ዓመት እድሜ በላይ እንደሚኖራቸው ተረድተናል ። የተወለዱበት ቦታ ገጠር በመሆኑና ወቅቱም ትምህርት የተስፋፋበት ጊዜ ባለመሆኑ የመማር እድል አላገኙም ። ይልቁንም በልጅነታቸው ነው የትዳርን ሃላፊነት የተቀበሉት ። እንደገለጹልንም ከአገቡአቸው ከህግ ባላቸው ከአቶ በየነ አራት ልጆችን አፍርተዋል ።

እንዲህ ይላሉ “”ጌታን ከመቀበሌ በፊት የነበረኝ ሕይወት ያው የዱሮው አምልኮ በማድረግ ሚካኤልንም፣ ሥላሴዎች፣ ማርያምንም ማህበር በመጠጣት ነበር ። እንደሃገሩ እንደወጉ ከህብረተሰቡ ጋር ከቤተሰቦቼ የወረስኩትን እያመለኩ እኖር ነበር ። በአካባቢው የወንጌል ምንነት አይታወቅም ። ማንም ስለእየሱስ አዳኝነት እንዲያወራ አይፈቀድም ። እንዴት ጌታን አገኘሽ ብትይኝ ፤-የባለቤቴ ከሌላ የተወለደ ልጃቸው ክርስቲያን ነበር ። ያሳድዱት ነበር ። ታዲያ ለእኛም አንዳንዴ ይነግረን ነበር። ሃገሬው ግን እንዲህ ያለ ነገር ከየት አመጣህ እያሉ ያሳድዱት ነበር ። ጌታ መቼም ሥራው ድንቅ ነውና አይኔን አሳወረና ሃኪም ቤት ከደሴ ከተማ ወዲያ ቦሩ የሚባል ቦታ ባለቤቴ የዘውኝ ሄዱ ። እዚያ መምህር ተፈራ የሚባሉ ጓደኛቸውን አገኙ ። አንተ አቶ በየነ እዚህ ምን አመጣህ ? አሉት ሚስቴ ታማ አይንዋን ታውራ አለ ። ይኸውልህ እኔ አራዳ ጊዮርጊስ ነበር የምቀድሰው ። አራዳ ጊዮርጊስ ስቀድስበት የኖርኩትን ጥዬ አሁን ጌታን አመልካለሁ ። እንካ በዚህ አምልክ ብለው መጽሐፍ ቅዱስ ይሰጡአቸዋል ። ያንን ይቀበላሉ ። ያንን ይቀበሉና ሲመጡ እኔንም ነይ እንሂድ አሉ ። አንዴ ምነው ልጁን ስታሳድዱ ኖረው እንግዲህ እኛ ደግሞ ምን እንሆናለን በዚህ እድሜአችን? ስላቸው ፤ ባልና ሚስት አንድ አካል አንድ አምሳል ነው ። እኔን መምሰል ይገባሻል አሉና ሳልታከም ቃሉን እዚያው መከታተል ጀመርኩ ። ስድስት ወር እዚያው ተቀመጥኩ። አባ የሚሉአቸው ሰውዬ ሲያስተምሩን ፤ ሲያስተምሩን ቆዩና እዚያ ጌታን አገኘሁ ። እንግዲህ ጌታ ሆይ አልኩ፤ እንግዲህ ጌታ ሆይ አዳነከኝም ተውከኝም አንተ ነህና ሃገሬ አልገባም ጅብ ይብላኝ እንጂ ሃገሬ አልገባም ብዬ እዚያው ቁጭ አልኩ ።ዶክተሩ ከታከምሽ አይንሽ ያይልሻል ግቢ አሉኝ። አይይ አልኩና ገባሁ። ጌታ ሲደርስልኝ እንደገና ሃኪሙ መረመሩኝና ኦፕራሲዮን አደረጉኝ ። የሁለቱንም አይኔን ሞራ አንድ ቀን ገፈፉኝ። አይኔም በራ። የእርሱ የጌታ እጅ ነበረበት ። ባለቤቴም መጡ። እሳቸውም እኔም ጌታን አገኘን። አይኔም በራልኝ። እያየሁ ወደ ቤቴ ተመለስኩ ። ክብር ለእርሱ ይሁን።”” በማለት ጌታን እንዴት እንዳገኙ ወ/ሮ ተዋበች ነገሩን ። በዚህም “በውኑ ለእግዚአብሄር የሚሳነው አለን” ተብሎ በእግዚአብሄር ቃል እንደተጻፈ እግዚአብሄር ከመረጠ ምንም ነገር እንደማያግደው እናስተውላለን ። ጌታን ከተቀበሉ በኋላ ነገሮች ሁሉ አልጋ በአልጋ አልሆኑም ።...

ወደ ገጽ5 ዞሯል

# ወጣቱና ፖርኖ

ከገጽ 2 የቀጠለ

ታዲያ ከፖርኖግራፊው ማዕድ ሲነሱ እነርሱም ሊተገብሩት ይነሳሉ። እንደ ስነልቦና ባለሙያዎች አገላለጽ ከሆነ እንዲህ ያለው ድርጊት ሌላ የትዳር ሳንካ ይፈጥራል ተብሎ ይታሰባል ። ባልና ሚስቱ የፖርኖውን ምስል ተግባራዊ በሚያደርጉበት ወቅት ወደ ስነልቦናቸው ክፍል የሚመጣባቸው የፖርኖግራፊው ትዕይንት በመሆኑ የስሜት እርካታቸው በትዳር አጋሮቻቸው ሳይሆን በፖርኖግራፊው ምስል ተዋንያን ላይ ይሆናል ። ከዚህ መረዳት የሚቻለው የረቀቀ አመንዝራነት በፖርኖግራፊ ውስጥ በጥበብ እንደተቀመጠ ሊጤን ይገባዋል ። የትዳር ተጣማሪዎች ባልናሚስት እርስ በርሳቸው ሳይሆን በስሜት የሚረካኩት በፖርኖግራፊው ላይ ባዩት አንስታይ አሊያም ተባእታይ ላይ ነው ።

አንድ ገጠመኝ እስቲ ላውጋችሁ ። በአንድ የክርስቲያኖች የጋራ መድረክ ላይ ተሰብስበን ሳለ በሞቀ ጨዋታችን መካከል አንድ ወንድም እጅ ላይ የምታምር ዘመንኛ ሞባይል አየሁኝ ። ‹ይቅርታ ልየት?› ብዬ ተቀብዬው ሞባይሏን አገላብጬ ካየኋት በኋላ ወደ ሚዲያ ማዕከሏ በመሄድ ያሏትን ፋይሎች ተመለከትኩ ። በሞባይል ውስጥ ከሚገኘው የቪዲዮ ፋይል ውስጥ ለማመን እስኪያቅተኝ ድረስ በርካታ ተንቀሳቃሽ የሩካቤ ስጋ ምስሎች ረድፍ በረድፍ ተቀምጠዋል ። አንድ ሁለት ሶስት እያልኩ ተመለከትኳቸው ። ሁሉም የቪዲዮ ምስሎች መልክ ያጡ እንቶፈንቶ የሆኑ ጸያፍ የፖርኖግራፊ ምስሎች ነበሩ ። ይህንን ጉዳይ ለሞባይሉ ባለቤት ለአቶ እገሌ ባዋየው ሳቅ ሳቅ አለብኝ ። ምነው አስደነቀህ እንዴ ? ከኢንተርኔት ላይ ነው እኮ የገለበጥኩት ። ብሎኝ እርፍ አለ ። ይህ ወጣት በአንድ የክርስቲያን ግብረሰናይ ድርጅት ውስጥ በሃላፊነት ላይ ተቀምጦ ይሠራል ። በርካታ እርሱን መሰል ወጣቶች የሚሠሩበት ድርጅት ተጠቃሚዎች ናቸው ። እነዚህ የድርጅቱ ተጠቃሚዎች እርሱ ዘንድ ዘወትር የሚመጡት አንዳች መፍትሄ ፍለጋ እንደሆነ ልብ ሊባል ይገባዋል ። ይህ ወጣት ፖርኖግራፊን እንዲህ በገሃድ ከተጠቀመ በምን መንገድ መልካም ነገር ከእርሱ ዘንድ ሊፈልቅ ይችላል ? ይህ ወጣት ከቆይታ በኋላ ፖርኖግራፊን በሚሠራበት ግብረሠናይ ድርጅት ውስጥ እንደ ኮር ቫልዩ (core value) ሳያስተዋውቅ አይቀርም የሚል ብርቱ ፍርሃት አለኝ ።

ለመሆኑ መጽሐፍ ቅዱስ ስለፖርኖግራፊ ምን ይለን ይሆን ? በእርግጥ ስለፖርኖግራፊ መጽሐፍ ቅዱስ ላይ በግላጭ የተጻፈ ቃል ባይገኝም በሌላኛው የትርጉም አቀጣጫው (Circuitously) ግን ፖርኖግራፊ ስህተትና ሐጢአት እንደሆነ ለአንባቢው ያስተዋውቃል ። አንዳንድ ጸሐፍት ግን አረ በፍጹም ... በግላጭ ይናገራል እንጂ› ሲሉ በሐተታ ጽሁፋቸው ይሞግታሉ ። እኔ ግን መጽሐፍ ቅዱስ በተጻፈበት ዘመን መች ፖርኖግራፊ ነበር ብዬ እሞግታለሁ ። እነርሱ ግን ‹ኸረ አለማወቅ› ይሉኛል ። ከፈለግህ ታሪክ አጥና ፤ ፖርኖግራፊ ጅማሬው ዛሬ አይደለም ። ሮም ተብላ በምትጠራው ጥንታዊቷ የሥልጣኔ አድባር ኔፕልስ ከተማ ውስጥ ታላቅ የስብሰባ አድባራት ውስጥ በድንጋይና በእንጨት የተቀረጹ ምስሎ- መዝናኛ / entertainment / ያገለግሉ ነበር ። ብለው ይሞግቱኛል ። በዚህ ሃሳባቸው እጄን ሰጥቻለሁ ። ለምን መሰላችሁ የፖርኖግራፊን ኢ- ስነምግባራዊነት አስመልክቶ ራሱ መጽሐፍ ቅዱስ ግል መልእክት እንዳለው ራሴ ወደመረዳት በመድረሴ...!

ስለ ፖርኖግራፊ አስመልክቶ በአዲስ ኪዳን ክፍሎች ውስጥ በሁለት ሥፍራ በአሉታዊ ጎኑ በጨረፍታ እንዲህ ተብሎ ተጽፏል ፦ ቀጥሎም ኢየሱስ እንዲህ አለ <u>አታመንዝር እንደተባለ ሰምታችኋል ፤እኔ ግን እንዲህ እላችኋለሁ ሴትን ተመልክቶ የተመኛት ሁሉ ያን ጊዜ በልቡ ከእርሷ ጋር እንዳመነዘረ ይቆጠራል ።</u> (ማቴ 5 ፡27) በአንድ ሃሳብ ላይ የመልእክቱ ይዘት ያተኩራል ። ያም ሃሳብ ሴትን ( ወንድን ) ስለመመልከትና ስለሚመጣው የስነምግባር <u>ዝቅጠት</u> ነው ። ይህ ተቃራኒ ጾታን ስለመመልከት በተነሳው የክርስቶስ አስተምህሮ በርካታ ጥያቄዎች በበርካታ ወጣቶች ዘንድ እስከዛሬ ድረስ ይጠየቃሉ ። ‹‹ መመልከት ምን ጣጣ አለው ? ዋናው ተግባሩ ነው እንጂ ›› በሚለው ሃሳብ ። ጥያቄው ያለው በወጣቶች ዘንድ ብቻ ሳይሆን በአዋቂዎችም ዘንድ ነው ። መመልከት ምን ጣጣ አለው ? የሚል ጥያቄ ያቀርባሉ። አንባቢ ሆይ መልሱ ምን ይመስልሃል?

መልሱ እንደ እኔ ፦ አለውም የለውምም የሚል ነው ። የለውም ብለን ስንናገር እንዲህ ነው ፦ ላጤ ሆነህ ሳለ አንዲት ጉብል ጸጉሯ ወርዶ ወርዶ ከትከሻዋ በላይ ያልሆነ ዳሩ ግን ተንዘርግጎ ወደ ታች ጣል ያለ እንዲሁም ቁመቷ እንደ ሐመሮች ዘንግ የዘለገ መልከ መልካም ልጅ አቧራ በነሳው አዲስ አስፋልት ላይ ብቻህን ሆነህ ከእርሷ ጋር በጉዞ ስትተላለፋት ልብህ ድንጋጤ ሞልቶት አዕምሮህ ምህዋሩን ለቆ ባለማስተዋል መንፈስ ተመትቶ ‹‹ ምነው እግዜር ልክ እንደዚህ ያለችውን አይነት ቆንጆ ቢሰጠኝ ›› ብለህ ብትመኝ የሐጢአትነቱ ዋጋ ባዶ ነው ። ዳሩ ግን ይህችኑ ቆንጆ ወጣት ‹‹ ምናለ ለሰከንድ እንኳን ገላዋን በነካሁ ፤ ድምጽዋን በሰማሁ ›› እያልክ ከተመኘህ የኃጢአትነቱ ዋጋ ምሉዕ ነው ። →

"ይህ ሰው በልቡ አመነዘረ" ብትባል ሚስጢሩ ያኔ ነው ። ማንም ሰው የማንንም ቆንጆ/ የትዳር አጋር ተነስቶ በእይታ ግልብ ስሜት በመነሳሳት በምኞት ፈረስ መጋለብ አይችልም።

ክርስቲያኖች ላለመስከርና
የጌታን መንፈስ ላለማሳዘን ከሚያሰክር መጠጥ
እንኳ ይርቃሉ ።ከፖርኖግራፊማ እንዴት?
የፖርኖግራፊ ምልከታ ጎጂ ባህርያት በብዙ
የሚገለጹ ቢሆኑም ጥቂቶቹን እንመልከት

-ለአመንዝራነት ይገፋፋል
-ሃይለኛ ሱስ ያስይዛል
- ትዳርን ያናጋል
- ለእጮኝነት ታማኝ አለመሆን ያመጣል
- በምኞት የተሞላ አይንና ልብ ይኖራል
- የበታችነትና የኃጢአተኛነት ስሜት ያመጣል
-ተስፋ የመቁረጥ ስሜት ይፈጥራል
-አላስፈላጊ ልምምድ ውስጥ ያስገባል
-በስሜት ሱስ ሰውነትን ይጉዳል
-ከእግዚአብሄር ሃሳብ ያርቃል
ለእግዚአብሄር ፍርድ ይዳርጋል
-ለበሽታ ያጋልጣል
-ለወንጀል ይዳርጋል

ፖርኖግራፊን በመመልከት መሳብ አለ፣ከዚያም
መላመድ፣ ከዚያም ሊወጡ በማይችሉበት
የኃጢአት ሱስ መያዝን ይመጣል።
ስለዚህ ከፖርኖግራፊ ምልከታ መሸሽ ይገባል።

የቅዱስ መጽሐፍ ህግና የህዝብ የጋርዮሽ ሕግ ለዚህ ቅንጣት እድል አይሰጡምና ። ለፖርኖግራፊ ሱሰኞች ይህ ሕግ እንቅፋት ነው ። የእርቃን ምስልን መመልከት ይችላሉ ። ለምስሉ ግላዊ ትርጓሜ ይሰጡ ዘንድ ልባቸው ቢፈቅድ ግን ከአመንዛሪነት አይለዩም ። በምስል ላይ የሚያዩት የሩካቤ ስጋ ግንኙነት ሃሳች ስለሆነ የሃሳችነት መንፈስ በልባቸው ገብቶ ይነግሳል ። ኂላ እየዋለ እያደረ የፖርኖግራፊን ተአምራት ማየት ይጀምራሉ ። የመጀመርያው ተአምራት በምስሉ ላይ ያሉትን ትዕይንት ተግባራዊ እንዲያደርጉ የዚህ ዓለም ገዢ ልባቸውን ድፍረት ይሞላል ። የዚያን ጊዜ ማንም ተነስቶ ሊያስጥላቸው አይችልም ። ለወኔአቸው ወደር የለውምና ። ቀድመው ያዩት የፖርኖግራፊ ምስል ከስነልቦናቸው የውስጠኛ ክፍል በኖ እስኪጠፋ ድረስ... ።የሚጠፋ ግን አይመስለኝም ። ምክንያቱም ያዩትን ምናባዊ ምስል ( ተንቀሳቃሽ አሊያም ደረቅ ሊሆን ይችላል ) ሊተገብሩት ሲነሱ ትግበራው ልክ አልመጣ ይላቸዋል ።

ከመሰናበታችን በፊት አንድ የፖርኖ ገጠመኝ ላጫውታችሁ ። ድሮ ልጆች እያለን እኛ ሰፈር አንድ ፊልም ቤት ነበር ። በእዛ ፊልም ቤት ዘወትር የፊልም ፕሮግራም አለ ። በየእለቱ ከሃምሳ እስከ ስድሳ የሚሆኑ ልጆች ወጣቶች ጎልማሶች ብሎም ጡረተኛ አዛውንቶች ፊልም ያያሉ ። አዳራሹ ሰፊ ነው ። ይህ ያልኳችሁ የተመልካች ቁጥር እጅግ ዝቅተኛ ስለነበር ለአዳራሹ ምኑም አይደለም ። ተመልካቹ እንደ ባህረ ጠብታ ያህል ስለሆነ የፊልም ቤቱ ባለቤቶች ብዙም ደስታ አይሰማቸውም ነበር ። ከሳምንቱ አንዱ የፊልም ፕሮግራም ቀን ግን አንጀታቸውን ያርስላቸዋል ። ያ ቀን እሁድ ነው ። ለየት ያለ የፊልም ቀን። ያን የፊልም ቀን ለየት የሚያደርገው የፖርኖ ቪዲዮ ቀን በመሆኑ ነው።

እርቃነ ሥጋቸውን የሆኑ የፈረንሳይ ተባእታይና እንስታይ በግላጭ ግብረሥጋ ግንኙነት ያደርጋሉ ። አዳራሹ ጸጥ ይላል ። ተደራሲያኑ ( ተመልካቾቹ ) የአንዳቸውም ትንፋሽ አይሰማም ። ድባቡ የተፈታ ከተማን ይመስላል ። በፖርኖግራፊ ተንቀሳቃሽ ምስል ልባቸው እንደተሰቀለ የእለቱ ፊልም ያበቃል ። ሁሉም ተመልካቾች ታዲያ የዚያን ዕለት ወደየቤቶቻቸው ( ከልጆች በስተቀር ) አይሄዱም ። ሁሉም በፊናው በፖርኖግራፊ አስተምሮ መሠረት የመስክ ልምምድ ለማድረግ ይወጣሉ ። አሁን ብዙዎች በሕይወት የሉም ። በኤች አይቪ ተበልተዋል ። ገሚሶቹ ደግሞ በአባላዘር በሽታዎች ክፉኛ ተጎድተው በስቃይ እመኝታቸው ላይ ይገኛሉ ። አንዳንዶች ዛሬም አሉ ። የፖርኖግራፊን የቤት ሥራ ዛሬም በመስራት ላይ ፣...።

ያኔ በመንደር ፊልም ቤቶች የተጀመሩት የፖርኖግራፊ ግብዓቶች ዛሬ በማንኛውም ኢትዮጵያዊ እጅ በዲጂታል ማጫወቻዎች አማካኝነት ይገኛሉ ። የፊልም አከራይ ቤቶች እንኳን የራሳቸው የሆነ የፕሮሞሽን ስታይል አላቸው ። በሰው ለሰው የመግባባት ዘዴ ደንበኞቻቸውን ይስባሉ ። በቅርብ ቀን አንዲት የፊልም ደንበኛዬ ወደፊልም ማዕከሏ ጎራ አልኩኝ እንደደረስኩም ‹‹ አንተ ግን ኢሮቲክ ፊልም አይጥምህም እንዴ? ላለፉት አራት ዓመታት የተከራየኸኝ ፊልም የሼባ ብጤ ናቸው ›› ። ያለችኝን አስታውሳለሁ ። ይህች ሴት ክርስቲያን እንደሆንኩ በሚገባ ታውቃለች ። ለአጽንኦት ያህል ባስታውሳትም የሰጠችኝ መልስ ‹‹ምን ጣጣ አለው?›› የሚል ነበር ።

ፖርኖግራፊ አሁን እኛ ሃገር በርክቷል ። ቤተክርስቲያንም ጭምር ። በዚህ ጽሁፍ ሊገለጹ ያልተወደዱ በርካታ ሳንካዎች አሉበት ። ነፍስንና ሥጋን አንቆ የመያዝ ልዩ ሃይል አለው ። በርካታ ቅዱሳን በዛሬ ዘመን ‹‹ተይዘውበታል›› ‹‹ሃይ›› ብትሏቸው አይሰሙም ። ልባቸው ደንድኗል ። እንደዚህ ላሉቱ መፍትሄው ቤተክርስቲያን ናት ። ፍቅርና ጥበብ በሞላበት መልኩ ከእንደዚህ አይነቱ እስራት የሚወጡበትን መንገድ ማመቻቸት ይገባታል ። በርካታ ‹ቅዱሳን› የዚህ ሱሰኝነት እንዳለባቸው ከላይ ከመግቢያችን ከአንዲት እህትን ተመልክተናል ። እርሷ በድፍረት ችግሯን በመግለጽ መስዋዕት ለመሆን በአደባባይ አውጥታ ተናግራለች ። ይህም ጽሁፍ ለጠቋሚነት ተጻፈ ። በቆላስይስ 3፡5 ላይ ያለው የሐዋርያው ጳውሎስ መልዕክት ደግሞ ለማጠንከሪያነት ።

"ስለዚህ **በእናንተ የሚገኙትን የምድራዊ ሕይወት ምኞቶች ሁሉ ግደሉ ፤ እነርሱም ዝሙት፣ ርኩሰት ፣ ፍትወት ፣... ናቸው"** ።

## እግዚአብሄርን መፍራት

ከገጽ 1 የቀጠለ

እግዚአብሄርን ስለ መፍራት ስናስብ እግዚአብሄርን መፍራት ማለት ምንድነው ? የሚል ጥያቄ ሳንጠይቅ አንቀርም ። እግዚአብሄርን መፍራት ማለት የእግዚአብሄርን ባለሥልጣንነት መቀበል ማለት ነው ። ሁሉን የሚችል ከሥልጣናት ሁሉ በላይ ሥልጣን ያለው ሊፈራ የሚገባው እግዚአብሄር ነው። ምክንያቱም ሥልጣኑ ወሰንና ገደብ ስለሌለው ነው ። የመንግስታትና የሀገር ገዢዎች ሥልጣን በሕገ መንግሥታቸው ክልል ውስጥ ነው ። የእግዚአብሄር ሥልጣን ግን ወደርና ርዝመት ስፋትና ጥልቀት የለውም ፤ ይህ ነውም ተብሎ አይነገርም ።

እግዚአብሄርን መፍራት ማለት ለእኔና ለእናንተ እርሱን በመፍራት መመላለስ ማለት ነው ። እግዚአብሄር ሁልጊዜ ፤ የሚመለከተን፤የማያንቀላፋ የምንሠራውን የምናደርገውን የምናከነውን ነገር ሁሉ በተገለጹ አይኖቹ የሚያይ አምላክ ነው ። እግዚአብሄር እንደሚያይ ካወቅን ፍርሃ እግዚአብሄር በውስጣችን ያድራል ነው ።

ሕዝብ እግዚአብሄርን በሚፈራበት ጊዜ በጽድቅ መመላለስ ይጀምራል ። በዚያን ጊዜ የእግዚአብሄር ባርኮት በሐገር ላይ ይሆናል ። እግዚአብሄርን የሚፈሩ መሪዎች በሥፍራ ላይ ሲቀመጡ ምድር ትባረካለች ። ሰላምና በረከት ይሆናል ። ነገር ግን እግዚአብሄርን ስለመፍራት አንድ ነገር ለማለት እፈልጋለሁ ይኸውም እግዚአብሄርን እንፍራው ስንል ምን ማለታችን ነው ? ያስፈራል ስንልስ ምን ማለታችን ነው ? ብዙ የሚያስፈሩን ነገሮች አሉ። ብዙ የምንፈራቸው ነገሮች አሉ ። እግዚያብሄርን መፍራት ማለት በልጅነታችን አንድ ነገር አናደርግም ካልን ወላጆቻችን እኛን እንደሚያስፈራሩበት አነዚያ የጭራቅ ታሪኮች ሁኔታ አይደለም ። እግዚአብሄር እንደዛ አይነት አምላክ ስለሆነ አይደለም ። እግዚአብሄር የሚፈራው ስለ ልዕልናው ፤ስለታላቅነቱ፤ ስለክብሩ ማቋረጫ ስለሌለው ወሰን ስለማይገኝለት ታላቅነቱ ነው ። ፍሩኝ ብሎ እግዚአብሄር ስለሚያስፈራራን አይደለም የምንፈራው ። ነገር ግን የእግዚአብር ፍርሃት ሰዎች ውስጥ የሚገባው የእግዚአብሄር ፍቅር ቀድሞ ሲገባባቸው ነው ። አለዚያ እንደ ሰው እልከኛ ፍጡር የለም ። ነገር ግን የእግዚአብሄር ፍቅር በውስጣችን በሚገባበት ጊዜ እግዚአብሄርን እንደ አባት እንፈራዋለን ።

እግዚአብሄር ሊፈራ የሚገባው አምላክ ነው። ይህ ሆኖ ሳለ ታዲያ ሰዎች ለምን እግዚአብሄርን አይፈሩትም ብለን መጀመርያ እንጠይቅ። በሁለተኛ ደረጃ ደግሞ እግዚአብሄርን በመፍራት የምናተርፋቸውን በረከቶች እንመለከታለን ፡-

**ለምንድነው ሰዎች እግዚአብሄርን የማይፈሩት/**

**1ኛ፡- ስለ እግዚአብሄር እውቀት ስለሌላቸው ነው ።**

ማንነቱን ስለማያውቁ እግዚአብሄርን አይፈሩትም ። እግዚአብሄርን ማንነቱን ባወቅነው ቁጥር እንፈራዋለን ። ምናልባት ሰዎችን ባወቅናቸው ቁጥር ድካማቸውንም ስለምናውቅ ፍርሃታችን እየጠፋ ሊሄድ ይችላል ። እኩል የሆንን እንደሆንን ሊሰማን ይችላል ። እግዚአብሄርን ግን ባወቅነው ቁጥር ልዩ የሆነው ክብሩ ጸዳሉ ታላቅነቱና ልዕልናው እየበዛ ስለሚሄድ ከትላንት ዛሬ፤ ከዛሬ ደግሞ ነገ ፤ ከነገ ደግሞ የዛሬ ዓመት በጣም እንፈራዋለን ። እግዚአብሄርን ባወቅነው ቁጥር ፍርሃት ነው በውስጣችን የሚመጣው ። ካሰብነው በላይ ከጠበቅነው በላይ ነው እግዚአብሄር ።

... ወደ ገጽ 9 ዞሯል

## እንደጥበበኞች ...

ከገጽ 1የቀጠለ

... ከምዕራፍ 4-6 ያለው ደግሞ እኛ ለእግዚአብሄር ልንኖር የሚገባውን ሕይወት ያሳየናል ፡፡ ክርስትና በሕይወታችን ሙሉ የሚሆነው እንደዚህ ሲሆን ነው ፡፡ ይሄ ሁለት ነገር በሕይወታችን ውስጥ ሲገባ ነው ፡፡ እግዚአብሄር በክርስቶስ በእኛ ሕይወት ውስጥ ምን እንደሠራ፣ በክርስቶስ ያገኘነው የሕይወት ክብርና ብልጽግና ምን እንደሚመስል ስናይ እና ከዚያ በኋላ ደግሞ በክርስቶስ የዳንን ሰዎች በክርስቶስ ሕይወት ያገኘን ሰዎች ለተጠራንበት ሕይወት እንደሚገባ ስንመላለስ የክርስትና በሕይወታችን ሙሉ ይሆናል ፡፡ ዛሬ ያለን ሰዎች አንዳንዶቻችን እግዚአብሄር በጸጋው በሠራው ሥራ ላይ ልባችን አርፎ እርሱ በጣም ገብቶን ሳለ የመመላለስ ፤የኑሮና የሕይወት ጉዳይ ላይ ጥያቄዎች አሉብን ፡፡
ሌሎች ሰዎች ደግሞ ኑሮአቸውን ለማሳመር



እነዚህ ሶስቱ ጠቢባን ( ሰብአ ሰገል) ወደ ዓለም የመጣው (የተወለደውን) የአይሁድ ንጉስ ክርስቶስ ኢየሱስን ለመገናኘት ተጓዙ፡፡ ከእነርሱ ተግባር ሦስት ነገሮች እናስተውላለን ፦
1ኛ ዘመኑን ይመረምሩ ነበር ፡፡
2ኛ በሚመራቸው (ኮከብ) እየተመሩ በጥንቃቄ ይጓዙ ነበር፡፡
3ኛ የእግዚአብሄርን ፈቃድ ( በህልም ) እየተረዱ ይጓዙ ነበር ፡፡ በአጠቃላይ በጥበባቸው <u>ዘመኑን ዋጅተውት</u> ነበር ፡፡

ጥረት ያደርጋሉ አካሄዳቸውን ለማሳመር ጥረት ያደርጋሉ ነገር ግን በጸጋው በክርስቶስ እየሱስ የማዳን ሐይል ውስጥ ያለውን ሕይወት ሳይካፈሉ ስለሆነ ድካማቸው ሁሉ ከንቱ ይሆናል ፡፡ ከዚህ ከምእራፍ 4 ጀምሮ ባለው ቃል ላይ ተመላለሱ የሚል ነገር ነው ሐዋርያው ጳውሎስ የሚናገረው ፡፡ መመላለስ የሚለው ቃል ተግባራዊ የሆነውን ሕይወታችንን የሚያሳይ ነገር ነው ፡፡ ክርስትና መመላለስ አለው ፣ ተግባር አለው ፡፡ በኑሮና በሕይወት የሚገለጽ ነገር ነው ፡፡ የክርስትና ሕይወታችን፤ በክርስቶስ የዳነው ማንነታችን በኑሮአችን ውስጥ እየተገለጠ ጌታ ክርስቶስ እየሱስ የሚያሳይ ካልሆነ በስተቀር እምነታችን ምናልባት የሞተ ይሆናል ፡፡

ታዲያ ሐዋርያው እነዚህ የዳኑ; በጌታ የከበሩ ሰዎች ያንን የዳነ ሕይወታቸው በዚህ ጨለማ በሆነው ዓለም ውስጥ እግዚአብሄር አምላክን እያስከበረ እንዲገለጥና እንዲመላለሱ ሲናገራቸው እንመለከታለን ፡፡ ከዚህ ምልልስ መካከል አንደኛው እንደጥበበኞች መመላለስ ነው ፡፡ መጽሐፍ ቅዱሳችን በዚህ ቦታ ላይ በግልጽ እንደጥበበኞች ተመላለሱ ይለናል ፡፡ በመንፈሳዊው ዓለም ጥበበኝነት አለ ፡፡ በመንፈሳዊው ዓለም ደግሞ ሞኝነት አለ ፡፡ በዚህ በነባራዊው ዓለም ውስጥ ጥበብ ነው የምንለው ነገርና ሞኝነት ነው የምንለው ነገር እንዳለ ሁሉ በመንፈሳዊው ዓለም ውስጥ ደግሞ ከእግዚአብሄር ጋራ ስንመላለስ ሞኝነት የሆነ ኪሳራ ያለው የሚጎዳ ሕይወት አለ ፤ ደግሞ እግዚአብሄር የሚከብርበት ጥበብ የተባለ ሕይወት አለ ፡፡

መጽሐፍ ቅዱሳችን ስለጥበብ ሲናገር የጥበብ መጀመርያ እግዚአብሄርን መፍራት ነው ይላል ፡፡ እግዚአብሄር ጠቢብ ነው አዋቂ ነው አንድን ሰው፤ የሚለው ያ ሰው እግዚአብሄርን በመፍራት የሚመላለስ ከሆነ ነው ፡፡ ሐዋርያው የሞኝነት ና የኪሳራ ሕይወትን ከጥበበኝነትና ከማስተዋል ሕይወት ጋር እያወዳደረ በጥበብ እንድንመላለስ ይመክራል ፡፡ ለመሆኑ በጥበብ መመላለስ ምንድነው? ወይም ጥበበኞችስ እንዴት ይመላለሳሉ? ስንል በጥበብ የመመላለስ ሕይወት መገለጫውን አራት ነገሮች ያስቀምጥልናል ፡፡ እነዚህ አራት ነገሮች ምን እንደሆኑ እንመልከት ፦

1ኛ) የመጀመርያው በጥበብ የመመላለስ የሕይወት መገለጫው ወይም ጥበበኞች እንዴት ይመላለሳሉ? ስንል መልሱ <u>በጥንቃቄ ይመላለሳሉ የሚል ነው</u> ፡፡

የእግዚአብሄር ቃል እንደዚህ ይላል፦ “እንደጥበበኞች አንጂ ጥበብ እንደሌላቸው ሳይሆን እንዴት እንደምትመላለሱ በጥንቃቄ ተጠበቁ ”(ኤፌ5፡15) ብሎ ይናገራል ፡፡ በብዙ ነገራችን ግዴለሾች እየሆንን ያለንበት ጊዜ ቢኖር ይሄ ጊዜ ነው ፡፡ በክርስትና ሕይወታቸው የቆዩ ሰዎች ድሮ ያደርጉት የነበረውን ጥንቃቄ እየተው እንደነገሩ መመላለስ የጀመሩበት ጊዜ ቢኖር ይሄ ጊዜ ነው ፡፡ ከጌታ የተቀበልነው የከበረ ሕይወት ፣ የዳንንበት ዘላለማዊ ሕይወት፤ የክርስቶስ ደም የተከፈለበት ሕይወት ጥንቃቄ ይፈልጋል ፡፡ መዳን አንድ ነገር ነው ፡ ያገኘነውን ጸጋና የዳንንበትን ድንነት መጠበቅና ወደ እግዚአብሄር መንግስት እስክንደርስ ድረስ በጥንቃቄ መመላለስ ሁለተኛ ነገር ነው ፡፡ አንድ የእግዚአብሄር ሰው ሲጽፉ ምን አሉ፦ *‹‹እስከ መንግስተ ሰማያት በር ድረስ ወደ ገሃነም የሚወስዱ መንገዶች አሉ››*

አንዳንዶቻችን ዳንን የውሃ ጥምቀት ወሰድን ጌታን ተቀበልን ከዚያ በኋላ ግን እግዚአብሄር በምንም ሊተመን የማይችለውን በውስጣችን ያስቀመጠውን ሕይወታችንን አንጠነቀቅለትም፡፡ የጥንቃቄ ጉድለት በሕይወታችን ውስጥ ብዙ ችግሮች ያመጣል ፡፡ እንዲያውም በአሁን ጊዜ በብዙ ሰዎች ሕይወት ውስጥ ያሉ ችግሮች መነሻቸው (ዲያቢሎስ የችግር መነሻ እንደሚሆን አውቃለሁ) የጥንቃቄ ጉድለት ሆኖ ታያላችሁ ፡፡ አገልጋዮች በአገልግሎታቸው የማይቀጥሉበት ፣የተመሠረቱ ትዳሮች በዚያው እውነተኛ ፍቅር የማይቀጥሉበት፤ የጀመርነው የክርስትና ሕይወት ዳር ሳይደርስ መንገድ ላይ የምንጠባጠብበት ምክንያት የተቀበልነው ከእግዚአብሄር ያገኘነው ህይወት ጥንቃቄ እንደሚጠይቅ ካለማወቃችን የተነሳ ነው፡፡ መጽሐፍ ቅዱሳችን ከጥንቃቄ ጉድለት የተነሳ ብዙ ውድቀት ውስጥ የገቡ ሰዎችን ያሳየናል ፡፡ በጥንቃቄ ደግሞ ነገራቸውን ጠብቀው እግዚአብሄር ወዳለው ቦታ ደርሰው የእግዚአብሄርን ክብር ያዩና የእግዚአብሄርን ሃሳብ ያገለገሉ ሰዎች እንዳሉ እንመለከታለን ፡፡

....ወደ ገጽ 6 ዞሯል

## ፊሉ ይናገር

ከገጽ 3 የቀጠለ

ከገዛ ልጆቻቸው ጀምሮ ወዳጅ ዘመድ ጎረቤት የአካባቢ ማህበረሰብ በሙሉ በእነርሱ ላይ ትልቅ ተቃውሞ አስነሱባቸው ፡፡ የተለያዩ ሁኔታዎችን በማንሳት ተቃውሞአቸውን ከመግለጽ ባለፈ ተጠምቀው ወደ እነርሱ ወይም ወደቀደመው እምነታቸው እንዲመለሱ ያለማሰለስ ያስጨንቁአቸው ገቡ ፡፡ የእነርሱ ምላሽ ግን የተገለጠልንን እውነት ትተን ወደ ቀደመው አንመለስም; የእግዚአብሄርን ልጅ እየሱስን እናመልካለን የሚል ነበር ፡፡ በዚህ መካከልም ከአካባቢው ሰዎች አንዳንድ ጌታን መቀበል ጀመሩ ፡፡ በእነርሱም ቤትም ከተለያዩ አካባቢዎች በሚመጡ አገልጋዮች መገልገልና ጌታን ማምለካቸውን ቀጠሉ ፡፡ ሰዎች ወደ ጌታ መምጣታቸው በእጅጉ ያስቆጣቸውና እንዲሁም በእምነታቸው መጽናታቸውን የተመለከቱት የአካባቢው ሰዎች ሌላ ደባ ከበስተኋላ በመጠንሰስ እነርሱን የሚጥሉበትን ወጥመድ ያዘጋጁ ጀመር ፡፡ እነርሱ ግን ጌታን ማምለካቸውን ቀጠሉ ፡፡

ወ/ሮ ተዋበች እንዲህ ይላሉ ፦ “”አሁን ተያ ወዲህ እሳቸው እየሄዱ ይመሰክራሉ ፡፡ ሰው ወደጌታ ያመጣሉ ፡፡ በአንድነት እናመልካለን ፡፡ መምህሬ ደስታ የሚባል የአካባቢው ቄስ እኛ ጋ መጣ ፡፡ መቅደስ መሄድ አቆመ፡፡ እኔ የበየነን አምላክ ነው የማመልከው፤ሌላውን ትቻለሁ አለ ፡፡ እስከዛሬም ለሠራሁትም ሥራ ለበላሁት ለጠጣሁት ይቅር ይበለኝ ፡፡ እንግዲህ ከእናንተ ተለይቻለሁ አለ ያ ቄስ ፡፡ያንጊዜ ባለቤቴን እንግዲህ አሉ *“መምሬ ደስታ የመሰለ ታቦታችንን ወደ አንተ አመጣህ፣ እስልመሃል እስልምና አደረክብን ፡፡ እንግድህ ከአገሩ ሂድልን ወይም ተውልን* “ አሉአቸው ፡፡ “አልተውም” አለ ፡፡ “እንግዲያው ልንገድልህ ነው ፡፡ ከብትህም መዘረፉ ነው”አሉ፡፡ “ውሰዱ” ፡፡ “አንተንም መግደላችን ነው ፡፡ ሴቱም እየበረረ አንተ ጋ ይመጣል፤ ወንዱም በርሮ አንተ ጋ ቄሱም በርሮ አንተ ጋ ይመጣል ሃገራችንን ልታሰልማት አይደለም ወይ ፡፡ ተመለስ አለበለዚያ ጠብቅ” አሉት “እሺ እጠብቃለሁ ጆርባዬም ይኸው አንገቴም ይኸው ጌታ እንደተወጋልኝ እወጋለሁ እንደተገረፈልኝ እገረፋለሁ ወደ እናንተ አልመለስም” አሉ ፣ቆረጡ ፡፡ እኔ ልጃቸውን ጠራሁና አረ እንዲህ ብለው ቆርጠዋል ፡ አረ እንዲያው እስቲ ዞር ይበሉ አልኩ ፡፡ ልጃቸውም አባባ እንሂድ! አላቸው ፡፡ እኔ አልሄድም አሉ ፡፡ እግዚአብሄር አልፈቀደም አልሄድም አሉ ፡፡ አንድ ቀን ማታ ቃሉን ያስጠኑአቸው የነበሩ ሰዎች መጡ ፡ ከእኛ ጋራ ሊያመልኩ መጡ ፡፡ ያው አምልኮንም መዝሙርንም ቃሉንም ጨረስንና እህል ልንበላ ስንል በመስኮት በኩል አፈሙዙን ብቅ አድርገው ጠመንጃውን ተኮሱብን ፡፡ ፣እኔ መስኮቱ ስር ነበርኩ፡፡ በራሴ ይሂድ በእግሬ ይሂድ አላውቅም፡፡ እኛን አልፈው ባለቤቴ ላይ ድርግም አደረጉባቸው ፡፡ከዚያ ሰው ሁሉ ግልብጥ አለና ወጥቶ ሄደ ፡፡ ቤታችን ረጅም ነው ፡ ሳር ቤት ነው፤ ፎቅ ነው ፡፡ አራቱንም ቤታችን አንዴ እሳት ለኮሱት፡፡ አቃጠሉት ፡፡

ባለቤቴ አልሞቱም ነበር፤ ትንፋሻቸው ነበር ፡፡ ሰው ሁሉ ወጥቷል፡፡ማንም የለም! ፡፡ ብቅ ብዬ ሳይ ሁለት ሰዎች ደጅ ድምጽ ያሰማሉ ፡፡

ደረጃ ( አስመላኪያችን ) እና አንድ ሌላ ሰው ናቸው ፡፡ ወደቤት ገብተው እርሳቸውን በብርድልብስ ጥቅልል አደረጉና አንጠልጥለው ውድማው ላይ አጋድመዋቸው ሄዱ ፡፡
በኋላ ባለቤቴ እኔን ጠርተው ተዋቡ ትሽሺ ይሆን? አሉ ፡፡ እኔ አልሸሽም; እርሶ ስትሞቱ እኔ ልሸሽ ኖሯል? በእግዚአብሄር ቃል የተያያዝነው እንግዲህ አንድ ጋ ነው ፡ አልኩ ፡፡ በይ ነይ ደግፊኝ አሉኝ ፡፡
ደገፍ ሳደርጋቸው " እንግዲህ ጠንክሪ እንዳትመለሺ ጠንክሪ " ብለው ግጥም አሉ ፡፡ ሞቱ ፡፡ ደረጃና ውድነህ ጥይቱ አላስኬድ ብሏቸው ውድማው ስር ድብቅ ብለው ነበር ፡፡ ‹‹እማማ ተጨረሱ?›› አሉኝ ፡፡ አዎን አልኩኝ ፡፡ አስከሬኑን በቅጡ በቅጡ አደረኩ፡፡ ውረዱና ለልጃችን አባትህ ተበጅቷልና ሬሳህን ቅበር በሉና ንገሩልኝ አልኳቸው ፡፡
እነርሱም ሄዱ ፡፡ ጠዋትም ሰዎች ሲመጡ ሲያፌዙብኝ ለነገራቸው ዋጋ ስመልስ ጌታን ተቀብለው "እንደተወጋ እወጋለሁ እንደተሰቀለ እሰቀላለሁ" ብለው ደፍረው ወደ ጌታ በመሄዳቸው ደስ እያለኝ ፤- " ሥጋቸው ቀባሪ ቢያጣም እንኳ ነፍሳቸው ሄዳለች ወደ አምላኳ! " "ሥጋቸው ቀባሪ ቢያጣም እንኳ ነፍሳቸው ሄዳለች ወደ አምላኳ " እያልኩ እየዘመርኩ እደጃቸው ቀብሬ መጣሁ ፡፡ ሁሉ አብረው ቂሶቹ ሃገር ሁሉ አብረው አይደለም እንዴ የገደላቸው ታዲያ እዚያው እደጃቸው ቀብሬ መጣሁ ፡፡ ያው ቀናቸው በዚህ ሆነ፡፡ የእግዚአብሄር ፈቃድ በዚህ ሆነ፡፡"" በማለት ነገሩን ፡፡
በዚያ ወዳጅ ዘመድ በከፋበት ስለእውነት በተገፋባት ምድር ባለቤታቸውን አጥተዋል ፡፡ መኖርያ ቤታቸው ከነሙሉ ንብረታቸው በእሳት ጋይቷል ፡፡ በአይን የሚታይ ተስፋ የሚደረግ ምንም የለም ፡፡ ነገር ግን በልባቸው ያነገሱት እውነት የሆነው እግዚአብሄር ግን ከእርሳቸው ጋር ነበር ፡፡ በዓለም ሳላችሁ መከራ አለባችሁ ነገር ግን አይዟችሁ እኔ አለምን አሸንፌዋለሁ ብሎ እየሱስ ለደቀመዛሙርቱ እንደተናገረ እርሳቸው የተከተሉት ጌታ ልዩና እውነተኛ በመሆኑ ተቃራኒ ሊቃወማቸው ግድ ነበር ፡፡ ወ/ሮ ተዋበች ባለቤታቸውን ከቀበሩ በኋላ ወዴት ሄዱ? የእርሳቸውስ እጣ ፈንታ ምን ይሆን ? እንዲህ በማለት ይቀጥላሉ :-""ባለቤቴ መንዝ የሚኖር ሌላ ልጅ አላቸው ፡፡ መሞታቸውን ሲሰማ መጣና እንሂድ አለኝ ፡፡ ያው ልብስ ንብረት የለም፤ ሁሉ ተቃጥሏል፡፡ አንጠልጥሎኝ ይዞኝ ወደ እርሱ ቤት መጣ ፡፡ የእኔ ልጆች ደግሞ መዘዞ ናቸው ፡፡ አቶ በየነን ገደሉአቸው ሲባል ሲሰሙ ከመዘዞ እርሷን አይናን ሳናያት አንቀርም ብለው እዚያ መንዝ መጡ ፡፡ ቅዳሜ ማታ ገድለዋቸው እሁድ አይደለም የቀበርኳቸው? እሁድ መጡና አደርን፡፡
ሰኞ ጠዋት አንጠለጠሉኝና መዘዞ ገባን ፡፡ እዚያ ልጆቼ ጋ ሰኞ ገባንና ሐሙስ ክርስቲያኖች ሊጠይቁኝ መጡ፡፡ እነ እመቤትና ከለላው መጡ ፡፡ ተላቀስን ፡፡ እንዴት ይሁን? አለች ፡፡ እንዴት ይሻላል ትያለሽ ውሰጂኛ አልኳት ፡፡ ሐሙስ ማታ ነው እንዲህ የተባባልነው ፡፡ተነሱ እንሂድ ! አለችኝ ፡፡ አማቼ ደግሞ ‹‹ትናንትና መጡ፤ ልጆቹን ሳይጠግቧቸው፤ እኛም ሳንጠግባቸው እንዴት ይሄዳሉ? ሳምንት ቅዳሜ ትወስጃቸዋለሽ፤ እስከዚያ ድረስ ምንም አንላቸው አለ ፡፡ ይሁን እንግዲህ አለችና እርሷም ሄደች ፡፡ በማግስቱ አርብ ዘመዶቼ ሰውን አስጠሩና እያስረገዱ

እያስረገዱ እንደሃገራችን እንደዱሮው መጡ ፡፡ እዚያ ተላቀስንና ‹‹ እንዲህ ያለ ቋንቋ አንቺ ዱሮሽ ምን ትችያለሽ? አሁን ቀርበሽ መልኩሰሽ አባትሽ ቤተክርስቲያን እያመለክሽ ትቀመጫለሽ›› እኔ ቆሎ እይዛለሁ፤ እኔ ዳቦ ጠላ እይዛለሁ፤ ነገ ትቀርቢያለሽ አሉ ፡፡ አርብ ነው እንዲህ የሚሉኝ፡፡ ገንዘባችሁን አትጨርሱ እኔ የመመለስ ቋንቋ የለኝም ፡፡ አልኳቸው ፡፡ ለአንዱ ስል አንዱ ፤ለአንዱ ስል አንዱ እንዲያው ግራ ግብት አለኝ፡፡
በኃላ ዝም ስል የግድ ነው የግድ ነው ብለውኝ ሄዱ ፡፡ ሌሊቱን አፌን ልጉም አደረገና እንዲያው ሆዴን ቀጥቀጥ አደረገና ተቀምጥ አመመኝ ፡፡ ማታ ጎረቤት ሁሉ ተሰብስቦ ድምድም ይላል ፡፡ ከዚያ ቀዳሚ ጠዋት አማቼ ‹‹እማማ›› አለኝ እቤት አልኩት፡፡ ደክሞኛል! ፡፡ ‹እንግዲህ ኃጢአቶቶችን ሁሉ ተናገሩና አስፈትቼ አሳምሬ በኖሩበት ሃገር እንድቀብርሁ የንስሃ አባቴን ልጥራ› አለኝ ፡፡ይህን ሲለኝ ችግር አለኝ ፡፡ እንዴ! እኔ ጌታን አምኜ እርሱን ተቋጥሬአለሁ አልኩትኝና እንዲያው እንባዬ ይፈልቅ ጀመር ፡፡ እርሱ ንስሃ አባቱን ሊጠራ ወጣ ሲል ፓስተር አጥሊ ከነወንድሙ ፤ ምንተሺ የሚሉትም ከተፍ እሉ፡፡ እሉ ወጣ ከማለቱ ከተፍ አሉ ፡፡ ምነው እማማ ምነው? ሲሉኝ አሞኛል እባካችሁ አልኩኝ ፡፡ ሊጸልዩልኝ ጎንበስ ሲል ታላቅ እህቴ ኡ ኡ ኡ አለች ፡፡

ከዚያ ‹እማማ› አለኝ ‹አቤት› አልኩት ፡፡ ‹ይበረቱ እንደሆነ መሀል ሜዳ ይገፍዎት ልሂድ?› አለኝ ፡፡ አኤም፡- እንኳን መሐል ሜዳ ከዚህ አውጣኝ እንጂ ወደፈለክበት ስደደኝ አልኩት ፡፡ ይህም ከጌታ ሳለመለየት ነው፡፡ ቂስ ሊጠራ የሄደው ሊያስመልሰኝ ሊያስጥለኝም አይደል? እርሱ ሳይመለስ ያዙኝና መሐል ሜዳ ወሰዱኝ ፡፡ እዚያ መሐል ሜዳ ክርስቲያኗ ሐኪም በሁሉቱም ታፋዬ መርፌ ውግት አርጋኝ፤ ለደረቴ ሹራብ፤ ለእግሬ ሱሪ፤ አበባ የመሰለ ጋቢም አለበሱኝና አስተኙኝ፡፡ ትኝት አልኩ ፡፡ እነርሱ ኮንፍራንሳቸው ሄዱ ፡፡ ደግሞ ሌሊት መጡና ጸልየውልኝ በሳ ሆንኩ፡፡ በሳ ስሆን ያዙኝና ደብረብርሃን እጠሀይ ቤት ወሰዱኝ፡፡ እሷ ቤት አደርኩ ፡፡ በማግስቱ እመቤት ጋ ወሰዱኝ፡፡ እኔም እዚያ ተቀመጥኩ፡፡አሁንም ይኸው ደብረ ብርሃን ከተማ አለሁ፡፡ ቤተክርስቲያኗም ጉዳቱን አይታ እየረዳኝ ይኸው አለሁ ፡፡ እስከዚህ ደረስሁ ፡፡ ይህ ሁሉ ከሆነ አስራ ስድት ዓመት ሆኖታል ፡፡ 15 እህትማማቾች ነበርን ፡፡ ከአስራምስቱ አስራ አራቱ ሙተዋል፡፡ እኔ ግን አለሁ ፡፡ እስከ አሁን አንደበቴም አልላላ ልቤም አልፈራብኝ ፡፡ ጌታ አጠንክሮኛል ፡፡ ስሙ ይባረክ ፡፡ ጌታንም እንደ አቅሜ አገለግላለሁ ፡፡ በጸሎት አገለግሎት አገለግላለሁ ፡፡ አቅምና እድሜ የሰጠኝ እግዚአብሄር ነው ፡፡

ዛሬ ለወጣቶች ለጎልማሶችና ለእናቶች የማስተላልፈው መልዕክት ጌታ ከእሳትም ከሞትም ያወጣልና ኑ ወደ እየሱስ! ጠንክሩ ነው፡፡ ከእግዚአብሄር ሌላ አዳኝ የለም ፡፡ ሌላ ፈዋሽ የለም ፡፡ የሰማይን ሕይወት ለመውረስ ጠንክሩ እላለሁ ፡፡ ከቤተክርስቲያን ደግሞ መበለቶችን አትጣሉ ፡፡ እኛም ጌታ እየሱስን አምነን እናንተ እንድታበረቱን ተጠግተናችኋል ደካሞችን ተንከባከቡ እላለሁ ፡፡" በማለት ወ/ሮ ተዋበች መልዕክታቸውን ያስተላልፋሉ ፡፡

ወ/ሮ ተዋበች በደብረ ብርሃን ሙሉ ወንጌል ቤተክርስቲያን ስር እየተረዱ በአንድ የቤተክርስቲያኒቱ አገልጋይ ቤት አንድ ክፍል

ተሰጥቶአቸው ጌታን እያገለገሉ ይገኛሉ ፡፡ ወ/ሮ ተዋበችን ያስጠጉት እኚህ የእግዚአብሄር ሰው ሲናገሩ፡- "እኚህ እናት ብዙ ፈተናን ያለፉ፤ ደግሞም የእግዚአብሄርን ክንድ ተአምራቱን ያዩ፤ በእምነታቸው ጠንካራ የሆኑ እናት ናቸው ፡፡ እግዚአብሄር አይናቸውን ከእውርነት አብርቷል ፡፡ ከክፉ አድራጊዎች ታድጓቸዋል ፡፡ ከበሽታቸው ፈውሷቸዋል ፤ የዘላለምን ሕይወት ሰጥቷቸዋል ፡፡ በአሁን ሰዓት በቤተክርስቲን በጸሎት ያገለግላሉ ፡፡ ከሥፍራው አይታጡም ፡፡ ከእኛ ጋር ያመልካሉ ፡፡ እርሳቸውን በማስጠጋቴ እኔም እጅግ ደስተኛ ነኝ ፡፡ በረከቴ ናቸው፡፡" ብለዋል፡፡ መጽሐፍ ቅዱስ ከስልሳ ዓመት በላይ የሆኑትን መበለቶች ቤተክርስቲያን አይክበድባት ይላል (ጢሞ5)፡፡ እንዲሁም በሌላ የተለያየ ሥፍራ መበለቶችን መርዳት እንዳለብን ቃሉ ይናገራልና ቤተክርስቲያን በዚህ ጉዳይ ትኩረት ሰጥታ መበለቶችን መርዳትና ማገዝ ይገባታል ፡፡ በረከቷ ናቸውና ፡፡ ---//---

## እንደጥበበኞች ...

ከገጽ 5 የቀጠለ

አሁን ያለንበት ዘመን ንቃትና ጥንቃቄ የሚጠይቅ ዘመን ነው፡፡ የሚመች ይመስላል፡፡ የሚደላ ይመስላል፡፡ ነጻነት ያለው ይመስላል፡፡ ሁሉ ነገር እንደልብ ያለ ይመስላል፡፡ ነገር ግን የሰው ሕወት እያዘቀጠ የመጣበት ጊዜ ቢኖር ይሄ ጊዜ ነው ፡፡ በዚህ ጊዜ ላይ ከምንጊዜውም ይልቅ በሕይወታችን ከጌታ ጋር ላለን ግንኙነት ትልቅ ጥንቃቄ እንድናደርግ የሚያስፈልግበት ምክንያት የዘመኑ አታላይነትና የጌታ መምጣት መቅረብ ነው ፡፡ ጌታ እየሱስ ክርስቶስ ሊመጣ በደጅ ነውና ፡፡ የእኛ ሩጫ ደግሞ ግቡ እዚያ ነው፡፡ ያ የሞተልንን ጌታ ከሞት የተነሳውን ጌታ እንደገና በክብር ተመልሶ አይተነው ከእርሱ ጋር መኖር ነው የሩጫችን ግብ ፡፡ እዚያ ለመድረስ ግን የተሰጠን ሕይወት ጥንቃቄ ይጠይቃል ፡፡ ምሳሌ 2፤11 ላይ እንደዚህ ይላል፡- "ጥንቃቄ ይጠብቅሃል ፣ ማስተዋልም ይጋርድሃል ፡፡" ጥንቃቄ ይጠብቃል፡፡

አንዳንዶቻችን ስለጥንቃቄ ሲነገረን ትንሽ አክራሪነት ይመስለናል ፡፡ እባክህ አታክርረው እኛ እኮ በጸጋው ነው የዳነው ፡፡ ሃሌሉያ! እግዚአብሄር ምህረቱ ብዙ ነው! ይላሉ፡፡ የእግዚአብሄር ጸጋ ጥንቃቄን የሚያመጣ ጸጋ ኃጢአተኝነትን የሚያስክድ ጸጋ እንጂ በኃጢአት የሚያጨማልቅ ጸጋ አይደለም ፡፡ ስለዚህ መጠበቅ የምንፈልግ ከሆነ ፤በሕይወታች የተጀመረው ነገር ዳር እንዲደርስ የምንፈልግ ከሆነ ፣ከክብር ወደ ክብር እንድንሻገር የምንፈልግ ከሆነ፤ ሊገለጥ ያለውን ጌታ በክብር ለመገናኘት እና ያን እለት እንዳናፍር የምንፈልግ ከሆነ ከጌታ ለተቀበልነው የከበረ ሕይወት ከምንም በላይ እንጠንቀቅ፡፡ ጠቢብ ይጠነቀቃልና ፡፡

በመሳፍንት ምዕራፍ13 ላይ አንድ ቤተሰብ እንመለከታለን ። ያ ቤተሰብ ልጅ ያልነበረው ቤተሰብ ነው ። ነገር ግን እግዚአብሄር አምላክ ወደዚያ ቤተሰብ መጣ ። አንዳንድ ጊዜ አንዳንድ ነገሮቻችን ይቆያሉ ። የቆየ ነገር ደግ ነው።እኛ ግን ነገራችን ወዲያው እንዲሆን እንፈልጋለን ። ግን አንዳንዴ እግዚአብሄር ይቆያል ። ሲቆይ ደህና ነገር ሊያመጣ ነው ። ክብር ለእግዚአብሄር ይሁን ። ይሄ ቤተሰብ ሳይወልድ ቆይቷል። ሴቲቷ መካን ናት። ነገር ግን የእግዚአብሄር መልአክ ወደዚህች ሴት መጣና "ትጸንሻለሽ" አላት ። የምትጸንሽው ልጅ እስራኤልን የሚታደግ ነው ። ናዝራዊ ነው ። እግዚአብሄር የሚጠቀምበት ነው ። ዝም ብሎ ልጅ አይደለም ። ልዩ የሆነ ልጅ ነው ። ነገር ግን አላት ለዚህ አሜን ማለት ብቻ ሳይሆን ይሄ ወደ አንቺ የመጣው በረከት ፣ ይሄ ወደ አንቺ የመጣው ልጅ ጥንቃቄ ይጠይቃል ። ከሚያሰክር ነገር ከወይን ጠጅ ደግሞም ከሚያረክስ ነገር ይሄ ልጅ እስኪወለድ ድረስ እራስሽን ጠብቂ አላት ።

የእግዚአብሄር ነገር ጥንቃቄ ያስፈልገዋል ። ከዚያ በኋላ ለባሏ ነገረችው ። ለባልዋ በነገረችው ጊዜ የዚህ ልጅ መምጣት በጣም ስላስደሰተው የእግዚአብሄርም ነገር እንዳለበት ስላወቀ እርሷ ያለችው ነገር ምናልባት ጉድለት ይኖረዋል ብሎ ስላሰበ እንደገና ወደ እግዚአብሄር ጸለየ ። ‹እግዚአብሄር ሆይ እንደገና ያንን ሰው ላክልን ለዚህ ህጻን የምናደርገውን ጥንቃቄ ያሳየን› ብሎ ጸለየ ። ለጥንቃቄ የሚጸለየውን ጸሎት እግዚአብሄር ይሰማል። ለጥንቃቄ እንድንጸልይ እግዚአብሄር ይርዳን ። እንደገና እግዚአብሄር ያንን መልአክ ላከለት እና ተናገራቸው ። ከነገርኳት ነገር ትጠንቀቅ፤ ይሄ ሕጻን ይወለዳል አለ ። ከተጠነቀቃችሁ በውስጣችሁ ያለ የእግዚአብሄር ነገር ይወለዳል ። ለብዙዎች በረከት የሚሆን፤ ለምድሪቷ ፈውስ የሚሆን፤ የምድሪቷን ጨለማ የሚያበራ፤ የጌታ የኢየሱስ ክርስቶስን ስም ከፍ ከፍ የሚያደርግ የእግዚአብሄር ነገር በሕይወታችሁ ውስጥ ይወለዳል። ካልተጠነቀቃችሁ ግን ይጨነግፋል ። እግዚአብሄር በህይወታቸው የጀመረው ነገር ዳር ሳይደርስ የጨነገፈባቸው ብዙዎችን እናውቃለን ። ሶምሶን ተወለደ ። ከተወለደ በኋላ እግዚአብሄር በኃይል ቀባው ።እግዚአብሄር በሃይል ተጠቀመበት ። ፍልስጥኤማውያንን የሚያናውጥ ሰው ሆነ ። ነገር ግን ሳምሶን እግዚአብሄር ይቀባው፤ እግዚአብሄር ሙላትና ሃይልን ይስጠው እንጂ ጥንቃቄ የጎደለው ቸልተኛ ሰው እንደነበር እናያለን ። ምን እንደሆነ ሁላችሁም ታውቃላችሁ ። የጥንቃቄ ጉድለት የእግዚአብሄርን ጸጋ ተላጭቶ በጠላቶቹ እጅ እንዲወድቅ አደረገው ። ዛሬ በህይወታችን ውስጥ ትልቅ ጥንቃቄ ያስፈልገናል ። ለምንሰማው ነገር መጠንቀቅ ያስፈልገናል ። ለምናየው ነገር መጠንቀቅ ያስፈልገናል ። በእግዚአብሄር ቤት ውስጥ ስንወጣና ስንገባ ጥንቃቄ ያስፈልገናል ። በተለይም ከተቃራኒ ጾታ ጋር ባለን ግንኙነት ጥንቃቄ ያስፈልገናል ፣፡ ከገንዘብ ጋር በተያያዘ ነገር ጥንቃቄ ያስፈልገናል ። የእግዚአብሔርም እጅ እኛ ላይ እንዳትከብድ ጥንቃቄ ያስፈልገናል ። ጥንቃቄ የሌለው ምልልስ የምትመላለሱ ሰዎች ትኖሩ ይሆን? ግዴለሽ የሆናችሁ ሰዎች ትኖሩ ይሆን? እግዚአብሄር እያስጠነቀቃችሁ ፣ የእግዚእብሄር መንፈስ እየወቀሳችሁ ፣ እግዚአብሄር በቃሉ እየተናገራችሁ እናንተ ግን ጥንቃቄ የሌለው ምልልስ የምትመላለሱ ሰዎች ትኖሩ ይሆን ? እግዚአብሄር ዛሬ ማስተዋልን ይስጣችሁ ። ክርስትና ጥንቃቄ ይጠይቃል። ከመዘመር ያልፋል! ከመስበክ ያልፋል! እሁድ ስብሰባ ከመምጣት ያልፋል። በየዕለት ህይወታችን፣ በየእለት ኑሮአችን ይሄ በደሙ የታጠበ፤የነጻና የተቀደሰ ሕይወታችን በተበላሸችው የአለም እርኩሰት እንዳይበላሽ ሕይወታችንን በንጽህና እንጠብቅ። ጌታ እየሱስ ሊመጣ ቀርቧል !! አሜን !

ከሁሉ በላይ እድንጠንቀቅ የሚያስፈልገው በውስጣችን ላደረው ለእግዚአብሄር መንፈስ ነው ። አንዳችን ላንዳችን በጣም እንጠነቀቃለን ። እንትና ሰላም ሳልለው ሄድኩ፡ ለእንትና ጥሩ ሰላምታ አልሰጠሁትም፤ እንትናን አልጠየቅሁትም፡ ለእንትና እንደዚህ አላደረግሁም ፤ ከእንትና ጋር ያለኝ ግንኙነቴ እንዳይበላሽ ይሄንን ላድርግ፤ ብለን እርስበርሳችን ላለን ግንኙነት ለወዳጆቻችን በጣም እንጠነቀቃለን ። እርሱ ጥሩ ነገር ነው ። ነገር ግን ከወዳጆቻችሁ ሁሉ የተለየ እግዚአብሄር ለቤዛ ቀን ዋስትና እንዲሆን በውስጣችሁ ያስቀመጠው የእግዚአብሄር መንፈስ አለና ከሁሉ በላይ ለእርሱ እንጠንቀቅ ። ጠቢብ በጥንቃቄ ይመላለሳል ። በጥንቃቄ የሚመላለስ ይጋረዳል ይሸፈናል ።

2ኛው ጠቢብ እንዴት ይመላለሳል፣ የጠቢብ ጠቢብነቱ መገለጫው ምንድነው? ስንል፡- <u>ዘመኑን እየዋጀ ይመላለሳል ።</u> ሐዋርያው ጥበበኛ ሁኑ ሲላቸው ዘመናቸውን እየዋጁ እንዲመላለሱ ደግሞ ሲናገራቸው እንመለከታለን ። እግዚአብሄር ከሰጠን ነገሮች መካከል አንዱ እድሜአችንን ነው፤ ጊዜአችንን ነው ። የእግዚአብሄር ቃል ዘመናችንን እድሜአችንን ፤ እግዚአብሄር እንድንኖርበት የሰጠንን ዘመን እንድንዋጀው እንድንገዛው ይናገረናል ። ዘመንን መግዛት ማለት ዘመንን የእግዚአብሄርን ሃሳብ በመፈጸም መጠቀም ማለት ነው ። እግዚአብሄር እንድናደርገው የሚፈልገውን የእግዚአብሄርን እቅድ በመፈጸም ዘመኖቻችንን ማጠናቀቅ ማለት ነው ። ቁም ነገር እየሰራንበት! ከጸሐይ በላይ የሚያልፍ መታሰቢያ ያለው ነገር በእግዚአብሄር መንግስት ውስጥ ማከናወን ማለት ነው። እንደ እግዚአብሄር ሰው ፣ እግዚአብሄር እንዳዳነው ሰው፣ እግዚአብሄር እንደጠራው ሰው፣ የእግዚአብሄር ዓላማ እንዳለበት ሰው እንዳንዱን ቀን የእግዚአብሄርን ሃሳብ አድርጎ ማለፍ ዘመንን መዋጀት ማለት ነው ። ስለ እስራኤላውያን የእግዚአብሄር መንፈስ በኋላ ላይ ታሪካቸውን ሲጽፈው እንደዚህ ይላል ። "ቀኖቻቸው በከንቱ አለፉ" ይላል ። ለምንድነው የእስራኤሎች ቀን በከንቱ ያለፈው? ስንል ከእግዚአብሄር ጋራ ሁልጊዜ የሚጋጩ ሰዎች ነበሩና ነው ። የእግዚአብሄርን ሐሳብ የሚጋፉ ፣ የእግዚአብሄርን ነገር የማይቀበሉ ፣ የማያምኑ የሚያጉረመርሙ ፣ ለእግዚአብሄር ሐሳብ የማይመቹ ስለነበሩ ሕይወታቸው በምድረበዳ የመንከራተት ሕይወት! ነበርና አንድም ቁም ነገር ሳይኖረው! በምድረበዳ ሁሉም አለቁ ። አግዚአብሄር ግን የእኔንና የእናንተን ዘመን ለክብሩ ያድርገው ። አሜን!! እድሜአችን አንዳንድ ጊዜ የሚሄድ አይመስለንም። ቀኖቻችን ግን እየሄዱ ነው ያሉት ።

ስለዳዊት ሲጻፍ እንደዚህ ይላል "ዳዊት በራሱ ዘመን የእግዚአብሄርን ሐሳብ ካገለገለ በኋላ አንቀላፋ" (ሐዋ.ሥ13:36) ይላል ። እኛ በዘመናችን ምን ሰርተን ይሆን የምናልፈው ? አንዳንዶቻችን ለእግዚአብሄር ክብር ከመሆን ይልቅ የእግዚአብሄርን ስም የማሰደብ ምክንያት እየሆንን በማይረቡ ሁኔታዎች ፣ የማይቀደሱትንና የማያንጹን ፊልሞች በቴሌቪዥኖቻችን የሚተላለፉ ፊልሞች ጊዜአችንን ላፍ አድርገው እየበሉት ነው ። ሊጸለይበት የሚገባ ጊዜ ፣ወንጌል ሊሠራበት የሚገባ ጊዜ ፣ የእግዚአብሄር ቃል ሊነበብበት የሚገባ ጊዜ፤ ለትውልድና ለቤተክርስቲያን ቁም ነገር ሊሆን የሚችል ነገር ሊሰራበት የሚገባ ጊዜ የማይረቡ የቴሌቪዥን ፕሮግራሞችና ማቆሚያ የሌላቸው የማኪያቶና የክትፎ መብላት የመዞር ጊዜ ሲበላቸው እንደ እግዚአብሄር ሰው ያሳዝነኛል። ወገኖቼ የእግዚአብሄር ሰው ራዕይ ያለው ነው ። ራዕይ ያለው ደግሞ ጊዜውን ለማንም አይሰጥም ። ራዕዩን ለመፈጸም እግዚአብሄር በውስጡ ያደረገውን ነገር ለመፈጸም ሌት ተቀን ይተጋል ።

እግዚአብሄር እናንተንም ጊዜአችሁንም ይፈልጋል!! ጊዜ ተዋጆ ማለት ጊዜን በእግዚአብሄር ፊት ማሳለፍ ስንችል ነው ። ስንቶች ነን ዛሬ ቋሚ የሆነ የማለዳ የጸሎት ጊዜ ያለን ? ስንቶች ነን ዛሬ ቋሚ የሆነ የማታ ጸሎት ጊዜ ያለን? ስንቶች ነን ዛሬ የእግዚአብሄር ቃል ለማንበብ ጊዜ ያለን? የእግዚአብሄር ቃል ጠቢብ ዘመኑን ይዋጃል ይላል ። ምን ሠርተን ነው የምንሞተው ? ዛሬ ብንሞት እግዚአብሄር ልጄ ምን አድርጎ መጣ ይለናል ።

ሐዋርያው ጳውሎስ እኮ *"እሩጫውን ጨርሼለሁ፣ ሐይማኖቱን ጠብቄአለሁ! መልካሙን ገድል ተጋድዬአለሁ! ዘመኔን ዋጅቼዋለሁ! አሁን ጻድቅ ፈራጅ ከሆነው ጌታ ከእርሱ የክብር አክሊል እቀበላለሁ "* አለ ። በ *2ኛ ጢሞ.4፤7-8* ላይ ። የእናንተ እና የእኔ ዘመን ግን ምን አይነት እሩጫ በመሮጥ ነው እየጨረስን ያለነው? የሩጫችንን አቅጣጫ ቀይረን በእግዚአብሄር ሐሳብና ፈቃድ ውስጥ እንድንሮጥ፤ ዘመናችንን ለዚያ እንድናውል እግዚአብሄር ይርዳን!! ዘመናችንን መዋጀት ያለብን ለምን እንደሆነ ከነግራችኋለሁ ። ካለፈ በኋላ ስለማናገኘው ነው !! ትላንት የጠፋ ገንዘብ ዛሬ ሊገኝ ይችላል ። ትላንት የጠፋ ጤንነት ዛሬ እግዚአብሄር ሊመልሰው ይችላል ። ነገር ግን ትላንት ያለፈን ትላንት ዛሬ ብታለቅሱ በምንም ልታመጡት አትችሉም ። ነገር ደግሞ በጊዜው ይከናወናል ። ማንም ሊሠራበት የማይችል ዘመን ይመጣል ። …

ወደ ገጽ 12 ዞሯል

ቤተሰባችን

# አለአግባብ ጋብቻና አስገድዶ...

ከገጽ 1 የቀጠለ

የእግዚአብሄር መለኮታዊ ጣልቃ ገብነት በሚነበብበት በይስሐቅና በርብቃ ጋብቻ የሁለቱም ወላጆች በጋብቻው ውስጥ ዓላማ እንዳለ በመረዳታቸው በእነርሱ ስምምነት ብቻ ጋብቻው አልተፈጸመም ። ሆኖም ግን ድንገተኛ በሆነው ይህ የጋብቻ ትስስር ርብቃ ተጠይቃለች ። እርሷም ለመጋባት ተስማምታለች ። እዚህ ላይ እንደምንመለከተው ምንም እንኳን የርብቃ ቤተሰቦች በጋብቻው ላይ ቢስማሙም ፣ ጋብቻው

ከእግዚአብሄር እንደሆነ ቢረዱም በመጨረሻ ላይ ግን ርብቃን ጠይቀዋታል ፡፡ በጋብቻው ስለተስማማችና እሄዳለሁ ስላለች መርቀው ሸኝተዋል ፡፡ ስለዚህ በጋብቻ ውስጥ ተጋቢዎቹ በማንኛውም መንገድ ይመራረጡ የሁለቱ ተጋቢዎች ስምምነት አስፈላጊና ወሳኝ መሆኑን እንረዳለን ፡፡ የጋብቻ ደራሲው እግዚአብሄር ነው ፡፡ ጋብቻ የተጀመረውም በኤደን ገነት ነው ፡፡ የጋብቻ ሐሳብ ቅዱስ ነው ፡፡ ሰው ግን ቅዱስ የሆነውን ጋብቻ ምንነት ካልተረዳ ሊያበላሸው ወይም ለተበላሸ ዓላማ ሊጠቀምበት ይችላል ፡፡ ጋብቻ ለቤተክርስቲያንና ለሐገር ግንባታ መሠረት የሆነውን ቤተሰብ የሚያስገኝ በመሆኑ፡ የሚጋቡ ሰዎች ጋብቻቸው በቤተክርስቲያን ደረጃ፣በሐገር ደረጃም ሊታወቅ ይገባዋል ፡፡ በዕብራውያን ም.13 ቁ. 4 ላይ ስለዚህ ጉዳይ ይናገራል ፧- “ መጋባት በሁሉ ዘንድ ክቡር መኝታውም ንጹህ ይሁን ሴሰኞችንና አመንዝራዎችን ግን እግዚአብሄር ይፈርድባቸዋል ” ይላል ፡፡

ነገር ግን በአንዳንድ ሐገሮች ህግ ተቀባይነት ቢኖረውም እንኳን በአንዳንድ ሰዎች ዘንድ ከመጽሐፍ ቅዱስ ሐሳብ ውጪ የሚፈጸሙ ጋብቻዎች ግን ክቡር ናቸው ማለት አይደለም ፡፡ በእግዚአብሄር ፊት ተቀባይነት የሌላቸው ለምሳሌ ሴት ከሴት ጋር ወንድ ከወንድ ጋር አንድ ወንድ ከብዙ ሴቶች ጋር አንድ ሴት ከብዙ ወንዶች ጋር የሚያደርጉት ጋብቻ ሁሉ ከእግዚአብሄር እቅድ ውጪ በመሆኑ የረከሰ ነው ፡፡

2ኛ *አስገድዶ መድፈር ምንድነው?*

አስገድዶ መድፈር አንድ ሰው በሌላ ሰው ላይ በተለያየ መንገድ ሃይል በመጠቀም ሳይፈልግ በግድ የሚፈጽመው ወሲባዊ ግንኙነት ነው ፡፡ ይህ አስገድዶ መድፈር በተቃራኒ ጾታም ሆነ በተመሳሳይ ጾታ የሚፈጸምበት ጊዜ አለ ፡፡

በአንዳንድ ቦታዎች አንዳንድ ጊዜ ለጋብቻ የሚፈላለጉ ጥንዶች በሁለቱ ፈቃደኝነት ሆን ተብሎ የተቀናበረ የአስገድዶ መድፈር የሚደረግበት ሁኔታ አለ ፡፡ ይህ የሚሆንበት የተለያዩ ምክንያቶች ይኖራሉ ፡፡ ጥንዶቹ ጋብቻቸውን ቤተሰቦቻቸው እንደማይቀበሉት ከአስገድዶ መድፈሩ በኂላ ግን ጊዜውን ጠብቆ ጋብቻውን ይቀበሉታል ብለው በሚያስቡበት ጊዜ ሆን ብለው አስገድዶ መድፈርን የሚመስል ሁኔታ ሊያዘጋጁና እንደዚህ አይነት ነገሮችን ሊፈጽሙ ይችላሉ ፡፡ በሌላ በኩል ደግሞ አንዳንድ ጊዜ እንዳንድ ጥንዶች ሰርግን ጥሎሽን በአቋራጭ ለማለፍ ይሄ የይምሰል አስገድዶ መድፈርን የሚጠቀሙበት ሁኔታ አለ ፡፡

በተለያዩ ምክንያት የተለያዩ ጥንዶች ሆን ብለው በሁለቱ ፈቃደኝነት የተቀናበረ አስገድዶ መድፈር የሚደረግበት ሁኔታ አለ ፡፡ ምክንያቶቹ ከአካባቢ አካባቢ ሊለያዩ ይችላሉ ፡፡

አስገድዶ መድፈርን በተመለከተ አንድ ወንድ ለጋብቻ በሚፈልጋት ወይም በማይፈልጋት ሴት ላይ ሊሆን ይችላል ከፈቃድዋ ውጪ ስለሚፈጽመው ወሲብ ይህም በጋብቻ ላይ በግለሰብም ሆነ በማህበረሰብ ደረጃ ስለሚያሳድረው ተጽእኖ ቀጥሎ በዝርዝር እንመለከታለን ፡፡

***አስገድዶ መድፈርን ከጋብቻ አንጻር እንመልከት*** *፡- የጋብቻ መሠረት በተጋቢዎች የሚፈጸም ቃልኪዳን ሆኖ ሳለ አንዳንድ ወንዶች ሴቶችን በመጥለፍና አስገድዶ በመድፈር ከፈቃዳቸው ውጪ ጋብቻን ለመመስረት የሚንቀሳቀሱበት ሁኔታ አለ ፡፡ አስገድዶ መድፈር በኢትዮጵያ ሕግ በወንጀል የሚያስቀጣ በእግዚአብሔርም ሕግ ኃጢአት የሆነ ተግባር ነው ፡፡*

ወሲባዊ ጥቃት የተፈጸመባቸው ሴቶች ከጥቃቱ የተነሳ ወደ አልፈለጉት ጋብቻ ውስጥ ከመግባት ከጥቃቱ በማገገም እግዚአብሄርን ተስፋ በማድረግ ለአዲስ ሕይወት እራሳቸውን ማዘጋጀት የሚችሉበትን መንገድ ቢመርጡ የተሻለ ነው ፡፡ ቤተክርስቲያንም ማህበረሰቡንና ወላጆችን የወሲብ ጥቃት ከፈጸመው ሰው ጋር ሴቶች በዛው ጋብቻ እንዲቀጥሉ ከሚደግፈው አስተሳሰባቸው እንዲላቀቁ ለማድረግ ማስተማር ይጠበቃባታል ፡፡ ሆኖም ግን አንድ ጊዜ ተበላሽታለች በቃ ያግባት ብሎ ያለሴቲቱ ፈቃድ አስገድዶ ከደፈራት ሰው ጋር ማጋባት ሴቲቱ ዘመንዋን በሙሉ ልብዋ ለሌለበት ጋብቻ እንድትዳረግ ከማድረግ አልፎ አስገድዶ በመድፈር ጋብቻን መመስረት በማህበረሰብ ውስጥ እንዲስፋፋና የሴቲቱ እህቶች የነገም ልጆቿ በጠቅላላው ማህበረሰቡን የሚጎዳ ነው ፡፡

ጋብቻ በተጋቢዎች መካከል በሙሉ ፈቃድ አብሮ ለመኖር የሚደረግ ስምምነት እንጂ የአንድን ወገን ፍላጎትን ብቻ ለማስፈጸም አንድ ወገን በሌላው ላይ አስገድዶ በወሲባዊ ጥቃት በመፈጸም የሚመሰረት ሕብረት አይደለም ፡፡ ሌላኛው ሳይፈልግ በሚደረግ የግብረ ሥጋ ግንኙነት ወይም አስገድዶ መድፈር የተፈፀመ ጋብቻ <u>የሁለቱ የልብ መጋባት ስለሌለበት አንድ ሥጋ እንደሆኑ አይቆጠርም ወይም ሊቆጠር አይገባውም፤</u> ይህ እንደ ጋብቻ መወሰድም የለበትም ፡፡ አንደኛው በሌላኛው ላይ በእግዚአብሄርም በሰውም ሕግም የሚያስቀጣ ወንጀል በመፈጸም ጋብቻ አይመሰረትም ፡፡

በሌላ በኩል በተለይ ሴቶች ለእንደዚህ አይነት ጥቃት ከሚያጋልጣቸው ሁኔታዎች ራሳቸውን መጠበቅ አለባቸው እንጂ ጌታ ይጠብቀኛል በማለት በጌታ ጥበቃ በማሳበብ ለስንፍናቸው ምክንይት በመስጠት ራሳቸውን ለአደጋ ማጋለጥ የለባቸውም ፡፡ ራሳቸውንም የሚጠብቁትም ከማንኛውም ወንድ ማለት ይዳፈራሉ ከሚሉአቸው ወንዶች ብቻ ሳይሆን አይዳፈሩም ከሚሉአቸው ወንዶች ጭምር ነው ፡፡ ለምሳሌ በመጽሐፍ ቅዱስ ክፍል ስለ አምኖንና ትዕማር እንመለከታለን ፡፡ አምኖን ታምሜአለሁ በማለት ለአባቱ ለንጉስ ዳዊት እህቱ ትዕማርን ወደ ክፍሉ መጥታ ምግብ እንድታቀርብለት ይጠይቃል ፡፡ ተዕማር በእናትም በአባትም

የአቤሴሎም እህት ስትሆን ከአምኖን ጋር የሚገናኙት በአባት ነው ፡፡ ትዕማር ይህን ብታውቅም ምንም ሳትገምትና ሳትጠብቅ ሄዳ ምግብ ማቅረብ ጀመረች ፡፡ ቢሆንም ከእርሷ ይልቅ ብርቱ ነበርና በግዳጅ የመደፈር ጥቃት ውስጥ ገባች ፡፡ ከዚያ በኂላ አምኖን ከቤቱ አስወጡልኝ አለ ፡፡

እርሷም ልብሷን ቀዳ እየጮኸች ሄደች ፡፡ ይህ በዚህ አላበቃም የትዕማር ወንድም አቤሴሎም ቀን ጠብቆ

ከሁለት ዓመት በኂላ የዳዊትን ልጆች ሁሉ ለግብዣ ጠርቶ አምኖንን አስገደለው:: በዘፍጥረት ም.34 ላይ ስለ ያዕቆብ ልጅ ዲና እናነባለን:: የዚያን ሃገር ሴቶች ልጆችን ለማየት ስትወጣ የዚያ ሀገር አለቃ ኤሞር ልጅ ሴኬም ዲና ስትወጣ አያት ወሰዶም አስነወራትም ፡፡ ሴኬም ዲናን ስለወደዳት እርሷን ለማግባት አባቱንና ሰዎችን ላከ ፡፡ በያዕቆብ ቤት ግን እንዲህ አይደረግምና የያዕቆብ ልጆች እህታቸው ሴኬም እንዳስነወራት በሰሙ ጊዜ እነዚያን ሰዎች ሁሉ እንደገደሉና ምርኮን እንደወሰዱ እናነባለን ፡፡ ያዕቆብ ሲቆጣ እነ ስምኦን የተናገሩት ምንድነው ' በጋለሞታ እንደሚደረግ በእህታችን ላይ ያድርግባትን? ነበር ያሉት ፡፡ በእዚህ ክፍሎች እንደምንረዳው አስገድዶ መድፈር እርሷን ብቻ ሳይሆን ቤተሰብን ህብረተሰብን እንደሚነካና ለጉዳት እንደሚያደርስ ነው:::: ስለዚህ ሴቶች በጉልበት ሊበረታባቸው ከሚችል ወንዶች መጠበቅ ይኖርባቸዋል ፡፡

3ኛ) *ተገዳ የተደፈረች ሴት የሚደርስባት ጉዳት ምን ያህል ነው ?*

በ2ኛሳሙ.ም13ቁ.1-33 ላይ እንደምናነበው ተገዳ የተደፈረችው ትዕማር ምን ያህል በስነልቦና መጎዳቷን ልብሷን በመቀደድና አመድ በራሷ ላይ በመነስነስ እጇን በራሷ ላይ በማድረግና በመጮህ እንደገለጸችው እንመለከታለን ፡፡ ተገዳ የተደፈረች ሴት ብዙ ጉዳቶች ሊጋጥማት ይችላል ፡፡ አንዳንድ ጉዳቶች ሁሉም ጥቃቱ የደረሰባቸው ሴቶች የሚደርስባቸው ሲሆኑ አንዳንዶቹ ጉዳቶች ግን አንዳንዶቹን ብቻ የሚያጋጥማቸው ይሆናል ፡፡ ከነዚህ ውስጥ አንደኛው ያልተፈለገ እርግዝና ነው ፡፡ ሁሉም እንዲዚህ ላያጋጥማቸው ይችላል ፡፡ ነገር ግን የተወሰኑት በአስገድዶ መድፈር ያልተፈለገ እርግዝና ሊያጋጥማቸው ይችላል ፡፡ ይህ እርግዝና በሚያጋጥምበት ጊዜ እነዚህ ሴቶች የተለያዩ የተወሰሰቡ ሁኔታዎች ያገጥሟቸዋል ፡፡ አንዳንዶቹ እርግዝናውን ለማስወረድ ይሞክራሉ ፡፡

ይህን በሚሞክሩበት ጊዜ እርግዝናውን በማስወረዳቸው የሚሰማቸው የጥፋተኝነት ስሜት አለ ፡፡ የራሳቸውን ልጅ ነው እያስወረዱ ወይም እየገደሉ ያሉት ፡፡ ስለዚህ በዚህ የጥፋተኝነት ስሜት የመዋጥ ጉዳት ውስጥ ይገባሉ ፡፡ አንዳንዶቹ ደግሞ እርግዝናውን ለማስወረድ ሲሉ ለዚህ የሚያስፈልጋቸው ገንዘብ ስለማይኖራቸው ይህንን ገንዘብ ለማግኘት የተለያዩ ክፉ ድርጊቶችን ለመፈጸም ሊነሳሱ ይችላሉ ፡፡ስርቆት ውስጥ ሊገቡ ይችላሉ ወይም ደግሞ ገንዘብን ፍለጋ ዝሙትን ወደ መስራት ሊሄዱ ይችላሉ ፡፡ ከዚያ አልፎ ደግሞ የማስወረዱ ሥራ ➔

በሴቲቱ ላይ ከቀላል ለሞት እስከሚያደርስ አካላዊ ጉዳት ሊደርስ ይችላል ። እርግዝናውን የሚጠብቁ ሴቶች ይኖራሉ። ሳያገቡ ተገዶ በመደፈር የተነሳ ያረገዙትን ለመውለድ በሚያስቡበት ጊዜ ማህበረሰቡ ስለእነርሱ በሚያወራው ወሬ ተጽእኖ ሊደርስባቸው ይችላል ። ከቤተሰብ ጋር ሊጋጩ ይችላሉ፤ ከማህበረሰብ ከጓደኞች ጋር ሊጋጩ ይችላል ። ሌላው ደግሞ የተለያዩ የህይወት እቅዶቻቸው ለጊዜውም ቢሆን መስተጓጎል ሊያጋጥማቸው ይችላል ። አንዳንዶች ትምህርታቸውን ሊያቋረወጡ ይችላሉ ።

**4ኛ አስገድዶ መድፈር የተንሰራፋበት ማህበረሰብ ምን ይመስላል?**

አስገድዶ መድፈር በህግ በማያስቀጣበት ወይም ህግ እያለ መንግስትና ማህበረሰቡ ህጉን የማይጠቀሙበት ማህበረሰብ፤ ለዝሙትና ለምንዝርና ገሃዳዊ ፈቃድ የሰጠ ነው ማለት ይቻላል።ዝሙትን እንደ ጀግንነት የሚያይ ማህበረሰብ ውስጥ የቤተሰብን ፈቃድ ለማለፍ ተብሎ ይሁን ደግሞ ጥሎሽና ሰርግን ለማለፍ በተለያዩ ምክንያቶች ይሆናል እንደዚህ አይነት መሰል ምክንያቶችን ተንተርሶ አስገድዶ መድፈርን ወደ ጋብቻ የመግቢያ መንገድ አድርጎ የሚቀበል ማህበረሰብ፤ በማህበረሰብ ላይ ለሚንሰራፋ አስገድዶ የመድፈር ወንጀል የተጋለጠ ይሆናል።

አስገድዶ የመድፈር ወንጀል እየከፋ ከሄደ በአዋቂዎች ላይ ብቻ ሳይሆን ለአቅመ አዳም ባልደረሱ ህጻናት ሁሉ ላይ ሊፈጸም የሚችል ወንጀል ነው ። ከዚያ ሲያልፍም በተቃራኒ ጾታ ላይ ይሁን በተመሳሳይ ጾታ መካከል ከጋብቻ ጋር ፈጽሞ ተያያዥነት በሌለው መልኩ ከመፈጸም ባለፈ በአንድ ሰው ላይ በአንድ ጊዜ ለብዙ በመሆን የአስገድዶ መድፈር ወንጀል ለመፈጸም እስኪነሳሱ የሚደርሱ ህሊናቸው የደነዘዙ ሰዎች በማህበረሰብ ውስጥ እንዲፈልቁ የሚሆንበት ሁኔታ ሊፈጠር ይችላል ። እንዲህ ዓይነቱ ሐጢአት በተመሳሳይ ጾታም ሆነ በተቃራኒ ጾታ የሚደረግ የአስገድዶ መድፈር በተለይ ለብዙ ሆኖ በአንድ ሰው ላይ የሚፈጸም አስገድዶ መድፈር ወንጀል እስከመፈጸም ድረስ የሚደርሱ ግለሰቦች በምድራችን ላይ ሊኖሩ እንደሚችሉ ማሰብ ወደዛ ከመድረስ በፊት ከወዲሁ በዚህ እስገድዶ የመድፈርን ወንጀል ማስወገድ ላይ የበኩላችንን አዎንታዊ የሆነ ድርሻ ለመወጣት እንድንሳሳ ሊያደርገን ይችላል ።

***...ወደ ገጽ 11 ዞሯል***

### እግዚአብሄርን መፍራት ከገጽ 4 የቀጠለ

የእግዚአብሄር ሰው ሙሴን እንመልከት ። እንደሙሴ እግዚአብሄርን ያወቀው ማንም ነብይ በዓለም አልተነሳም ይላል መጽሐፍ ቅዱስ ። እንደ ሙሴ ፊት ለፊት እግዚአብሄርን ያነጋገረ ; እግዚአብሄር የመለሰለት ማንም የለም ። ነገር ግን እግዚአብሄር በሲና ተራራ ላይ በተገለጸበት ጊዜ ሙሴ እንዲያው አወቅሁ ብሎ ዘው ዘው ብሎ አልሄደም ። ነገር ግን ከዚህ ቀደም ካወቀው ይልቅ በልዩ ሃይልና ክብር ስለመጣበት እፈራለሁ እንቀጠቀጣለሁ አለ ። ዛሬም እግዚአብሄር በልዩ ክብርና ሃይሉ በሚገለጥበት ጊዜ መንቀጥቀጥ ይሆናል ። ምንም እንኳን ልጆቹ ብንሆን ፤በደሙ የተዋጀን ብንሆን እግዚአብሄር አምላካችንን በልዩ ነገር ባወቅነው ቁጥር የሚኖረን ፍርሃት የሚኖረን መንቀጥቀጥ ታላቅ ነው ። ብዙ ጊዜ ስህተቶች ይፈጸማሉ ። የሚፈጸሙት ምናልባት ደጋግመን ከምንሰማው ስብከት ነው ። ጌታ ኢየሱስ ወንድማችን ነው። አሜን ። ጌታ ኢየሱስ አባታችን ነው ። እንዲህ ያሉ ነገሮችን ስንሰማ አሜን እንላለን እውነት ነው ። ነገር ግን ወገኖች ሆይ ያ ማለት ግን እግዚአብሄርን በጣም አውቀነዋልና በእግዚአብሄር ላይ መዝናናት እንጀምራለን ማለት አይደለም ። ስህተት ላይ እንወድቃለን። ምክኒያቱም እግዚአብሄር የሚያቃጥል የሚያጠፋ እሳት ነው ። አዎ ወገኖች ሆይ እግዚአብሄር ታላቅ በልእልና የተሞላ አምላክ ነው ። ስለዚህ የእግዚአብሄርን ማወቅ በጣም ገዝፎ በሚመጣበት ጊዜ የእግዚአብሄር ህዝቦች ድሮ ከሚፈሩት ይልቅ እግዚአብሄርን ይፈሩታል ። ይሄን እግዚአብሄር ያድርግልን ። ከእግዚአብሄር ቤት እግዚአብሄርን መፍራት ሲጠፋ እንደሚያስፈራኝ ነገር ሌላ የሚያስፈራኝ ምንም ነገር የለም ።

2ኛ. ሰዎች እግዚአብሄርን መፍራት የሚያቆሙት <u>መንፈሳዊ እውርነት በላያቸው፡ ላይ በሚመጣበት ጊዜ ነው</u> ። አንድ ጊዜ አብርሃም ጌራራ ወደ የሚባል ሃገር አንደሄደ በዘፍ. ም.20 ላይ እንመለከታለን ። በዚያም ሰዎቹን ተመለከታቸው። አብርሃም በጣም የተደነቀው ነገር በፍጹም ሰዎቹ እግዚአብሄርን መፍራት በአይናቸው ፊት አለመኖሩን ነው ። ስለሆነም ሚስቱ ሳራም ውብ ሴት ስለነበረች እርሷን እንዲህ አላት “ ቢጠይቁሽ ወንድሜ ነው በይ እኔም ደግሞ እህቴ ናት እላለሁ” ። በማለት ተስማምተው ሄዱ ። ንጉሱም ሳራን ወሰዳት ከእርሰዋ ጋር ሊተኛ ፈለገ ። እግዚአብሄር ግን ታላቅ አምላክ ነውና እንዲገናኛት አልፈቀደም ። እርሷ ባለባል ናት ይህም ሰው ነብይ ስለሆነ ተጠንቀቅ አለው ። እገድልሃለሁ አለው እግዚአብሄር ። እግዚአብሄር ይሄን ባለው ጊዜ ንጉሱ ጠዋት ተነስቶ ምንድነው ያደረግህብን ? ብሎ አብርሃምን ጠየቀ ። ምን ላድርግ ? አለ አብርሃም በዚህ ከተማ እግዚአብሄርን መፍራት እንደሌለ አየሁ አለ ። ስለምትገድሉኝ ከመዋሸት ሌላ ምንም ምርጫ የለኝምና አለ ። እግዚአብሄር ግን ጣልቃ ገባ። ሮሜ ም. 3 ቁ 13-18 ላይ እግሮቻቸው ደም ለማፍሰስ ፈጣኖች ናቸው ከከንፈሮቻቸው በታች የእባብ መርዝ አለ በአይናቸው ፊት እግዚአብሄርን መፍራት የለም ይላል ። እግዚአብሄርን መፍራት ሲያቆሙ መታወር ነው ።ይሄ ከባድ የሆነ ነገር ነው ። ከዚሁ ጋር አያይዘን የምንመለከተው ሌላው ነገር እግዚአብሄርን እናውቃለን የሚሉ ሰዎችም ቢሆኑ ሃጢአት ወደ ህይወታቸው በሚመጣበት ጊዜ ልቦናቸውን ያሳውራል። ሀጥያት መንፈሳዊ ነገሮችን እንዳናይ ይከላከለናል ። በመጽሐፍ ቅዱስ ላይ ስንመለከት በ1ኛ ሳሙኤል ም. 2 ላይ ስለ ኤሊ ልጆች ታሪክ እናነባለን ። እነዚህ ልጆች ካህናት ናቸው። ነገር ግን እግዚአብሄርን አይፈሩም ነበር። መስዋዕት በሚቀርብበት ጊዜ ለእግዚአብሄር ሊሰዋ የሚገባውን ነገር እየቀሙ እነርሱ ወደ ቤታቸው ይዘው ይሄዳሉ ወይም ደግሞ እዚያው በቤተመቅደስ ይበሉ ነበር። ከዚያም አልፎ ደግሞ ቤተመቅደስ ውስጥ ከሚያገለግሉት ሴቶች ጋር ያመነዝሩ ነበር፡ ይላል ። ምን ነካቸው እነዚህ ሰዎች? እነዚህ የትልቅ ካህን ልጆ ምን ነካቸው? የደረሰባቸው ነገር ምንድነው? <u>መንፈሳዊ እውርነት</u> ደረሰባቸው ።

በኢሳይያስ መጽሐፍ ላይ ስናይ
“ ከባርያዬ በቀር እውር ማነው? ” ከባርያዬ ከመረጥኩት ሌላ የታወረ ማነው ይላል ። **ሐጢአት ያሳውራል!** የገንዘብ ፍቅር ያሳውራል! የሥጋ ምኞት ያሳውራል ! እርሱን መፍራት በአይናቸው ፊት ስለሌለ እያወቁት እንደ እግዚአብሄርነቱ መጠን ስላላወቁት እነዚያን ሁለት ሰዎች መታቸው፤ ቀሰፋቸው፡ ሞቱ ። ለምን? በእግዚአብሄር ላይ ተዝናንተው ነበርና ። ዛሬ እንዲህ አይነት ወንጌል ብዙ ጊዜ አይሰበክም ። ነገር ግን እላችኋለሁ ወደ እግዚአብሄር በተጠጋን ቁጥር ወደ ውስጠኛው ቤተ መቅደስ በገባን ቁጥር የሚገባውን ክብርና ፍርሃት ካልሰጠነው ዛሬም እግዚአብሄር እኛን ይመታናል ። ምክንያቱም ያው የጥንቱ እግዚአብሄር የዛሬም እግዚአብሄር ነው ። አዲስ ኪዳን ለመዝናናት ያስችለናል ማለት አይደለም ። ለመቀለድ ያስችለናል ማለት አይደለም ። እንዲያውም ያ ሥጋ ለብሶ ከድንግል ማርያም የተወለደው እየሱስ ክርስቶስ በዚህ ምድር ላይ የራሱን ሥጋውን ቆርሶ ደሙን አፍሶ ወደ ቅድስተ ቅዱሳን ያስገባን ጌታ ዛሬም ፈራጅ ነው ።

**3ኛው፡- <u>አለመታዘዝ</u> ፡- ሰዎች አለመታዘዝን ሲመርጡ** ፤ ክቡር ለሆነው ለእግዚአብሄር ቃል እምቢ ሲሉ ማለት ነው ። ጌታችን እየሱስ ክርስቶስ እንዲህ አለ ስለ ፍርድ ሲናገር የምፈርድባችሁ እኔ አይደለሁም <u>አባቴ ነው</u> አለ ። እንደገና <u>የሚፈርድባችሁ</u> ይሄ የምትሰሙት <u>የእግዚአብሄር ቃል ነው</u> አለ ። ብዙዎቻችን መጽሐፍ ቅዱስ በቤታችን አለ፤ እናነበዋለን ! ቤተ ክርስቲያን እየመጣን ቢያንስ በሳምንት አንድ ጊዜ የእግዚአብሄርን ቃል እንሰማለን ። ነገር ግን ይህ ቃል ካልታዘዝነው በእኛው ላይ መልሶ ሰይፍ ይመዘብናል ። እንድንታዘዘው የእግዚአብሄር ቃል ይናገራል ። እግዚአብሄርን መፍራት ያስፈልገናል ።

በሚልክያስ መጽሐፍ ላይ ነብዩ ሚልክያስ በተነሳበት ዘመን እስራኤላውያን መስዋእትን በእርግጥ ለእግዚአብሄር ያቀርቡ ነበር ። ሲያቀርቡ ግን ፈጽሞ ከቃሉ ውጭ የሆነውን ያቀርቡ ነበር ። መስዋእት ሲያቀርቡ የመጀመርያውን ማህጸን የሚከፍተውን ለእግዚአብሄር እንዲሰጡ ነው እግዚአብሄር ያዘዛቸው ። እንከን የሌለውን አንካሳ ያልሆነውን እውር ያልሆነውን በሽታ የሌለበትን ነበር ያዘዛቸው ። እነርሱ ግን የማይፈልጉትን፤ አርደው እንኳን ሊበሉት የማይችሉትን አይኑ የታወረውን ሰባራውን እያመጡ ለእግዚአብሄር የምንሰጠው መስዋእት ነው ይሉ ጀመር። እግዚአብሄርም ይህን አየና ነብይን ላከባቸው “ይሄንን ለአለቃህ አቅርብለት ።ትወስድለታለህ ወይ? ። አትወስድም ! አለ ። ስለዚህ በሚልኪያስ1፡6 ላይ እግዚአብሄር ምን አለ? “እኔስ አባት ከሆንኩ ክብሬ ወዴት አለ? ጌታስ ከሆንኩ መፈራቴ ወዴት አለ ?” አለ ።

→

እግዚአብሄር የሚፈልገው የህይወታችንን ትራፊ አይደለም፡፡ የገንዘባችንን ትራፊ አይደለም፡፡ እግዚአብሄር ከእኔና ከእናንተ የሚፈልገው ***በኩራትን*** ነው! ፡፡ **ለእርሱ በኩራት ይገባዋል** ፡፡ በመስቀል ላይ ደሙን ስለእኛ ያፈሰሰ የራሱን ሕይወት ሳይሳሳ ቆርሶ የሰጠን እርሱ በኩራት ይገባዋል ፡፡ የእኔና የእናንተ ነገር ለእግዚአብሄር መሰጠቱ ለእግዚአብሄር የሚጠቅመው ሆኖ አይደለም ፡፡ ነገር ግን በአባትነቱ ይከበራል በጌትነቱ ይፈራል ፡፡ ስለዚህ የእግዚአብሄር ፍርሃት በቤቱ እንዲነግስ ያስፈልጋል ፡፡ የእግዚአብሄር ፍርሃት በኑሮአችን እንዲሆን ያስፈልጋል ፡፡ በምናደርገው ነገር ሁሉ ላይ የእግዚአብሄር ፍርሃት መኖር ይኖርበታል ፡፡ በቤታችን እንገባለን፤ በሮቻችን እንቆልፋለን፤ መሽቷል ብቻችንን ነን ያለነው፡፡ ምን እንደምንሠራ ምን እንደምናደርግ ማንም ሰው አያውቅም፡፡ እግዚአብሄር ግን ይመለከታል **እርሱን መፍራታችን የሚታወቀው ያኔ ነው** ፡፡ ምድራዊ ገዢዎችን አለቆች ባለሥልጣናትን እንፈራቸዋለን፡፡ እነርሱ ግን አንድ ቀን በነው ይጠፋሉ፡፡ የእኔና የእናንተ ጌታ ግን ለዘላለም ይኖራል ፡፡ እግዚአብሄር የተባረከ ይሁን ፡፡ ስለዚህ የእግዚአብሄር መፈራቱን ስናስብ ዳዊት ሲናገር “ወደ እግዚአበሄር ቤት በገባህ ጊዜ እግርህን ጠብቅ” ይላል ፡፡ ሁለመናችን የተጠበቀ መሆን ይኖርበታል፡፡ ለምን? እግዚአብሄርን እንፈራዋለን፡፡ይህ የእግዚአብሄር መገኘት ያለበት ሥፍራ ነው ፡፡ በእርግጥ ወገኖች ሆይ በዚህ ዘመን ይሄን ለብሳችሁ ኑ ይሔን አታድርጉት የሚል ሥብከት አይሰበክም ፡፡ምክንያቱም ሰዎች በሕግ ሳይሆን እግዚአብሄርን በመፍራት ሊያደርጉት ይገባቸዋልና ነው፡፡

***እግዚአብሄርን በመፍራት የምንጠቀመው ምንድነው?***

1ኛ **የእግዚአብሄር አይኖች እርሱን በሚፈሩት ሰዎች ላይ ነው** ፡፡ የእግዚአብሄር አይኖች ሁልጊዜ እርሱን በሚፈሩት ላይ ለበጎ የተገለጡ ናቸው ፡፡ መውጣትና መግባትህን እግዚአብሄር ይጠብቃል ይላል መፅሐፍ ቅዱስ፡፡ የማንን ? የአንተን፡፡ ለምን? እርሱን በመፍራት ስለምትመላለስ ፡፡ በኢዮብ መጽሐፍ በም.1 ቁ 1 ላይ ስንመለከት የአምላክ ልጆች በእግዚአብሄር ፊት ለመቆም መጡ ሰይጣንም ደግሞ በመካከላቸው መጣ፡፡ እግዚአብሄር ጠየቀው ከወዴት መጣህ አለው ፡፡ ሰይጣንም ምድርን ሁሉ ዞርሁአት በእርስዋም ተመላለስሁ ወዲያ ወዲህ ተንከራትቼ በደንብ ፈትሼአታለሁ አለ፡፡ የእግዚአብሄርን ቃል “እርኩስ መንፈስ ከሰው በወጣ ጊዜ” ይላል ፡፡ እነሆ ይወጣል ነገር ግን ከወጣ በኋላ ተመልሶ ይመለከተዋል ሰውየውን ከሩቅ ሆኖ ይጎበኘዋል ፡፡ ይፈትሸዋል እኔንና እናንተን ወገኖቼ ይፈትሸናል ያየናል ማለት ነው ፡፡ ስለዚህ እግዚአብሄር ባሪያዬን ኢዮብን አየኸው ወይ? እንደእርሱ ቅን በጎ እግዚአብሄርን የሚፈራ ማንም የለም ፡፡ኢዮብ እግዚአብሄር የመሰከረለት ሰው ፡፡ ኢዮብ እግዚአብሄርን የሚፈራ ሰው ነበር ፡፡ ምናልባት ልጆቼ በልባቸው እግዚአብሄርን ሰድበዋል እያለ በየጊዜው ይቀድሳቸው ነበር ይላል መፅሐፍቅዱስ ፡፡ እስከዚህ ድረስ እግዚአብሄርን ይፈራው ነበር ፡፡ እውነት ነው እግዚአብሄር ሊፈራ የሚገባው ነው፡፡ እግዚአብሄርም ኢዮብን እያየ ደስ ይለዋል ፡፡ ወገኖች ሆይ ስትፈሩት እግዚአብሄር ደስ ይለዋል ፡፡ የእርሱ አይኖች እናንተ ጋ ነው ያሉት ፡፡ ስለዚህ እንደ ኢዮብ እግዚአብሄርን የሚፈራ ሰው እንሁን ፡፡ መጽሐፍ ቅዱስ **የእግዚአብሄር መልአክ እርሱን በሚፈሩት ሰዎች ዙርያ ይሰፍራል ይላል**፡፡ ተስፋውን አያችሁት? እርሱን በሚፈሩት ዙርያ የእግዚአብሄር መልአክ ይሰፍራል ፡፡ ይሄ ቀላል ነገር አይደለም ፡፡ ይሰፍራል ይገኛል ፡፡ እርሱንስ በማይፈራ ሰው ዘንድ ይሰፍራል ወይ? አይሰፍርም ማለት ነው፡፡ አይገኝም ማለት ነው ፡፡ ምክንያቱም እግዚአብሄርን መፍራት በእርሱ ዘንድ የለምና፡፡

2ኛ **እግዚአብሄርን ስንፈራው ቤታችን ኑሮአችን የተባረከ ይሆናል** ፡፡ በኤፌሶን 5- 21 ላይ ባልና ሚስት በእግዚአብሄር ፍርሃት እንዲኖሩ ይናገራል ፡፡ እግዚአብሄርን በመፍራት በሚኖሩበት ጊዜ እግዚአብሄር አምላክ እቤታቸውን ይባርከዋል ፡፡ ትልልቅ የእግዚአብሄር ሰዎች የወጡበትን እስቲ እዩ ! ሁልጊዜ አንድ አይነት አገላለጽ ነው ያለው፡፡ ወላጆቹም እከሌ እከሌ ይባሉ ነበር; እግዚአብሄርንም የሚፈሩ ነበሩ ይላል ፡፡ እግዚአብሄርን መፍራት ባለበት ቤት ውስጥ ሐሜት የለም ፡፡ ጸብ የለም ፡፡ ክርክር የለም ፡፡ ምክንያቱም ሚስትም ትፈራለች ባልም እግዚአብሄርን ይፈራል ፡፡ ልጆችም ደግሞ በዚያው መስመር ይሄዳሉ; እግዚአብሄርን ይፈራሉ ፡፡

3ኛ **የእግዚአብሄር ፍርሐት ኃጢአትን ከመስራት ይቆጥበናል** ፡፡ የእግዚአብሄር ፍርሐት ውስጣችንን ሲሞላው ኃጢአት ለማድረግ ፈጣኖች አንሆንም ፡፡ ብናደርግ እንኳን በሚያስፈራው በእግዚአብሄር ፊት ተንበርክከን በሑሑታና በጩኸት በለቅሶ የእግዚአብሄርን ይቅርታ እንጠይቃለን፡፡ 2ኛ ቆሮ. ም.7 ቁ.1 ላይ ስንመለከት የእግዚአብሄር ፍርሃት በቅድስና እግዚአብሄርን በመፍራት መኖር እንደሚገባን ይናገራል ፡፡ ዮሴፍን እንመልከት ፡ ዮሴፍ በጌታው በጶጢፋር ቤት ውስጥ በነበረበት ጊዜና ወቅት የጶጢፋር ሚስት ችግር ውስጥ ልትጥለው ሞክራ ነበር ፡፡ ነገር ግን እንቢ ስላለ እስር ቤት ውስጥ ወደቀ፡፡ ሰባት ዓመት ታሰረ ፡፡ ለሰዎች ሞኝነት ይመስላል ፡፡ ማን ያየው ነበር ? ምን ተቸገረ 7 ዓመት ገብቶ የሚማቅቀው ? የሚሉ ሊኖሩ ይችላሉ ፡፡

ቆራጥ አቋም ነበረው፡፡ እግዚአብሄር ከሚወስኑ ሰዎች በስተጀርባ አለ፡፡ አቋም አስፈላጊ ነው፡፡ ሰባት ዓመት ሁሉ ያየው የተመለከተው የተቀበለው ራዕይ ፈተነው ይላል ፡፡ ፈተና የለም አይደለም ወገኖቼ ትፈተናላችሁ፡፡ ለምን መከራ እቀበላለሁ ? ለምን በዚህ ውስጥ ሁሉ አልፋለሁ? በመስሪያ ቤቴ የሚደርስብኝስ እግዚአብሄርን በመፍራቴ አይደለምን? በትምህርት ቤት ውስጥ በትዳር ውስጥ እግዚአብሄርን በመፍራቴ አይደለምን? ይሄ ሁሉ የምቀበለው ክርስቲያን በመሆኔ አይደለምን? ልንል እንችላለን፡፡ ቀላል ነው ማለቴ አይደለም ፡፡ ሰባት ዓመት ፈተነው ጠላት ተፈታተነው ፡፡ እግዚአብሄር ግን በእርሱ ወቅትና ሰዓት ለባርያው ሊመሰክር መጣ ፡፡ ዮሴፍን አከበረው ፡፡ ወገኖች ሆይ ያከብራችኋል፡፡ ወደ እናንተም ቤት ይመጣል ፡፡ ወደ አንተም ቤት አንድ ቀን ይመጣል ፡፡ እርሱ አንድ ቀን መጥቶ ከፍ ያደርጋችኋል ፡፡ የዮሴፍ ሕይወት **ቁልፉ እግዚአብሄርን መፍራት ነበር** ፡፡ ፈርኦን ምን ሰጠው? በሙሉ እንዳለ ሃገሩን አስረከበው ፡፡ ምክንያቱ ለምን ነበር ? ፈተና መጣለት; ፈተናውን ግን አለፈ ፡፡ እግዚአብሄር ፈተናችሁን እንድታልፉ ይርዳችሁ !! ፈተናው በጣም በትንንሽ ነገር ሲሆን ይችላል ፡፡ ለይሁዳ 30 ብር ናት፡፡ ግን ፈተናውን ሊያልፉት አልቻለም ፡፡ ለአንዳንዶች ምን ፈተና እንደሚመጣ አላውቅም ፡፡ ለሳምሶን ሌላ ነው፣ ለአንዱ ትእቢት ነው፣ ለሌላው የተለየ ነው፡፡ ብዙ አይነት ፈተናዎች ይመጡላችኋል ፡፡ በተለይ የእግዚአብሄር እጅ ከእናንተ ጋር መሆን ሲጀምር! አገልጋዮች ከአደጋ መዳን ከፈለጋችሁ የሚመጣላችሁን ክብር አትቀበሉት ፡፡ ወደ እናንተ ሲመጣ ወደ ጌታ መልሱት ፡፡ ክብሬን ለማንም አልሰጥም ይላል ጌታ፡፡ እየተፈተናችሁ ያንን ፈተና ካለፋችሁ የእግዚአብሄር እጅ በእናንተ ላይ ይሆናል፡፡

**4ኛው እግዚአብሄርን በመፍራት ጸሎታችን ይመለሳል**፡፡ ዕብራውያን፡ 5፣7-8 ለይ ስለእየሱስ ክርስቶስ ከተነገረው የተሻለ ጥሩ ምሳሌ የለንም ፡፡ “እግዚአብሔርንም ስለመፍራቱ ተሰማለት” ፡፡ ይላል ፡፡ ጌታ እየሱስ እግዚአብሄር አብን ይፈራ ነበር ፡፡ ከመፍራቱም የተነሳ ጸሎቱ ይሰማ ነበረ ፡፡ አንዳንዶቻቻችን የመጸለይ ችግር የለብንም፡፡ የመጾም ችግር የለብንም ፡፡ግን ጸሎታችን ያለ ፍርሃ እግዚአብሄር ነው ፡፡ አንድ ሰው አስታውሳለሁ፡፡ እንደዛ ሰው የሚጾም ሰው አላየሁም ፡፡በጣም ይጾማል ፡፡ አገልጋይ ነው ፡፡ ሲጸልይ ደግሞ እየተንከባለለ ነው የሚጸልየው ፡፡ ሲነሳ ግን ይሄንንም ይዞ በጥፊ ያቺንም ይዞ እንደዛው፤፤ሰዎችን ከቤተክርስቲያን ማባረር ነው፡፡ የማያለቅስበት ሰው የለም ፡፡ ስለዚህ በኋላ ይህ ባህሪው ተለመደና እርሱ ሲጸልይ ሲንከባለል ሌሎች ክርስቲኖች ያው እንግዲህ ይንደባለል ተውት ይሉ ነበር ፡፡ ያ አይነት ፀሎት ተሰሚነት የለውም ፡፡ አንድ ነገር አስፈላጊ ነው! ፍርሃ እግዚአብሄር!! ፍርሃ እግዚአብሄር አንደበታችንን ይቆጣጠራል፣ ፍርሃ እግዚአብሄር ቁጣችንን ይቆጣጠራል ፣ ነገራችንን ሁሉ ይቆጣጠራል ፡፡ ወገኖች ሆይ የምናደርገውን ነገር ሁሉ በፍርሃት እናድርግ ፡፡ አገልግሎት ያለፍርሃ እግዚአብሄር ምን ያደርጋል? አንዳንዴ ይመስለናል ፡፡ ይኸው እርሱ እንደፈለገ አይደለም የሚኖረው? አገልጋይ አይደለ ?እከሌ ምን ሆነ ? እገሊት አሁን እንደፈለገች ነው የምትኖረው ምን ሆነች? እንላለን፡፡ ለጊዜው ይመስለናል እንደዛ መቀጠል የሚቻል ይመስለናል ፡፡ እመኑኝ አይቻልም ፡፡ እግዚአብሄር ዛሬም በዙፋኑ ላይ ነው ፡፡ አምላካችን ዛሬም የሚፈራ አምላክ ነው!! የሚሰገድለት አምላክ ነው ፡፡ መላዕክት ፊቱን አያዩም ቀና ብለው አይመለከቱም ፡፡ ከመላዕክት መካከል ለእርሱ የቀረቡት እንኳ እነ ሱራፍልና ኪሩቤል እንኳን ስድስት ክንፍ ያላቸው ሁለቱን የሚጠቀሙበት ፊታቸውን ለመሸፈን ነው ፡፡

በፊትህ ማን መቆም ይችላል እያሉ ሌሊትና ቀን ይሰግዳሉ ፡፡ ማን ሊቆም ይችላል? በፊቱ ማንም ሊቆም አይችልም!! እኔና እናንተ የምናመልከው ጌታ አጋንንትና መናፍስት በፊቱ ሊቆሙ አይችልም ፡፡

➔

በሽታ ደዌ ፣ህመም ቫይረስና ካንሰር በፊቱ ሊቆም አይችልም ። ክፉ የሆነ ሃይል ሁሉ በፊቱ ሊቆም አይችልም!! ማን በእርሱ ፊት ሊቆም ይችላል?

5ኛ <u>እግዚአብሄርን ስንፈራ የእርሱ መገኘት በፊታችን ይሄዳል</u> ። ዘጸአት ም.23 ቁ.27 ላይ መፈራቴን በፊትህ እሰዳለሁ… ይላል። እስራኤላውያንን ነው ያላቸው። የእግዚአብሄርን ታቦት ተሸክሞ መሄድ ብቻ ነው ለእነርሱ የሚያስፈልጋቸው። ሌላ የሚያደርጉት ነገር የለም ። ወዲያውኑ በዚያ ከተማና በዚያ በጠላት ሰፈር ላይ የእግዚአብሄር ፍርሃት ይወድቅ ነበር ። የእስራኤል አምላክ ወደሰፈሩ መጥቶብናል ወየው ይላሉ ። እንዲንቀጠቀጡ ያደርጋቸው ነበር ። ለምን? የእግዚአብሄር ፍርሃት ቀድሞ በህዝቡ ላይ ይወድቅበት ነበረና ነው። ዛሬም ወገኖች ሆይ ቤተክርስቲያን የእግዚአብሄር ፍርሃት በላይዋ ላይ ቀድሞ ሲመጣ አህዛብ ሁሉ ይንቀጠቀጣሉ ። ይፈራሉ ። እግዚአብሄርን ስንፈራው ቀድሞ ይወጣል ። መፈራት በምንኖርበት አካባቢ ይመጣል! መፈራት በመስሪያ ቤታችን ይመጣል። መፈራትና ግርማና ሞገስ በምንሄድበት ሁሉ ሥፍራ ይሆናል ። ለምን? እግዚአብሄርን እንፈራዋለንና የእርሱ ህልውና እየወጣ ከፊታችን ይራመዳል ።ሃሌሉያ ። እግዚአብሄር ሲፈራ እግዚአብሄር በሰው ፊት የሚያሳልፈው ይህንን ነው። ዛሬ እኔና እናንተ ለህይወታችንና ለአገልግሎታችን የሚያስፈልገን ጸጋ ይሄ ነው ። ለእግዚአብሄር ለአምላካችን ዛሬም የሚኖረን ፍርሃት፤ በፊቱ ያለን መንቀጥቀጥና መውደቅ ይሄንን ያከናውናል !! ስለ ንጉስ ዳዊት በ1ኛ ዜና ም.14 ቁ.17 እና በ1ኛ ሳሙኤል ም. 11 ቁ.7 ላይ ይሄንን ትመለከታላችሁ ። ወደ አዲስ ኪዳን ስንመጣ በሐዋ፣ም.5 ላይ በነበሩትም ህዝቦች ላይ ታላቅ ጸጋ ነበረባቸው ይላል ህዝቡም ይፈሩአቸውና ያከብሩአቸው ነበር ። ሊተባበራቸው የሚደፍር አንድም እንኳን አልነበረም ይላል ። እግዚአብሄርን ስለፈሩት እርሱ ደግሞ አብሮአቸው ወጥቶ ነበር ።

6ኛ..<u>እግዚአብሄር ታላቅ ሥራውን የሚያከናውነው እርሱን በሚፈራ ሰው ውስጥ ነው</u> ።

ሰው እግዚያብሄርን ሲፈራ እግዚአብሄር ሊያከብረው ይጀምራል!! በሉቃስ ወንጌል ም.23 ቁ.40 ላይ ከጌታ እየሱስ ክርስቶስ በስተቀኝ የነበረው ያ ወንበዴ ምን አይነት የመገለጥ መንፈስ በዚያ ሰዓት እንደተሰጠው በጣም ይገርመኛል ። አስበኝ በመንግስትህ ማለቱ ለእኔ ይደንቀኛል! ጌታ እየሱስ ክርስቶስ መንግስት እንዳለው ማን አስተማረው? ያኛው ወንበዴ ጌታን በሚሳደብበት ጊዜ ይሄኛው ምንአለው አንተ እግዚአብሄርን አትፈራም? እግዚአብሄርን መፍራት በውስጥህ የለም? እኔና አንተ የሚገባንን አገኘን ይህ ሰው ግን ንጹህ ሰው ነው! አለ ። ዘወር አለና ጌታ ሆይ በመንግስትህ ስትመጣ አስበኝ አለው ። ጌታም እውነት እልሃለሁ ከዚህ ሰዓት ጀምሮ በገነት ከእኔ ጋር ትኖራለህ አለው ። ወገኖች ሆይ በእግዚአብሄር ቃል ስንመለከት በዘጸአት ም.18 ቁ.21 እነዚያ ከሙሴ ጋር እንዲያገለግሉ እግዚአብሄር የመረጣቸው ሰዎች ፍርሃ እግዚአብሄር የነበራቸው ናቸው ። በነህምያ ም.7 ቁ. 2 ላይ ተመልከቱ ፤ፍርሃ እግዚአብሄር ነበራቸው ። ዛሬም እግዚአብሄር እስከመጨረሻው እርሱን የሚፈራውን ሰው በፊቱ የሚንቀጠቀትለትን ሰው ይፈልጋል ።

7ኛ እግዚአብሄርን የሚፈሩ ህዝቦች <u>በጎ ነገር አይጎድልባቸውም</u> ። ከመልካም ነገር ሁሉ ይጠግባሉ ይላል ። ወገኖች ሆይ ዛሬ ሰዎች በአቋራጭ ሃብት ሲበዛላቸው፣ በአቋራጭ እንደተደላደሉ ሲመስሉን፤ ከፍ ከፍ ያሉ ሲመስሉን ሕይወታችን አንዳንዴ ጥያቄ ውስጥ ያድራል ። ፈተና ውስጥ እንወድቃለን ። ነገር ግን እላችኋለሁ ያ ታይቶ እንደሚጠፋ አበባ ነው ። ነገር ግን የአንተ መልስ ሲመጣ ፣የአንተ በረከት ሲመጣ ለአንተ መጎብኘት ሲሆንልህ ፍሬ ያለው የሚኖር የማይሞት ደስ የሚያሰኝ በረከት ነው። ስለዚህ እግዚአብሄርን ለሚፈሩ ከበጎ ነገር አይጎድልባቸውም ይላል መፅሐፍ ቅዱስ ። ምንም አይጎድልብንም ። ስላልዋሸን ፣ ጉቦ ስላልተቀበልን፣ ስላልሰጠን ፣ባለማጭበርበራችን፣ባለማታለላችን የሚጎድልብን ምንም የለም ። ሁሉ ነገር አለን። ጌታ የተባረከ ይሁን ። ሁሉም ደግሞ ይበዛልናል ። ልዩነታችን ይህ ነው ። እነርሱ ጋ አንድ አሲድ አለ ። ያላቸው ነገር ሁሉ በረከት የለውም ። የሚያከማቹት ሁሉ በረከት የለውም ። ይሰበስባሉ አይበሉትም ፣ ይሰራሉ አይኖሩበትም ። ያከማቻሉ አንድም የሚቀርላቸው ነገር የለም ። ለእኔና ለእናንተ ግን እግዚአብሄርን ለምንፈራ እግዚአብሄር ጥቂቱን ነገር ያበዛልናል ። በክፉም ቀን አናፍርም ። እቤታችን የተረጋጋ ነው ኑሮአችን የተረጋጋ ነው ።

ወደጌታ ያልመጣችሁ እህቶቼ ወንድሞቼ ትኖሩ ይሆናል። ወደጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ መምጣት ትፈልጋላችሁ፡፤ ግን ትፈራላችሁ ምክንያቱም እኔ እንዴት አድርጌ እመጣለሁ ስንት ነገር ይጎድልብኛል ፤ አሁን ጌታ እሱስ ክርስቶስ በሕይወቴ እንዲገባ ብፈቅድ ሕይወቴ ቢለወጥ ዝናዬ ይሄዳል ብዙ የሚጎድሉብኝ ነገሮች አሉ እኔ የማቃቸው ብላችሁ ታስቡ ይሆናል ። ይሄ እንዳያሳስታችሁ። ይሄ የጠላት ወሬ ነው ። ወደ እየሱስ ስትመጡ ጥቂቱ መቶ ይሆናል ። መቶው ሺህ ይሆናል ። ክብር ለእርሱ ይሁን!!

እግዚአብሄር አምላክ ስደተኛይቱን አስቴርን ያከበረ፣ የወደቀችውን ሩትን ወደ እግዚአብሄር ሰው በመጠጋቷ እግዚአብሄርን በመፈለግ ጌታ ያከበራት፡ ባዶ የነበረውን ቤት የሞላ አምላክ ነው ። በጽድቅ የሚገኝ መዝገብ ይበልጣል ። ሕይወታችሁን ለእየሱስ ክርስቶስ ያልሰጣችሁ የመዳን ቀን አሁን ነው!! ምክንያቱም ወደድንም ጠላን እየሱስ ክርስቶስ ይመጣል። ለፍርድ ይመጣል! የዚህ ዓለም መጨረሻ የሚጠቃለለው በሌላ አይደለም፡ እየሱስ ክርስቶስ ሲመጣ ነው ። እግዚአብሄርን ፍሩት እርሱን በመፍራት እንጠብቀው ። እግዚአብሄርን መፍራት መዝገቡ ነው ይላልና ቃሉ ፡ --//--

## መድፈር የተንሰራፋበት ህብረተሰብ..

ከገጽ9 የቀጠለ

አስገድዶ መድፈርን በተመለከተ በመጽሀፍ ቅዱስ ውስጥ ከተጻፉ ታሪኮች አንዳንዶቹን እንመልከት ፡ በተመሳሳይ ጾታም ሆነ በተቃራኒ ጾታ አንድ ሰው በአንድ ሰው ላይ ወንጀል ከመፈጸም ባለፈ ብዙዎች በመፈራረቅ በአንድ ሰው ላይ ወንጀል የፈጸሙበትን ታሪክ እናገኛለን ። በዘፍ.19 ከ1-11 ባለው ክፍል ላይ ሰዶም የነበረበትን ሁኔታ እንመለከታለን ።

"ገናም ሳይተኙ የዚያች ከተማ የሰዶም ሰዎች ከብላቴናው ጀምሮ እስከሽማግሌው ድረስ በየሥፍራው ያለው ህዝብ ሁሉ ቤቱን ከበቡት። ሎጥንም ጠርተው እንዲህ አሉት፡- በዚህ ሌሊት ወደቤትህ የገቡ ሰዎች ወደየት ናቸው? እናውቃቸውም ዘንድ ወደ እኛ አውጣቸው ። ሎጥም ወደ እነርሱ ወደ ደጅ ወጣ መዝጊያውን በኋላ ዘጋ እንዲህም አለ ፡-

ወንድሞቼ ሆይ ይህን ክፉ ነገር አታድርጉ እነሆ ወንድን ያላወቁ ሁለት ሴት ልጆች አሉኝ እነርሱን ላውጣላችሁ እንደወደዳችሁም አድርጉባቸው በእነዚህ ሰዎች ብቻ ምንም አታድርጉ እነርሱ በጣራዬ ጥላ ሥር ገብተዋልና። እነርሱም፡- ወዲያ ሂድ አሉት።ደግሞም እንዲህ አሉት፡- ይህ ሰው በእንግድነት ለመኖር መጣ ፍርዱንም ይፈርድ ዘንድ ይፈልጋል አሁን በአንተ ከእነርሱ ይልቅ ክፉ እናደርግብሃለን። ሎጥንም እጅግ ተጋፉት የደጁንም መዝጊያ ለመስበር ቀረቡ። ሁለቱም ሰዎች እጃቸውን ዘርግተው ሎጥን ወደ እነርሱ ዘንድ ወደ ቤት አገቡት መዝጊያውንም ዘጉ ። በቤቱ ደጃፍ የነበሩትንም ሰዎች ከታናሻቸው ጀምሮ እስከ ታላቃቸው ድረስ አሳወሩአቸው ። ደጃፉንም ለማግኘት ሲፈልጉ ደከሙ"(ዘፍ19፤4-11)ይላል ። የሰዶም ሰዎች የወጡት በብዛት ጎልማሶችና ወጣቶች ብቻ ሳይሆን ብላቴኖችና ሽማግሌዎች ጭምር ነበር ። ሁሉም የወጡት በሁለቱ ሰዎች ላይ ወሲብ ለመፈጸም ነው ለማለት ያስችግራል። ነገር ግን የተወሰኑት ተራ በተራ ይህን ወሲብ ለማድረግ የተነሳሱ እንደሆነ እንረዳለን ። ታዲያ ለአቅመ አዳም ያልደረሱ ብላቴኖችና ሽማግሌዎች ለምን ወጡ ለሚለው ጥያቄ ይህንን የወሲብ ወንጀል እንደ ትእይንት ለማየት የመጡ ነበሩ ለማለት ይቻላል ።

ከክፍሉ እንደምንመለከተው ጤነኛ አእምሮ ላለው ሰው ለመረዳት እጅግ የሚቸግር አንድ ነገር እናያለን ፡- ሎጥ በሁለቱ ሰዎች ላይ ወንጀሉ እንዲደረግ ካለመፈለጉ የተነሳ ሁለት ደናግል ሴቶች ልጆቹን ለእነርሱ ለመስጠት ፈቃደኛ ሆኖ ሳለ ፡ እነርሱ ግን ከደናግል ሴቶች ይልቅ ከተመሳሳይ ጾታ ጋር ከወንድ ጋር ወሲብ ለመፈጸም መፈለጋቸውን እንመለከታለን ። ሎጥ ላውጣላችሁ ባላቸው ጊዜ እነዚህ የሰዶም ሰዎች የሰጡት ምላሽ፤- እርሱ ራሱ እንግዳ ሰው መሆኑንና በዚህ አካባቢ ላይ መርሆዎችን የማውጣት መመርያን የመስጠት ተገቢ የሆነውንና ያልሆነውን ነገር የመናገር መብት እንደሌለው የሚገልጽ ምላሽ ነበር ። እንደዚህ የከፋ ወንጀል ወደሚፈጸምበት ማህበረሰብ ወደመሆን ሰዶም በአንድ ጀንበር ገብቷል የሚል ሃሳብ የለኝም ። ነገር ግን አስገድዶ መድፈር ከትንሽ ጀምሮ አንድ ወንድ በአንድ ሴት ላይ ከመፈጸም ጀምሮ ከዛ በኋላ አስገድዶ መድፈር በወጣቶች ላይ መፈጸም፤ በልጆች ላይ ፤በአዛውንቶች ላይ ወደመፈጸም ከዚያ በኋላ በአንድ ሰው ላይ ከመፈጸም አልፎ ብዙ ሰዎች ሆነው በአንድ ሰው ላይ ወደመፈጸም እንዲህ እያለ ይህ አስገድዶ መደፈር እየሰፋ የሚሄድ መሆኑን መናገር ይቻላል ።

→

እነዚህ የሰዶም ሰዎች የደረሱበትን ደረጃ ስንመለከት ደናግል ሴቶች ተሰጥቷቸው ሳለ እነርሱ ላይ የአስገድዶ መድፈርን ለመፈጸም ፈቃደኛ ባለመሆን ከዚህ እጅግ የከፋውን ነገር ማለትም እንግዶች የሆኑት ወንዶችን ላይ አስገድዶ የመድፈርን ወንጀል ለመፈጸም በመፈለግ አስተሳሰብና መንፈስ ሲያዙ እንመለከታለን ፡፡ በጊዜው ሎጥ ተቀብሎአቸው የነበሩት ሁለት ሰዎች የእግዚአብሄር መልአክቶች ስለነበሩ እነዛ ሰዎች እንዲታወሩ በማድረጋቸው አስገድዶ መድፈር ወንጀሉ ሳይፈጸም የቀረበት ሁኔታ ነው ያለው ፡፡ እዚህ ደረጃ ላይ የደረሰውን ማህበረሰብ እግዚአብሄር በምን አይነት ቅጣት እንደቀጣ በክፍሉ መጨረሻ እናነባለ ፡፡ የእሳት ዲን ከሰማይ አዘነበ ፡፡ሰዶምንና ነዋሪዎችዋን ሁሉ አጠፋ፡፡

በሌላ የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍል ላይ ደግሞ እጅግ የከፋ አስገድዶ መድፈር ሲፈጸም እንመለከታለን ፡፡ በመፅሐፈ መሳፍንት19 ላይ ከቁ.16 ጀምሮ አንድ ከኤፍሬም ሐገር በእንግድነት በጊብአ የቀመጠ ሽማግሌ ሰው አንድ መንገደኛ አግኝቶ በአደባባይ ከሚያድር በቤቱ ከቁባቱና ከከብቶቹ ጋር እንዲያድር ይጋብዘዋል ፡፡ እንግዳውም እሺ ብሎ ወደ ሽማግሌው ቤት ያመራል ፡፡ በዚያም ከተማ የነበሩት ሰዎች ቢንያማውያን ነበሩ ፡፡ እንግዶቹ አርፈው በልተው ጠጥተው ሰውነታቸውን ደስ ካሰኙ በኋላ በከተማው የነበሩት ወስላቶች ተሰብስበው ቤቱን ከበቡት ፡፡ ሽማግሌውንም ወደቤትህ የገባው ሰው ማነው እንድንደርስበት አውጣልን አሉት ፡፡ ሽማግሌውም ወንድሞቼ ሆይ ይህ ክፉ ነገር አታድርጉ ይህ ሰው ወደ ቤቴ ገብቷልና ድንግል ልጄ እና የእርሱም ቁባት አሉ አሁንም አወጣቸዋለሁ እንደወደዳችሁም አድርጉባቸው በዚህ ሰው ግን እንደዚህ አይነት ሐጢአት አታድርጉ፡አላቸው ፡፡ እነርሱ ግን አልሰሙም ፡፡ በአስቸገሩአቸው ጊዜ ቁባቷን አውጥተው ሰጧቸው ፡፡ እነዚህም ምናምንቴዎች እስኪነጋ ድረስ ተራ በተራ በሴቲቱ ላይ አመነዘሩባት ፡፡

ሲነጋም ወደ ኤፍሬም ተራራ የሚሄደው እንግዳ የቤቱ በራፍ ላይ ወድቃ አገኛት፡፡ ሞታ ነበር ፡፡ እስክትሞት ድረስ እነዚህ ወስላቶች አመነዘሩባት፡፡ ይህም አንግዳ ሰው ቁባቱ እንዲህ መሞቷን ተመልክቶ እጅግ በማዘኑ ሰውነቷን ለአስራሁለት ቆራርጦ ለአስራሁለቱ ነገዶች መላኩንና እንዲህ አይነት ነገር በእስራኤል አይደረግም አስቡበት ምከሩበት ሲል እንመለከታለን ፡፡ በዚህም ምክንያት አስራ አንዱ የእስራኤል ነገድ ተሰባስበው ወደ ቢንያም ሃገር በመምጣት ከእስራኤል ይህንን ክፉ ሥራ እናስወግዳለንና እነዚህን ወስላቶች አውጡልን ብለው ሲጠይቁ እናያለን ፡፡ ቢንያማውያን ግን አናወጣም በማለታቸው ትልቅ ጦርነት መቀስቀሱን እናነባለን ፡፡ በዚህም ጦርነት እሥራኤል ለጊዜው ሁለቴ በመሸነፍ ብዙ ሺህ ህዝብ ቢያልቅበትም በሦስተኛው ዙር ግን የቢንያማዋውያንን ነገድ በጣት እስከሚቆጠሩ ድረስ እንደጨረሷቸውና ከተማቸውን እንዳቃጠሉ ከ25 ሺህ ህዝብ በላይ እንደገደሉ እንመለከታለን፡፡ ታዲያ ይህ ሁሉ እልቂት ለምን መጣ ስንል፡- አስገድዶ የመድፈርን ወንጀል የሚፈጽሙ ወስላቶችን አጋልጦ የማይሰጥና በእቅፉ የሚይዝ ማህበረሰብ በመፈጠሩ ነው ፡፡ እነዚያን ወስላቶች ወይ ሳይቀጣ ወይ አጋልጦ ሳይሰጥ በእግዚአብሄር ላይ ትልቅ በደል በመፈፀሙ ሁሉም ለእልቂት ሲዳረጉ እንመለከታለን፡፡

**5ኛ) የአስገድዶ መድፈር ወንጀልን እንዴት መቀነስ ይቻላል?**

1ኛ) የሕዝቡን አእምሮ በመገንባትና ወንጀሉ ሊያደርስ የሚችለውን ጉዳት እንዲያዩ በማድረግ ፡፡ ይህንን ወንጀል አቅልሎ ከማየት ይልቅ ወንጀሉ እጅግ የከፋ ጉዳት በማህበረሰቡ ላይ ሊያደርስ እንደሚችል ሰዎች እንዲረዱት ማድረግ ይገባል ፡፡

2ኛ) በመንግስት የወጡ አስገድዶ መድፈርን የሚቃወሙ ሕግጋትን በመጠቀም ወንጀለኞች በሕግ እንዲጠየቁ በማድረግ ፡፡

3ኛ) ይሄን አስገድዶ መድፈርን የሚያስፋፉ ክፉ መናፍስትን በጸሎት መፋለም፡፡

4ኛ) አስገድዶ መድፈርን ህዝቡ እንዲጸየፈው የሚያደርግን መረዳት ወደ ህዝቡ የማድረስን በአእምሮ ደረጃ ሊሠራ የሚችለው ሥራ መሥራት ፡፡ ይሔ ሁሉም የሚሠራው ሥራ ነው ፡፡

5ኛ) በተገኘው አጋጣሚ ሁሉ አስገድዶ መድፈርን መቃወምና ብዙዎች እንዲቃወሙት ማነሳሳት፡ በመሥሪያ ቤቶቻችን፤ በትምህርት ቤቶቻችን፤ በአምልኮ ሥፍራዎች(በየትኛውም ሃይማኖት ያሉ ሰዎችን ሊጎዳ የሚችል ስለሆነ) ይህንን ወንጀል መቃወምና እንዲቃወሙት ማነሳሳት ፡፡

6ኛ) እግዚያብሄርን መፍራትን ህዝቡን ማስተማር፡፡ የእግዚአብሄር ሰዎች ሊሠሩት የሚችሉት አንዱ ሥራ እግዚያብሄርን መፍራትን ህዚቡን ማስተማር ነው፡፡ ይህ ወንጀሉን የሚፈጽሙ ሰዎችና ለወንጀል መፈጸም ሰዎችን የሚያመቻቹ ሰዎች እንዲቀንሱ ሊያደርግ የሚችል ነው ፡፡

7ኛ) ለትዳር አጋር ታማኝ የመሆንን አስፈላጊነት ማስተማር፡፡ ለትዳር አጋር ታማኝ መሆን ሞኝነት ሳይሆን ሥልጣኔ እንደሆነ እንዲያስቡ ማስቻል፡፡ በባለትዳሮች መካከል መቻቻልና መተጋገዝን ማጎልበት በጋብቻ ውስጥ የሚያጋጥሙትን ተግዳሮት በጽናት መፋለምና ድል በማድረግ የሚገኘውን ደስታ አብሮ ማጣጣም፤በቤተሰብ መካከል የሥራ ክፍፍልንና የሐላፊነት እንዲገነባ ማድረግ እንዲሁም ጊዜያቸውን ለመልካም ነገር እንዲያውሉት ማድረግ ፡

8ኛ ) ግልጽነትና መደማመጥ በትዳር ውስጥ ሆነ በጠቅላላው በማህበረሰብ ውስጥ ማስረጽ ፡፡

9ኛ) ሴቶች ከአስገድዶ መደፈርም ሆነ ከሌሎች በሰይጣን ወይም በሰው ወይም በተፈጥሮ አደጋ ሊደርስባቸው ከሚችል ጉዳት ጌታ እንዲጠብቃቸው በጸሎት መጋደል ፡፡ በተስፋ ቃሉ መሠረት የጥበቃ ጸሎት ማድረግ አስገድዶ መድፈር እንዳይስፋፋ ያደርጋል ፡፡

10ኛ) የመጨረሻው ሰው የዘራውን የሚያጭድ እንደሆነ ማወቅና ማሳወቅ ነው ፡፡ የተዘራው ክፋት ሲበዛ አጨዳው በዚያው መጠን ይበዛል ፡፡በኦሪትዘሌዋውያን ምዕራፍ 18 እንዲህ ይላል፡- እንደተቀመጣችሁበት እንደግብጽ ምድር ሥራ አትስሩ እኔም እንደማስገባችሁ እንደ ከነዓን ምድር ሥራ አትሥሩ በሥርዓታቸውም አትሂዱ በእነዚህ ሁሉ ከፊታችሁ የማሳድዳቸው አሕዛብ ረክሰዋልና በማለት ያስጠነቅቃል፡፡

በአጠቃላይ የጋብቻን ዓላማና ክብር በማህበረሰብ ውስጥ ማስፋፋት እጅግ መልካም ነው ፡፡ የወሲብን ፍላጎት በሰዎች ውስጥ ያስቀመጠው እግዚአብሄር ሰዎች ይህንን ፍላጎት የሚያረኩበትን መንገድ አዘጋጅቷል ፡፡ ይህ መንገድ ጋብቻ ይባላል ፡፡ ይህንን ስል የጋብቻ ዓለማ ወሲብን ማርካት ነው እያልኩ አይደለም ፡፡ የጋብቻ ዓላማ ወሲብን ከማርካትም ያለፈ ነው ፡፡ የጋብቻ ዓላማ በቅድሚያ ጋብቻና ሰውን የፈጠረውን እግዚአብሄርን ማገልገል ነው ፡፡ ነገር ግን እግዚአብሄርን ከማገልገል ቀጥሎ ጋብቻ የእያንዳንዱ ግለሰብ ወሲባዊ ፍላጎት ማርካትም ሌላው ኣላማው ነው ፡፡ ስለዚህ የእግዚአብሄርን ሐሳብ ከማገልገል ጋር ከእግዚአብሄር ጋር ያለንን ጤናማ ግንኙነት ከመጠበቅ ጋር ባል ከሚስት ሚስት ከባል ጋር ጤነኛ ህብረት እንዲኖራቸው፡ ከዚያም አንዳቸው የሌላውን የወሲባዊ ፍላጎት እንዲያረኩ ይህም የእግዚአብሄር ፈቃድ ነው ፡፡ ስለዚህ ይህንን የእግዚአብሄር ፈቃድ ያለበትን ጋብቻ እግዚአብሄርንም ለማገልገል፤ ባል ለሚስት ሚስት በሏን እንዲያገለግሉ በጋብቻ ውስጥ ያለውን ዓላማ በማህበረሰብ ውስጥ ማስረፅ አስገድዶ መድፈርን ወንጀል ይቀንሳል ፡፡ --//--

## እንደጥበበኛች ...

ከገጽ 7 ዞረ

ማንም ምንም ሊያደርግ የማይችልበት ዘመን ይመጣል ፡፡ እግዚአብሄር በሰጠን ዘመን የእግዚአብሄርን ሐሳብና የእግዚአብሄርን ዕቅድ አድርገን እንድናልፍ ዘመናችንን እንድንዋጅ እግዚአብሄር ይርዳን ፡፡ ሰይጣን የብዙ ሰዎችን ዘመን እንዲሁ አጨልዉ፡ በላው!! እግዚአብሄር ጊዜን የሰጠን ግን ያን ጊዜ ለእግዚአብሄር ክብር እንድናውል ነው ፡፡

3ኛው፡- ጠቢብ እንዴት ይመላለሳል ስንል የእግዚአብሄርን ፈቃድ እያደረገ ይመላለሳል ፡፡ " ስለዚህ የጌታን ፈቃድ ምን እንደሆነ አስተውሉ እንጂ ሞኞች አትሁኑ"(ኤፌ5፡17) እግዚአብሄር ለእናንተ እቅድና ዓላማ አለው፡፡ ያንን ነው ማየት ያለብን ፡፡ ምንድነው ለእኔ ህይወት የእግዚአብሄር ኣላማ ማለት አለብን፡፡ ሰው ሁሉ አሜሪካ ስለሄደ አሜሪካ መሄድ የለብንም፤ ሰው ሁሉ ዓረብ ሃገር ስለሄደ ዓረብ ሃገር መሄድ የለብንም ፡፡

ብዙ ጊዜ እኛ የእራስ እቅድ የሚባል ነገር አይገባንም ፡፡ እዚህ ጎረቤታችን ሱቅ ከከፈተ ሁላችንም ሱቅ ነው የምንከፍተው ፡፡ እንትና ሥጋ ቤት ከከፈተ ሁላችንም ሥጋ ቤት ነው የሚከፍተው ፡፡ ነገር ግን እንደዚህ መሆን የለብንም፡፡ እግዚአብሄር በአንተ ሕይወት ላይ ዓላማ አለው!!!! እግዚአብሄር በአንቺ ሕይወት ላይ ዓላማ አለው ! ጠቢብ ሰው እግዚአብሄር ለግሉ ያለውን የእግዚአብሄር ዓላማ ይረዳል ፡፡

የኩሬኝ ህይወት ይብቃን ፡፡ ደግ ደጉን እንኮርጅ፡፡ ግን በሕይወታችን ያለውን የእግዚአብሄርን ፕሮግራም ግን ከማንም መኮረጅ አንችልም ፡፡ የእኛ የተለየ ነው ፡፡ ➔

ይስሐቅ ረሐብ በመጣ ጊዜ አብርሃም ወደ ግብጽ ስለወረደ ወደ ግብጽ ሊሄድ ተነሳ :: ቀላል ነው ምንም ችግር የለውም ::
ግብጽ ዳቦ አለ :: አባቴም በረሐብ ጊዜ ወደ ግብጽ ነው የወረደው እኛም ወደ እዛ እንኮብልል ብሎ ሲነሳ እግዚያብሄር፡-"አይደለም! በአብርሃም ያለው አሠራርና በአንተ ያለው አሠራር ልዩነትአለው" አለው፡ ‹‹ወደ ግብጽ አትውረድ በምልህ ቦታ ተቀመጥ :: በዚያ እኔ ከአንተ ጋር እሆናለሁ›› አለው:: ክብር ለእግዚአብሄር ይሁን!! የእግዚአብሄርን ፈቃድ ማስተዋል ማለት ለእናንተ ሕይወት እግዚአብሄር ያለውን ዕቅድና ዓላማ መረዳት ማለት ነው :: የእግዚአብሄር ፈቃድ ውስጥ ትልቁ በረከት ማግኘታችን ፣ ማጣታችን; ውጤታማ መሆናችን፣ አለመሆናችን ብቻ ሳይሆን በእግዚአብሄር ፈቃድ ውስጥ የምናገኘው ሌላም ነገር አለ :: አሁን አንዳንድ ጊዜ እንትና በእግዚአብሄር ፈቃድ ውስጥ ስላልኖረ አልተሳካለትም ብቻ ነው የምንለው አይደል? ካለመሳካትም ያልፋል :: ሰው ያለ እግዚአብሄር ፈቃድም ሄዶም ሊሳካለት ይችላል :: ምድራዊ ነገር ሊሳካለት ይችላል :: በእግዚአብሄር ፈቃድ ውስጥ ስንሆን የሚመጣው ትልቁ ነገር እግዚአብሄር ከእኛ ጋር ይሆናል

አዎ ! የእግዚአብሄርን መገኘት በሕይወታችሁ ውስጥ የምትፈልጉ ከሆነ ፣የእግዚአብሄር መገኘት አብሮአችሁ እንዲገኝ የምትሹ ከሆነ ዛሬ እነግራችኋለሁ!! እግዚአብሄር ከማ ጋር ይሆናል ብትሉኝ እግዚአብሄር በፈቃዱ ሐሳብ ውስጥ ከሚኖር ሰው ጋራ ይሆናል ::

ብዙ ነገር እጡ ፣ አንድ ነገር ግን እንዳታጡ እለምናችኋለሁ :: የፈለገ ነገር በሕይወታችን ውስጥ ይጥፋ ፣ ብዙ ነገር ወደ እኛ አይምጣ ፣ ብዙ ነገር ከእኛ ይወሰድ ፣ ነገር ግን አንድ ነገር አይወሰድ የሰራዊት አምላክ የእግዚአብሄር አብሮነት ከእኛ አይወሰድ:: እግዚአብሄር ከሌለ ምድርና ሞላዋ የእኛ ብትሆን ባዶ ነው!!! በእግዚአብሄር ውስጥ ግን ምድረበዳም ሙላት ነው:: ምድረ በዳም ብልጽግና ነው:: ዛሬ ከእግዚአብሄር ርቀን ልንሄድ እንችላለን:: እንደፈለገን ልኖር እንችላለን:: ሊሳካልን ይችላል:: ነገር ግን አንድ ነገር እናጣለን:: እግዚአብሄር የፈለግነውን አይከለክልም:: ግን እጁን ያወጣል ! እግዚአብሄር ከሕይወቱ ውስጥ እጁን ከሚያወጣ ዛሬ ብሞት ይሻለኛል

## ቅድስና ለእግዚአብሄር ነው !

*ከአንተነህ ተሰፋዬ*

እስቲ አባቴ ልጠይቅህ
በኤደን ገነት ውስጥ ሳለህ
እንዴት ነበር ያኔ ፍቅርህ
ይሞቅ ነበር ወይ ለብ ያለ
መልስልኝ ግልጽ አድርገህ
ከአንተና ከእናታችን
ሌላ ሳይኖር ሚቀናቀን
የሚያስቀና ሁሌ አንተን
እየመጣ ሌትና ቀን
ወይስ በዱር አናብስቱ
ትቀና ይሆን በተብእቱ
ይጥምህ ነበር ያኔ ፍቅሩ
ተቀናቃኞች ሳይኖሩ
ሔዋንን የሚያዳንቋት
አሞካሽተው የእርሷን ውበት
ምቀኛም ሳይኖርባችሁ
መሐል ገብቶ የሚያጣላችሁ
ራቀ ብለህ ከሥፍራው ሔደህ
በሄዋን ልብ ናፍቆት ነበረህ?
ታዲያ ካልሄድክ ራቀ ብለህ
ሁሌ በአይንህ እየተያየህ
ሰለቸችህ አንጂ ሄዋን
ዘወትር የምታያት ሌትና ቀን?
ካልሰለቸችህ ካልታከተህ
ታዲያ ልጆችህ በማን ወጣን
በአንድ የማንወሰን
አንዱን ስንይዝ ሌላው ያምረናል
አልገባኝም ለምን ይሆን
እስቲ አዳም ልጠይቅህ
መልስልኝ ግልጽ አድርገህ
የዘመናችንማ
አዳም ባክህ እስኪ ስማ
የእጮኛሞች መከዳዳት
ከእግዜር ፈቃድ ወጥቶ መሳት
ያለጊዜው ክበድ መሆን
መበዳደል መተዛዘን
ባጣ ቆየኝ ባጣ ቆዪኝ
ለጥቅሙ ለጥቅሚ
ባይሳካለት ዳግም ሊገኝ
በዚያን ጊዜ ይህ ነበር ወይ?
መልስልኝ እስቲ አዳም ሆይ
እስቲ አባቴ ልጠይቅህ
መልስልኝ ግልጽ አድርገህ
የባልና ሚስቱ ግጭት
የጎሪጥም መተያየት
ለምን ይሖን በዘመኑ
አንዱ አንዱ መኮነኑ
ያለመተማመን የመጣው
ያኔ ይሆን በቅርቡ ነው
እስቲ አዳም ሆይ ልጠይቅህ
መልስልኝ ግልጽ አድርገህ
ምናልባት ያቺ የበላሃት እጸበለስ
ዘርታ ኖረች በአንተ ዓመጽ
ከዚያ ወዲህስ እንዴት ነበር
የአንተና የሔዋን ፍቅር
እስቲ አዳም ሆይ ልጠይቅህ
መልስልኝ ግልጽ አድርገህ
እህ አንተ አዳም ምነው ዝም አልክ
ጥያቄዬን እየሰማህ
እንዳልሰማ ጆሮ ዳባ ልበስ ብለህ
አሃ ገባኝ ገባኝ ለጥያቄ መልስ
ባይኖርህ
ተሳስሮብህ አንደበትህ
በአዲስ ኪዳን አንተ አልኖርህ
ደግሞስ ምን ጥልቅ አድርጎህ
ለካ አንተ አቅም አጥተህ
ህግን ሰምተህ ህግን ጥሰህ
በህግ ሞተህ ተቀብረሃል
በአሸናፊው በአማኑኤል ተሸረሃል
ታዲያ የአሮጌ አዳም የእርሱ ልጆች
የስጋ ውልድ የዓለም ሰዎች
ላንሆን ጌታን ተቀብለን
ስንኖር ሳለን በእርሱ ታምነን
ለእጸበለስ ዛሬም ታለልን
አይኖቻችን ይህን ዓለም ሲቋምጡ ግሳንግሱን
በጉያችን የያዝነውን አስነጠቅን እንቁአችንን
ላውርድ እያልን እንቃይ ቆጡን
ቁስ አፍቃሪ ቁስ ወዳጆች
ለቁስ ኑረን ለቁስ ሟቾች
ፈቀቅ ላንል ከሰው ተርታ
ገንዘብ ወደን ስናምታታ
ታማኝነት ጸጋችንን
ገድለን ቀበርን እንቁአችንን
ላውርድ እያልን እንካይ ቀጡን::
ላንረካ ላንጠረቃ
ከአልጋችን ስንነቃ
ቆንጆ ወደን ቆንጆ ናፍቀን ከንፈን
የሰዶምን ልምላሜ ከሩቅ አየተን
ተው ስንባል እንቢ ብለን
የእርሱን መንፈስ አስመረርን
በዚያው ልንቀር በዲን ቀልጠን
ተው ስንባል እንቢ ብለን
የእርሱን መንፈስ አስመረርን
በዚያው ልንቀር በዲን ቀልጠን
ተው ስንባል እንቢ አልን
ትእግስቱን እየፈተንን
ቁጣው ነዶ እስኪያነፍረን
ግን ምነው ቸኮልን ምነው ቸኮልን
ልንጠፋ የእርሱን መንፈስ ስናክፋፋ
ተው ተመለስ ተይ ተመለስ ተይ ተመለሽ
አይምሰልሽ የሚያድንሽ ይህ ሽብሸባሽ
ይሕ ጩኸቴ ይህ ጩኸትሽ
ምን ? የዳንነው በጸጋው ነው?
ታዲያ እኔ መቼ ይህንን ካድኩት
ለሐጢአት መሸፈኛ አናድርገው
ነው እንጂ ያልኩት
ያ እኮ ነው ጉድ ያደረገን
የወሰድነው ቁንጽል ቃሉን
ተጠርቀን እንዳንኖር ያወረደን ከመስቀሉ
ሃናንያና ሰጲራን ለማየት የጋረደን
የአዲስ ኪዳን ነዋሪዎች መሆናቸውን
አስዘንግቶን
በጸጋው ድነሃል ብሎ ከቅድስና ያሸፈተን
ያ ነው ጉድ ያደረገን
የወሰድነው ቁንጽል ቃሉ
ተጠርቀን እንዳንኖር ያወረደን ከመስቀሉ
በእርግጥ ጸጋውማ አድኖናል
በእየሱስ ደም አምልጠናል
መዳናችን እንዲፈጸም
ከኃጢአት ለምን አንርቅም ?
አይኖቻችን ከመስቀሉ
ዳግም እዚያው ይሰቀሉ!
መቅደሳችን ይጥራ ጓዳው!
አዎ ቅድስና ለእግዚአብሄር ነው!!
ቅድስና ለእግዚአብሄር ነው!

እግዚአብሄር እጁን ከሚያወጣ ፣ ከእኔ ኑሮ ፣

ከእኔ ሕይወት፤ ከእኔ መውጣት መግባት ውስጥ የእግዚአብሄር እጅ ከሚወጣ ሌሎች እጆች ተጠቅልለው ይውጡ::
መለመን ካስፈለገ ስለእግዚአብሄር እየተባለም አንድ ቂጣ ተበልቶ ማደር ይቻላል :: መሞትም ካስፈለገ መሞት ይቻላል:: ግን እግዚአብሄር ከሕይወታችሁ ከሚርቅ ፣ የሚሔድ ነገር ካለ ይሂድ::
በእግዚአብሄር ፈቃድ ውስጥ የእግዚአብሄር መገኘት ይበዛላችኋል :: ክርስቲያኖች እባካችሁ ፀልዩ!! በር ስለተከፈተ ዘው አትበሉ:: እዛ ውስጥ አንቆ የሚይዝ ነገር ሊኖር ይችላል :: አንዳንዶቻችን በር ስለተከፈተ ብቻ የእግዚአብሄር ፈቃድ ነው እንላለን::ላይሆንም ይችላል:: እዚያ ምን እንደሚጠብቅህ ማወቅ አለብህ :: በሩ ይዘጋ:: ተዘግቶም የእግዚአብሄር ፈቃድ ይሆናል :: ለምን?እግዚአብሄር፤ሊከፍተው ይችላልና:: አዎ ጠይቁ እግዚአብሄርን :: በመውጣትና በመግባት ውስጥ እግዚአብሄርን ጠይቃችሁ መውጣት መግባት ተለማመዱ :: በሕይወታችን ውስጥ የእግዚአብሄር ፈቃድ ይሁን ::
አስተሳሰባችን መቀየር አለበት :: እኛ ከአለም ስንመጣ ይዘነው የመጣነው አመለካከት አለ :: በእግዚአብሄር ያለው አመለካከት መጽሐፍ ቅዱሳዊ ነው:: አስተሳሰባችን በዚህ መታረም አለበት :: መንፈሳዊ ሕይወታችንን በፊሎሶፊ ልንመራ አንችልም፤: መንፈሳዊ ሕይወታችንን በፊዚክስ፣ በኬሚስትሪ ልንመራ አንችልም::

መንፈሳዊ ሕይወታችንን ልንመራ የምንችለው በእግዚአብሄር ቃል ሃሳብ ነው:: አንዳንዶቻችን ደግሞ የእግዚአብሄርን ቃል አንወድም :: ሰባኪ አንኳን ሲሰብክ የሚሰበን ተረቱ ነው:: ስንት ነገር ተናግሮ ተረቷን ይዘን እንሄዳለን :: ተረቱ ስላልጠቀመን ነው የመጣነው!! እውነት ግን አርነት ያወጣናል :: አሜን! --//---

# የጥያቄዎ መልስ

1ኛ ጥያቄ

በ2ኛ ዮሐንስ ምዕራፍ.2 ላይ ለተመረጠችው እመቤትና ለልጇ የሚል ቃል አለ ፡፡ እንዲሁም ኢሳያስ 60፡14 ላይ ደግሞ “የናቁሽ ሁሉ ወደ እግርሽ ጫማ ይሰግዳሉ” ይላል ፡፡ ብዙዎች ይህን ክፍል ሲያነቡ የተጻፈው ለማርያም ነው ይላሉ፡፡ ይህ እውነት ነውን? እባካችሁ አብራሩልኝ፡፡

<u>መልስ በወንድም ከፋሲል ግዛው</u> ፡-

በኢሳያስ 60 ላይ ብቻ ሳይሆን በአጠቃላይ በኢሳያስና በተለያዩ የብሉይ ኪዳን መጽሐፍት ላይ ስለ ጽዮን የተነገሩ ክፍሎች አሉ ፡፡ አንዳንድ የሃይማኖት ክፍሎች ስለጽዮን የተነገሩትን ክፍሎች በሙሉ በቀጥታ ከማርያም ጋር አያይዘውት ትርጓሜ ይሰጣሉ ፡፡ ከዛ የተነሳ ለጽዮን የተነገሩ መልካም ነገሮችን በሙሉ ለማርያም እንደተነገሩ አድርገው ይቀበሉታል፤ ይተረጉሙታል ፡፡ ያም ብቻ ሳይሆን በዚህ ጥያቄ ላይ እንደተጠቀሰው በሁለተኛ ዮሐንስ ቁ.2 ላይ የተገለጸችውን እመቤት ማርያም እንደሆነች ይናገራሉ ፡፡

እንግዲህ ይሄ ያላቸውን አመለካከት አጠንክረው ለማቅረብ ካላቸው ፍላጎት የተነሳ በብሉይ ኪዳንም ላይ በአዲስ ኪዳንም ላይ የሚያገኙትን ነገር በቀጥታ ከማርያም ጋር የማያያዝ ነገር እንዳለ እንመለከታለን ፡፡ አንድ በቀጥታ መመልከት ያለብን ነገር ብሉይ ኪዳን ላይ ያለውን ቃል ስንተረጉም መጠንቀቅ ያለብን መሆኑ ነው ፡፡ በብሉይ ኪዳን ላይ አዲስ ኪዳን ላይ የምናያቸውን ነገሮች ክንዋኔ አልጀመሩም ፡፡ ተስፋው ወይም ትንቢቶች አሉ ፡፡ ብሉይ ኪዳን ላይ ግን እግዚአብሄር እየተናገረ ያለው ነገር ለእስራኤል ነው ፡፡

በዘፍጥረት ም.3 ቁ. 15 ላይ ተስፋ ከተሰጠበት ጊዜ ጀምሮ ዓለምን ሁሉ በክርስቶስ ኢየሱስ በኩል የማዳን ተስፋን እውን ለማድረግ በዘፍጥረት ም.12 ላይ እግዚአብሄር አብርሃምን ሲጠራ እንመለከታለን ፡፡ የአብርሃምን ዘር እያበዛ፤ እያበዛ በቁጥር 70 ከሆኑ በኋላ ወደ ግብጽ እንደገቡ እናያለን ፡፡ በዘጸአት መጽሐፍ ላይ እንደገና እስራኤላውያንን ከግብጽ ሐገር የማውጣት እንቅስቃሴ እናያለን፡፡ እግዚአብሄር ለአብርሐም በዘፍጥረት15 ላይ ቃል እንደገባለት ከጉልበትህ የሚወጣው ህዝብ በባእድ ምድር ለ400 ዓመት ይገዛል፤ ከዛ በኋላ ይወጣል ተብሎ የተሰጠውን ቃልኪዳን እንዲፈጸም እግዚአብሄር እስራኤልን ከግብጽ ሃገር ሲያወጣ እንመለከታለን ፡፡ ከግብጽ ሐገርም ካወጣ በኋላ ምድሪቷ ላይ ሲያሰፍራቸው እንመለከታለን፡፡ አንግዲህ ጽዮን የሚለውን ነገር በትክክል ማወቅ አለብን ፡፡ ጽዮን ማለት እስራኤል ሐገር ኢየሩሳሌም ውስጥ ያለው ቤተመቅደሱ ያለበት አካባቢ ነው ፡፡ እዛ ቤተመቅደሱ ይገኛል፡፡ይህ ማለት የእግዚአብሄር መገኘት በዚያ ሥፍራ ላይ አለ ማለት ነው ፡፡ በዘዳግም 12 ላይ እሥራኤል አግዚአብሄር እንደተናገረው እኔ በማሳይህ ሥፍራ ቤተመቅደሴን ትሰራለህ፡፡ በዚያ ስፍራ በአንድ ልብ በአንድ ሃሳብ ታመልኩኛላችሁ እንዳላቸው በዚያ ስፍራ ማለትም በጽዮን አካባቢው ላይ ቤተመቅደሱ ተሰርቷል ፡፡ እንግዲህ በተደጋጋሚ እግዚአብሄር ስለጽዮን ሲናገር በዛ ወቅት ከእስራኤል ጋር ስላለው ግንኙነት የሚገልጽ ነው ፡፡ መጽሐፍ ቅዱሳችን የሚለንን እውነታውን መጠበቅ አለብን ፡፡ ምን ማለት ነው? በታሪክ ውስጥ በትክክል የተከናወነ መጽሐፍ እንደሆነ ማወቅ አለብን ፡፡ የመጽሐፍ ቅዱሳችንን ነገር መጠበቅ አለብን፡፡ አለበለዚያ መጽሐፍ ቅዱሳችን ስህተት ይሆናል ፡፡ እግዚአብሄር ራሱን በታሪክ ውስጥ ለህዝቡ የገለጠ አምላክ ነው ፡፡ እስራኤል ሲል እስራኤል የምትባል ህዝብ ነበረ፡፡ ጽዮን ሲል ጽዮን የሚባል ቦታ ፤ቤተመቅደስ ሲለን በዛ ዘመን ቤተመቅደስ ነበረ ፡፡ ነብያትን ሲያነሳ ኢሳያስ ኤርሚያስ እያለ ሲናገር እነዛ ሰዎች ነበሩ ማለታችን ነው ፡፡

በመጀመርያ መጽሐፍ ቅዱሳችን ውስጥ የተገለጡ ሃሳቦች በታሪክ ውስጥ እውነት እንደሆኑ ወይም በአንድ ወቅት ትክክለኛ ታሪክ እንደነበሩ መቀበል አለብን ፡፡ ይሄን ስናደርግ በትክክል እግዚአብሄር የተናገረው እውነት እንደሆነ ያደረገው እውነት እንደሆነ ተስፋ የገባው ነገር እውነት እንደሆነ መመልከት መቀበል አንጀምራለን ፡፡ በሌላ አባባል ወደኋላ ስንሄድ እንደልብወለድ መጽሐፍ አድርገን አንቀበለውም ፡፡ እግዚአብሄር ራሱን በትክክል የተገለጸበት ነው ፡፡

ባቢሎን ሲለን ሌላ ነገር አናስብም፡፡ ባቢሎን የሚባል ሃገር እስራኤልን መጥቶ እንደወረራት ብዙ ህዝብና ንብረት እንደወሰደ ቀጥታ በሆነ መንገድ እንቀበለዋለን፡፡ ይሄን ክፍል ወደተለያዩ ሃሳቦች ከተረጎምነው ግን ባቢሎን የሚባል፡ ሃገር አልነበረም ንጉስም አልነበረም አልወረራትም እያልን ታሪካዊ እውነታውን እየካድን እንሄዳለን ማለት ነው ፡፡ እንግዲህ መጽሀፍቅዱሳችን ላይ መጠንቀቅ ያለብን አንዱ ትልቁ ነገር ታሪካዊ እውነታዎችን መጠበቅ አለብን ፡፡

ብሉይ ኪዳን ላይ የእስራኤል ማህበረሰብ አለ፡፡ አሰፋፈሩን ሁሉ አስቀምጦልናል፤ ቦታውን ሁሉ አስቀምልናል፣ ቤተመቅደሱ የተገነባበትን ሥፍራ ጽዮንን አካባቢ በትክክል አስቀምጦልናል፡፡ ቤተመቅደሱ እንዴት እንደተገነባ በትክክል ተቀምጦልናል ፡፡ ጽዮንን በቀጥታ ከማርያም ጋር ካያያዝን በብሉይ ኪዳን ጽዮን የሚባል አካባቢ የለም ብለን እንደመካድ ይቆጠራል ፡፡ እንደገና በጣም መጠንቀቅ ያለብን ስለጽዮን በጎ ነገር ብቻ አይደለም የተነገረው ፡፡ እንደምትፈርስም፣ እንደሚያጠፋትም፣እግዚአብሄርን እንደካደችውም የተነገረባቸው ብዙ ሥፍራዎች አሉ፡፡ እነዚያን መልዕክቶችም አምጥተን ማርያም ላይ እናዛምድ ብንል የተሳሳተ ነገር ውስጥ እንገባለን፡፡ ስለዚህ በቀጥታ ያንን ክፍል ለእስራኤል፣ ለጽዮን ወይም ለአካባቢውና ለህዝቡ ብቻ ማስቀመጥ አለብን ፡፡ ይሔን ስንል ማርያም በአዲስ ኪዳን ያላትን ድርሻ እያሳነስነው አይደለም፡፡ ወደ አዲስ ኪዳን ስንመጣ በማቴዎስ ወንጌል ፣ በሉቃስ ወንጌል፣ማርቆስ ወንጌል እና የተለያዩ ክፍሎች ላይ ስለማርያም መሰጠት ፣ጌታን ስለመውለዷ፤ ስለማርያም በጎ ሥራዎች ፣እና እግዚአብሄርም ስለገባላት ቃል በትክክል ያስቀምጣል ፡፡ እዚህ ስፍራ ላይ ስንመጣ ለማርያም ያለን አክብሮት እየጨመረ ይመጣል ፡፡ ነገር ግን ለማርያም ያለንን መስጠትና ለማርያም ያለንን አክብሮት የምንጨምረው ከማይገቡ ጥቅሶች ላይ ተነስተን ሳይሆን በትክክል ከተገለጠው ከመጽሐፍ ቅዱስ ሐሳብ ላይ ተነስተን ነው ፡፡ ስለዚህ ብሉይ ኪዳን ላይ ስለጽዮን የተነገረው ነገር በሙሉ ስለማርያም የተነገረ አይደለም ፡፡ ስለማርያም ወይም ከድንግል እንደሚወለድ ተስፋ ተሰጥቷል ፡፡ ኢሳያስ ም.7 ላይ በግልጽ የተቀመጠልን ነገር አለ፡፡ ይህንን በትክክል እንቀበላለን፡፡ ብለይ ኪዳን ጽዮን ሲል ስለማርያም እየተናገረ አይደለም፡፡ ጽዮን ከተማ አለ፡፡ እዚያ አካባቢ ቤተመቅደስ እንዳለ እንመለከታለን ፡፡

በ2ኛ ዮሐንስ ም.1 ቁ.2 ላይ የሚናገረው ክፍል ስለእመቤቷ ሲናገር አንድ ነገር አዕምሮአችን ላይ እንዲመጣ ያስፈልጋል ፡፡ በሐዋ.ሥራ ም. 1 ላይ ‘ሐይልን በተቀበላችሁ ጊዜ በኢየሩሳሌም፤ በሰማርያ በገሊላ እስከ ምድር ዳርቻ ምስክሮቼ ትሆናላችሁ፡’ ይላል ፡፡ ምዕራፍ.2 ላይ ደግሞ ሃይልን ሲቀበሉ እናያለን፡፡ ከምዕራፍ ሁለት ጀምሮ በኢየሩሳሌም ወንጌልን ሲያሰራጩ እንመለከታለን ፡፡ ከምዕራፍ.8 ቁ.2 ጀምሮ ደግሞ ወደ ሰማርያ ሲንቀሳቀሱ እንመለከታለ ፡፡ ከምዕራፍ.13 ቁ.2 ጀምሮ ደግሞ መንፈስ ቅዱስ ‘ጳውሎስና በርናባስን ለጠራኋቸው ሥራ ለዩልኝ’ ሲልና ጳውሎስና በርናባስ ሲለዩ ፤ወደ ተለያዩ ሥፍራዎች ቤተክርስቲያንን ማስፋት ሲጀምሩ እንመለከታለን ፡፡ በዚህ ውስጥ አብረን መረዳት ያለብን ነገር በዚያ ዘመን ያለችው ቤተክርስቲያን ቦታ ወስዳ ህንጻ ገንብታ የምትንቀሳቀስ አይነት ቤተክርስቲያን አይደለችም ፡፡ የምትሰበሰበው በቅዱሳን ሰዎች ቤት ውስጥ ነው

ስለዚህ ዮሐንስም የጻፈው በቤቷ ቤተክርስቲያን እንድትመሰረት ላደረገች ሴት እንጂ ለማርያም አይደለም ፡፡ ለማርያምማ ቢሆን በቀጥታ ስሟን ይጠቅሳል ፡፡በ1ኛ ዮሐንስና 2ኛዮሐንስ ላይ ያሉትን ጽሁፎች ቀና በሆነ ልብ እንድንመለከታቸው ያስፈልጋል፡፡በሁለተኛው የሐዋርያው ዮሐንስ መልእክት ላይ “በእኛ ስለሚኖርና ከእኛ ጋር ለዘላለም ስለሚኖር እውነት እኔ ሽማግሌው በእውነት ለምወዳቸውና እኔ ብቻ ሳልሆን እውነትን የሚያውቁ ሁሉ ደግሞ ለሚዷቸው ለተመረጠች እመቤትና ለልጆችዋ” (ቁ1-2)ይላል፡፡ እዚህ ላይ እንደምናየው የተጻፈው ለልጆቿ ብቻ አይደለም ፡፡ እውነትን ለሚያውቁ ሁሉ ደግሞም ለሚወዷቸው ፤ ለተመረጠች እመቤትና ለልጆቿ እያለ ይናገራል ፡፡ይህ ከማርያም ጋር የተያያዘ አይደለም ፡፡ በቤቷ ቤተክርስቲያን ለተመሠረተባት ሴት እየጻፈላት ነው ፡፡ ቤቷ ውስጥ ለሚሰበሰቡት ሰዎችና ለእርሷም ልጆች ይሄን መልእክት እየጻፈላቸው እንዳለ እንመለከታለን ፡፡

ይህ መልእክት የሚናገራቸው የተለያዩ ሃሳቦች አሉ ፡፡ እንዴት ትዕዛዝን ለአብ እንደተቀበሉ ይናገራል ፤ እንዴት አንዳንዶች ከዚህ ትእዛዝ እንደወጡ ፤ ብዙ አሳቾች ከዓለም ወደ ቤተክርስቲያን እንደገቡ ፤ክርስቶስ በሥጋ እንደመጣ የማያምኑ ሰዎች እንዳሉ ይናገራል ፡፡

➔

እንግዲህ ይህን ሁሉ በቀጥታ ከማርያም ጋር ካዛመድነው ማርያም ክርስቶስ በስጋ እንደመጣ ወደአለማመን አሳቾች እያሳቷት ወደ ተሳሳተ ነገር እየገባች ስላለ ዮሐንስ ሊያስተካክላት እንደጻፈ እየተቀበልን ነው ማለት ነው ። አንድን ክፍል ስንተረጉም እመቤት የሚለውን ማርያም ነች ካንል ውስጥ ያለውን መልእክት ለእርሷ እንደተጻፈ አብረን መቀበል አለብን። "..አዲስ ትእዛዝ አይደለም የምጽፍልሽ ..ብዙ አሳቾች ወደአለም ገብተዋልና፡እነርሱም ክርስቶስ በስጋ መምጣቱን የማያምኑ ናቸው.." ። ይላታል። ትእዛዝ ያስተላልፍላታል። ስለዚህ እነዚህን ክፍሎች ዮሐንስ ሲጽፍ ይህችን ሴትና ከእርሷ ጋር ያሉትን ምእመናን ከዚህ ስህተት ለመታደግ ነው ። ስለዚህ ይህ መልዕክት ከማርያም ጋር መዛመድ የለበትም ።

2ኛ ጥያቄ ፡-

መጽሐፍ ቅዱስ ሲናገር የልጁ የእየሱስ ክርስቶስ ደም ከሐጢአት ሁሉ ያነጻል ይላል ። እንዲሁም በሌላ ሥፍራ በመንፈስ ቅዱስ ላይ ስድብን የተናገረ የኃጢአት ስርየት እንደሌለው ይናገራል ። ይህ ሥረየት የሌለው የስድብ ቃል ምን አይነት ስድብ ቢሆን ነው ?

<u>መልስ በወንድም ከፋሲል ግዛው</u> ፡-

መጽሐፍ ቅዱሳችን የልጁ የእየሱስ ክርስቶስ ደም ከማንኛውም ኃጢአት እንደሚያነጻ ይናገራል ። ይህንንም ክፍል በ1ኛ ዮሐንስ ምዕራፍ.1 ቁ.7 ላይ እናገኘዋለን ። በሌላ በኩል ደግሞ እንደተባለው በማቴ.12 ቁ.32 ላይ መንፈስ ቅዱስን የሚሳደብ አይሰረይለትም ይላል ። ስለዚህ የክርስቶስ ደም ከኃጢአት ሁሉ ነጻ ያወጣል እያለ እንደገና በመንፈስ ቅዱስ ላይ የተሳደበ ኃጢአቱ ስርየት የለውም ሲል ላይ ላዩን ስናየው እርስ በርሱ የሚጋጭ ይመስለናል ። ግን የሚጋጭ አይደለም ። በዚህ ስፍራ ላይ አሁንም እንደገና ተመልሰን መመልከት ያለብን ከጥቅሱ ባሻገር አውዱን ወይም ክፍሉ ላይ ያለውን አጠቃላይ ሐሳብ መመልከት አለብን ።በማቴ12 ላይ ክርስቶስ በእርኩስ መንፈስ የተያዘውን ሰው ነጻ ካወጣ በኋላ ክርስቶስ ያገለገለበትን አገልግሎት ሰዎች ወይም ካህናትና፣ እስራኤላው ወይም አይሁዳውያን ሲያጣጥሉት እንመለከታለን። ክርስቶስ አጋንንትን ያወጣው በብኤልዜቡል መንፈስ እንደሆነ ተናገሩ። እየተናገሩ ያሉት ጉዳይ ወይም በቀጥታ እዚህ ሥፍራ ላይ ስድብ ተብሎ የተቀመጠው ጉዳይ እኛ በቀን ተቀን ግንኙነታችን በምናውቀው ስድብ ብለን በምንላቸው አስጸያፊ ቃላቶችን አይደለም ። ክርስቶስ በእግዚአብሄር ሐይል ወይም በመንፈስ ቅዱስ ሐይል ነበር ያገለገለው። በማቴ. 4 ላይ እና በሌሎችም ወንጌላት መጀመርያ ላይ እንደምንመለከተው ክርስቶስ እየሱስ አገልግሎት ከመጀመሩ በፊት በመንፈስ ቅዱስ ሲሞላና በመንፈስ ቅዱስ ወደ ምድረበዳ ሲሄድ እንደገና በመንፈስ ቅዱስ ምሪት ወደ ገሊላ ሲመለስ እናገኛለን ። ክርስቶስ አገልግሎቱን ሲጀምር በመጀመሪያ ያደረገው ከኢሳያስ መጽሐፍ ላይ ጠቅሶ እግዚአብሄር ቀብቶኛል ብሎ ነው የተናገረው ። የእግዚአብሄር መንፈስ በእርሱ ላይ ነበር ። ስለዚህ በክርስቶስ እየሱስ ላይ ያለውን የመሲህነት ሥራ የሚገልጠው መንፈስ ቅዱስ ነው ።

በብሉይ ኪዳን መጽሐፍ ላይ መሲሁ ሲመጣ የሚያከናውናቸው ነገሮች ተዘርዝረው ተቀምጠዋል ። የእግዚአብሄርን መንግስት እንደሚሰብክ ፣ለድሆች ወንጌልን እንደሚሰብክ ፣ተአምራትን እንደሚያደርግ ፣ህዝቡን እንደሚያሳርፍ የተሸለ ቃልኪዳን እንደሚስገባ፣ ብዙዎችን እንደሚያተርፍ ተዘርዝሮ በኢሳያስ 53 ላይ ተገልፅዋል።ስለመሲሁ የተቀመጡ መገለጫዎችን በብሉይ ኪዳን መጽሐፍ ላይ በተለያየ ሥፍራ ላይ እናገኛለን ። ስለዚህ በሌላ አባባል በክርስቶስ እየሱስ ላይ የመሲሕነቱን ሥራ እየገለጠ ያለው ራሱ መንፈስ ቅዱስ ነው ። በዚህም ሥፍራ ማለትም በማቴዎስ ምዕራፍ12 ላይ እርኩስ መንፈስ የተጠናወተውን ወይም ጋኔን ያደረበትን፣ዲዳ የሆነውን ሰው ወደ



እየሱስ ሰዎችን ሲፈውስ

እርሱ አምጥተውለት ሲፈውሰው ፈሪሳውያን ይቃወሙታል ። የምትሠራው ከአጋንንት ነው፡ ይሉታል ። ማቴ.12 ቁ 24 ላይ ስንመለከት " ፈሪሳውያን ግን ይህን በሰሙ ጊዜ እርሱ አጋንንትን የሚያስወጣው በብኤልዜቡል በተባለው በአጋንንት አለቃ ነው አሉ" ይላል ።

ይሄ በቀጥታ የተቃረነው፡ ጌታ መንፈስ ቅዱስን ነው ። ክርስቶስ በመንፈስ ቅዱስ ሃይል አጋንንትን አስወጥቷል። ፈሪሳውያን ደግሞ በብኤል ዜቡል መንፈስ ወይም በአጋንንት አለቃ ሌሎችን አነስ ያሉ አጋንንቶችን ያስወጣል ወይም ደግሞ በእርሱ ላይ የሚሠራው የእግዚአብሄር መንፈስ አይደለም እያሉ ነው ።

➔

# ከደብዳቤዎቻችሁ

➢ በምትልኩልን ደብዳቤዎችና ጋዜጦች ተባረከናል ።

ከሬዲዮ ፕሮግራማችሁ አልፎ በምትልኩልን ደብዳቤዎችና ትምህርት አዘል መንፈሳዊ ጋዜጦች እኛ ሐገርን ከውጪ ጠላት ለመጠበቅ በየዳር ድንበሩ የተሰማራነው የመከላከያ ሠራዊቶች ብዙ ትምህርቶችን ፣ መበረታቻን፣ ሰላምንና ፣ መጽናናትን አግኝተናል ። ስላገኘነው በረከት እግዚአብሄርን እያመሰገንን ላሕያው ተስፋ አገልጋዮች በሙሉ ልባዊ ምስጋናን ስም አቀርባለሁ

ታሪኩ ካሳ
ከእንትጮ

የባህታዊው ደብዳቤ

በስመ አብ ወወልድ ወመንፈስ ቅዱስ አሐዱ አምላክ አሜን ። የተወደዳችሁ የክርስቶስ አገልጋዮች እንደምን ሰንብታችኋል ? እኔ ቸሩ አምላክ ይመስገን በጣም ደህና ነኝ ። እኔ የምኖረው ከዓለም ተለይቼ በገዳም ውስጥ ነው ። የኦርቶዶክስ ሐይማኖት ተከታይ ነኝ ። እናንተ ከየትኛው ሐይማኖት እንደሆናችሁ አላውቅም ነገር ግን በውስጤ ያሉት ልዩ ልዩ መንፈሳዊና መጽሐፍ ቅዱሳዊ ጥያቄዎች ሁሉ በሬዲዮ የጥያቄዎ መልስ ፕሮግራማችሁ ላይ ተመልሶልኛል ። ፕሮግራማችሁን ያገኘሁት ድንገት ሌሎች ፕሮግራሞችን ስፈልግ ነው። በጣም ልዩና ትምህርት ሰጭ ፕሮግራም ስለሆነ በርቱ እግዚአብሄር ከእናንተ ጋር ይሁን እላለሁ።

ስማቸውያልተጠቀሰ ከደብረማርቆስ
ተክለሃይማኖት ገዳም

ሕይወቴ እና አገልግሎቴ
የተገነባው በእናንተ አገልግሎት ነው !

ውድ ሕያው ተስፋዎች እንደምን አላችሁ? ደህና ናችሁ ? ከአስር ዓመት በላይ የእናንተን ሬዲዮ ፕሮግራም ስከታተል ቆይቻለሁ ። የእኔ ሕይወትና አገልግሎት በብዙ መልኩ የተገነባው በእናንተ አገልግሎት ነው ። ከጥቂት ዓመት በፊት በእስር ቤት እያለሁ የእናንተ ፕሮግራም ትልቅ አጽናኜ ነበር ። ከእናንተ የሚደርሱኝ ልዩ ልዩ የጽሁፍ መልእክቶች ትራክቶችና ጋዜጦች በጊዶሌ ቃለሕይወት ላለው አገልግሎቴ ትልቅ መሳርያዎቼ ነበሩ ። አሁንም ቃል ልገባላችሁ የምፈልገው ከእናንተ ጋራ ያለኝን ግንኙነት እንደምቀጥልና የክለባችሁ አባል መሆን እንደምፈልግ ነው ። እግዚአብሄር አገልግሎታችሁን ይባርክ ፡

አስራቴ ማቴዎስ
ከአርባ ምንጭ

ስለዚህ ጌታ ኢየሱስ ሊያስተካክላቸው :- በማቴ12:23 ላይ እንዲህ አላቸው ይላል።

# ሕያው ተስፋ ሬዲዮን በማድመጥ

“አንድ መንግስት ተከፋፍሎ እርስበርሱ የሚጋጭ ከሆነ ያ መንግስት ይወድቃል ። እንዲሁም አንድ ከተማ ወይም አንድ ቤተሰብ

**በአማርኛ ከምሽቱ 1.:30 -2: 00**
በ25ሜትርባንድ(12125 khz) አጭር ሞገድ

**በኦሮምኛ ከምሽቱ 2-2 :30**
በ31 ሜትር ባንድ( 9595 khz) አጭር ሞገድ
ሕያው ተስፋ ሬዲዮ አገልግሎት
የፖ.ሳ. ቁ.9431 አ. አ.
E mail info@hiyawtesfa.org
Website www.hiyawtesfa.org
ሥልክ 0910223561

# መንፈሳዊ ሕይወትዎን ይመግቡ

እርስበርሱ ከተለያየ ጸንቶ መኖር አይችልም ። ሰይጣንንም ሰይጣን የሚያስወጣ ከሆነ እርስበእርሱ ተለያየ ማለት ነው ታዲያ መንግስቱ እንዴት ጸንቶ ሊኖር ይችላል? ደግሞስ እኔ አጋንንትን የማስወጣቸው

**የአማርኛ ፕሮግራሞች**

ሰኞ --- ቤተሰባችን

ማክሰኞ - የጥያቄዎ መልስ

ዕሮብ --- ታውቃላችሁን

ሐሙስ --- ከደብዳቤዎቻችሁ

አርብ -- ከመንፈሳዊ ሴማታችን

ቅዳሜ --- ራሱ ይናገር

እሁድ --- ወጣት ለክርስቶስ

በብኤልዜቡል ከሆነ ልጆቻችሁስ በምን ያስወጧቸዋል? ስለዚህ ልጆቻችሁ በእናንተ ላይ ይፈርዱባችኋል” አላቸው።
እኔ አጋንንትን የማስወጣው በእግዚአብሄር መንፈስ ከሆነ የእግዚአብሄር መንግስት ወደ እናንተ መጥታለች ማለት ነው ”አላቸው። ክርስቶስ እየሱስ እራሱ አጋንንትን የሚያስወጣበት መንፈስ የእግዚእበሄር መንፈስ እንደሆነ አስረግጦ ይነግራቸዋል ። ስለዚህ እዚህ ሥፍራ ላይ እንደምናየው ለእነዚህ ሰዎች ስድብ የተባለው ነገር ክርስቶስ በመንፈስ ቅዱስ ሀይል አጋንንትን እያስወጣ መሲህያዊ ማንነቱን መንፈስ ቅዱስ ሲገልጥ እነዚህ ሰዎች ግን ‹አይደለም› ብለው ሲቃወሙ በሌላ አባባል መሲህነቱን አንቀበልም እያሉ ነው ። መሲሕነቱን ያልተቀበለ ሰው ደግሞ የዘላለም ህይወት ሊኖረው አይችልም ።
ኃጢአቱ ሊሠረይለት አይችልም ። በአብ በኩል ብቻ ሊሄድ ወይም ደግሞ በሌላ መንገድ ወደ እግዚአብሄር እገባለሁ ቢል አይችልም ። መጽሐፍ ቅዱስ ዮሐንስ ወንጌል ላይ ‘ልጁ የሌለው አብ አንኳን የለውም’ ይላል ። ልጁን ደግሞ የሚገልጠው መንፈስ ቅዱስ ነው ። ስለዚህ መንፈስ ቅደስን መሳደብ ማለት ይሔ በተለምዶ በኛ ዘመን ላይ ያለውን ስድብ መሳደብ ማለት አይደለም ። መንፈስ ቅዱስን መሳደብ ተብሎ የተቀመጠው መንፈሱ ቅዱስ ክርስቶስ እየሱስ እንደሆነ፤ መሲህ እንደሆነ፤ አዳኝ እንደሆነ በተአምራት ሊሆን ይችላል፣ በስብከት ሊሆን ይችላል፣በተለያዩ አገልግሎቶች ሊሆን ይችላል፡በሚገልጥበት ጊዜ ሰው ‹ያንን ያደረገው የአጋንንት መንፈስ ነው› ብሎ ሲያስብ ያ ሰው ክርስቶስ እየሱስን አይቀበልም ። ክርስቶስ እየሱስን ካልተቀበለ ደግሞ የዘላለም ሕይወት አይኖረውም ወይም ኃጢአቱ አይሰረይለትም ። ምክንያቱም ክርስቶስ እየሱስ መሲህ እንደሆነና ስለሰዎች ኃጢአት በመስቀል ላይ እንደሞተ በምናምንበት ጊዜ ያን ጊዜ ደሙ ከኃጢአታችን ሁሉ ያነጻናልና ነው፡ ይሄን ደግሞ እውነታ የሚገልጸው ጌታ መንፈስ ቅዱስ ነው ። በዮሐንስ ወንጌል14፣15-16 ላይ እየሱስ፡ ‘እርሱ በመጣ ጊዜ እኔን ያከብረኛል፡ ወደ እውነት ሁሉ ይመራችኋል ፣ያስተምራችኋል፣ያሳስባችኋል”እያለ ስለመንፈስ ቅዱስ ተናግሯል ።እርሱ ክርስቶስን ያከብራል፤ ስለኃጢአት ዓለምን ሁሉ ይወቅሳል ይላል ። ይህን ሊገልጥ የሚችለው መንፈሱ ነው። መንፈሱ በሚገልጥልን ጊዜ ክርስቶስ እየሱስ ትክክለኛ መንገድ እንደሆነ፤ እርሱን መቀበል የዘላለም ሕይወት እንደሚሰጥ፤ እርሱን በመቀበል በላያችን ላይ ያለው ኃጢአት ተወግዶ ወደ እግዚአብሄር መንግስት መግባት እንደምንችል መንፈሱ አብርሆትን በሚሰጠን ጊዜ ያን የገለጠውን መንፈስ አለመቀበል መንፈስ ቅዱስን እንደመስደብ ነው። ይሄ ደግሞ ኃጢአታችንን እንዳይሰረይ ያደርጋል። ለምን? ምክኒያቱም ኃጢአትን ሊያስተሰርይ የሚችለውን የእየሱስ ክርስቶስን ደም ወይም እየሱስን መንፈሱ ሲገልጥልን አልተቀበልነውምና ነው ። ስለዚህ ሀሳቦቹ ግጭት የላቸውም። መንፈሱን መሳደብ ማለት እኛ አንደምናውቀው በዚህ ዘመን እንዳለው አይነት ስድብ ሳይሆን መንፈሱ እየሱስን ሲገልጠው አለመቀበል ማለትመንፈሱን አለማክበር ወይም መንፈሱን እንደመስደብ ተደርጎ በመጽሐፍ ቅዱሳችን ላይ ይወሰዳል። መንፈስ ቅዱስን የሰደበ በሌላ አባባል ክርስቶስ ኢየሱስን ሲገልጥለት ያልተቀበለ ሰውና ለኃጢአቱ ንስሐ ያልገባ ሰው ኃጢአቱ አይሰረይለትም ማለት ነው። በየትኛውም መንገድ አይሰረይለትም ።

## *የዘላለም ሕይወት ማግኘት ለሚፈልጉ!!*

**_የሞትን ድልድይ በእየሱስ ተሻገር!!**



**እግዚአብሄር ይወድሀል !! የዘላለም ሕይወትን ሊሰጥህ ይፈልጋል ከአንተ ግን የሚጠበቅ ነገር አለ ይኸውም : ኃጢአት ሰርተሃል ኃጢያተኛ መሆንህን እመን።"ሁሉ ኃጢአትን ሠርተዋል የእግዚያብሔርም ክብር ጎድሎአቸዋል” ይላል ቃሉ።**
**የኃጢአት ትንሽ የለዉም ዉሸት፣ ሃሜት፣ ማመንዘር፣ መስረቅ፣ መግደል፣ ሁሉ ሐጢአት ነዉ።* የኃጢአት ደሞዝ ሞት ነዉ (ሁለተኛ ሞት) ከእግዚያብሔር መለየት በገሃነም እሳት ለዘላለም መጣል።**
*** ኢየሱስ ክርስቶስ ለፍርድ ይመጣል።ባልተቀበሉት ሰዎች ሁሉ ላይ ሊፈርድባቸዉ የሚመጣ ኢየሱስ ብቻ ነዉ።**
*** ይህ ጊዜ ግን የፍቅርና የምህረት ጊዜ ነዉ ኢየሱስ ክርስቶስ ይወድሃል ከዚህ ፍርድ ሊያድንህ ዋጋ ከፍሎልሃል። በመስቀል ላይ የኃጢአት ዕዳህን ሁሉ ከፍሎልሃል።**
*** ስለዚህ ጊዜ ሳያልፍብህ የፍርድ ቀን ሳይመጣ እየሱስን ተቀበል።እንደ ግል አዳኝህ አድርገህ ተቀበለዉ ወደ ልብህ አስገባዉ በንስሃም ወደ እርሱ ቅረብ።**
*** ኢየሱስ እንዲህ ይልሃል፡- እኔ የዓለም ብርሃን ነኝ የሚከተለኝም የሕይወት ብርሃን ይሆንለታል እንጂ በጨለማ አይመላለስም!!**
**እየሱስን አምናለሁ ማለት ብቻ በቂ አይደለም አምነህ ካልተከተልከው አትድንም!!**
*** እኔ መንገድና እዉነት ሕይወትም ነኝ በእኔ በቀር ወደ አብ የሚገባ የለም።**
*** በሩ እኔ ነኝ በእኔ የሚገባ ቢኖር ይድናል መሰማርያም ያገኛል።**
*** ሐዋርያዉ ጴጥሮስ እንዲህ አለ፡-መዳን በሌላ በማንም የለም እንድንበት ዘንድ የተሰጠን ከሰማይ በታች ሌላ የለምና።**
*** ኢየሱስ ክርስቶስ ያድንሃል የዘላለም ሕይወት ይሰጥሃል። እዉነተኛ ሰላምና ደስታን በዉስጥህ ያፈሳል። ከማንኛዉም በሽታ ነፃ ያወጣሃል ኢየሱስን ተከተል ኃጢአት መሥራትን አቁም።**
**አሁን እንዲህ ብለህ ፀልይ ጌታ**
**ኢየሱስ ሆይ ዛሬ ወደ አንተ መጥቻለሁ አንተ አዳኜ እንደሆንክ አምናለሁ ኃጢአተን ሁሉ ይቅር በለኝ ከእንግዲህ ወዲህ ኃጢአት እንዳልሠራ ጠብቀኝ። በቃልህ ሕይወተን አሳድግ ለዘላለም መንግሥትህ አብቃኝ። ከእግዚአብሄር ሰዎች ጋር ተገናኝ ወደ እግዚአብሄር ቤት ሂድ። መጽሐፍ ቅዱስ አንብብ በየዕለቱ ፀልይ። በአድራሻችን ጻፍልን፡**

**ሕያው ተስፋ ሬዲዮ አገልግሎት**

**የፖ.ሳቁ. 9431 አ. አ.**
**E mail info@hiyawtesfa.org**
**Website www.hiyawtesfa.org**
**ሥልክ 0910223561**